የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያ

የጎልማሶች ሰንበት ትምህርት

# የእውነት ውድ ሀብቶች (1)

# ከፈጣሪያችን ጋር መወያየት



## TREASURES OF TRUTH (I)

## Reasoning With Our Creator

ቅጽ 99 ቁ. 1

ታህሳስ 23/2015 - መጋቢት 16/2015

# የጎልማሶች ሰንበት ትምህርት

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያ

## የእውነት ውድ ሀብቶች (1)

## ከፈጣሪያችን ጋር መወያየት

ታህሳስ 23/2015 - መጋቢት 16/2015

በሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ተሐድሶ እንቅስቃሴ የጄነራል ኮንፍራንስ የሰንበት ትምህርት ክፍል በየሦስት ወሩ የሚታተምና በሪፎርሜሽን ሄራልድ የሕትመት ማህበር የሚሰራጭ ነው
5240 Hollins Road, Roanake
Virginia 24019-5048, U.S.A
Periodical Postage Paid at
Roanoke, Virginia 24022-999
tWebsite: www.sdarm.org
E-mail:info@sdarm.org

አንደኛ ሩብ ዓመት

የሰንበት መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ያለ አንዳች ተጨማሪ ሐሳብ በመጽሐፍ ቅዱስና በትንቢት መንፈስ ላይ ፍጹም የየዕለት ጥናት ነው። ጥያቄዎቹም በተቻለ መጠን አጭርና ግልጽ እንዲሆኑ ታስበዋል። በአንዳንድ ምክንያቶች መሠረታዊ ሐሳቡ ግልጽ ሆኖ እንዲስተዋል ሲባል ቅንፎች እንዲገቡ ተደርጓል። ጠለቅ ላለ ጥናት ከመሠረታዊ ምንጮች መረጃዎችን መጠቀም በጥብቅ ይመከራል።

# የእውነት ውድ ሀብቶች (1)

## ከፈጣሪያችን ጋር መወያየት

ማዉጫ                    ገጽ


1. የእግዚአብሔር ቃል ዛሬ ለሰው ልጆች..............5
2. ኃያሉ የእግዚአብሔር ቃል............................10
3. እሳታማ እባቦች.............................................15
4. ዘይት በመብራቱ ውስጥ ስጠኝ.....................20
5. ወንጌል በብሉይ ኪዳን.................................26
6. የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ህግ........................31
7. የወንጌል ምሥጢር......................................36
8. በመስቀሉ ላይ የተቸነከረ.............................41
9. ብንናዘዝ.......................................................47
10. “በእውነትህ ቀድሳቸው”.............................52
11. አሮጌዉ ኪዳን..............................................57
12. ኑ አብረን እንወያይ.....................................62

# መቅድም

ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ በዚህች ምድር ላይ ከ6,000 ለሚበልጡ ዓመታት የሠራውና ያቆየው በርግጥም አስደናቂና አስደማሚ ፍጥረት ናቸው። የታላቁ ፍጥረት ዘውድ ደግሞ በራሱ አምሳል የተፈጠረው የሰው ልጅ ነው! ይህ በዚች ፕላኔት ላይ ለመኖርና በእሷ ላይ የበላይነትን እንዲይዝ ታስቦ የተፈጠረ ፍጥረት ዘር ነው።

ለሰው ልጆች በተሰጠው የማሰብና የማመዛዘን ችሎታ ምክንያት ይህ ዝርያ–ሆሞ ሳፒየንስ– ይህ መብት በአደራ ተሰጥቶታል። ከምንም በላይ ግን በምድር ላይ ግርማ ሞገስ ባለው ፈጣሪ ፊት ለዘላለም የመኖር እድል የተሰጠው ፍጥረት እርሱ ብቻ ነበር።

እንደ ማንኛውም ልዩ መብትና ኃላፊነት፣ ይህም ቅድመ ሁኔታዎች ያሉት ነበር። ጻድቅና መሐሪ የሆነዉ የዓለማት ፈጣሪ እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች በፊታችን በግልፅ አስቀምጦልን፤ የቃል ኪዳኑን ዝግጅት እንድንረዳ ከእርሱ ጋር እንድንወያይ ይጋብዘናል።

ስለዚህ በሚቀጥሉት ሦስት ወራት ውስጥ በመላው ዓለም የሚገኙ የሰንበት ትምህርት ተማሪዎች "ከፈጣሪያችን ጋር ማመዛዘን" የሚለውን ዋና ርዕስ ያጠናሉ። ይህም በቀጣይ ለአንድ ዓመት ሙሉ ከምንማረዉ "የእዉነት ዉድ ሀብቶች" ከሚለዉ ትልቅ ዋጋ ያላቸውን አስደናቂ የእውነት እንቁዎች በመረዳት ለዘለአለም ለመታጠቅ ከሚሆነዉ ትምህርት የመጀመሪያዉ ክፍል ነዉ። የሚድኑ ሁሉ በአምላክ ላይ ጥልቅ፣ እውነተኛ እምነትና በምድር ታሪክ ውስጥ የመጨረሻውን ሰዓት የሚያጋጥሙትን ፈታኝ ፈተናዎች እንኳን ሳይቀር የሚጸና የድል አድራጊ ክርስቲያናዊ ተሞክሮ ሊኖራቸው ይገባል።

የማሰብ ችሎታ ላላቸው ፍጥረታት የተነገረው ሃይማኖት እውነተኛ ስለመሆኑ ምክንያታዊ የሆኑ ማስረጃዎችን ያዘጋጃል፤ ምክንያቱም በልብና በባሕርይው ውስጥ ከፍተኛ ውጤት ያስገኛልና። የክርስቶስ ጸጋ በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ይገለጣል። የተቀደሱ ነን የሚሉትን፣ የመንፈስ ፍሬዎች በህይወታችሁ ይገለጣሉን? የክርስቶስን የዋህነትና ትህትናን ትገልጣላችሁን፣ እንዲሁም በክርስቶስ ትምህርት ቤት በየቀኑ እየተማራችሁ መሆኑን፣ በህይወታችሁ ከራስ ወዳድነት ነጻ የሆነዉን የህይወቱን ምሳሌ በማንጸባረቅ እውነታውን ትገልጣላችሁን? ብለን እንጠይቅ።

ማናችንም ብንሆን ከሰማይ አምላክ ጋር ያለንን ግንኙነት ልናገኝ የምንችልበት ከሁሉ የተሻለው ማስረጃ ትእዛዛቱን መጠበቃችን ነው። በክርስቶስ ላይ ስላለን እምነት ከሁሉ የተሻለው ማረጋገጫ በራስ አለመተማመንና በእግዚአብሔር ላይ መታመን ነው። በክርስቶስ ለመኖራችን ብቸኛው አስተማማኝ ማረጋገጫ የእርሱን መልክ ማንጸባረቅ ነው። ይህን እስካደረግን ድረስ በእውነት እንደምንቀደስ እናረጋግጣለን፤ ምክንያቱም እውነት በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ውስጥ ምሳሌ ይሆናልና።"–Ye Shall Receive Power, p. 121.

የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ለመታዘዝ ቢጥሩም ግን ጥቂት ሰላም ወይም ደስታ ብቻ የሚያገኙ ብዙዎች ናቸው። ይህ ተሞክሯቸዉ የተግባራዊ እምነት እጦት ውጤት ነው። በጨዋማ ምድር፣ በደረቅ ምድረ በዳ እንዳለ ይመላለሳሉ። ብዙ ሊጠይቁ እየቻሉ ጥቂት ብቻ ይጠይቃሉ፤ ምንም እንኳ ለእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ወሰን ባይኖረዉም።"–The Acts of the Apostles, p. 563.

በዚህ ሩብ ዓመት ሁላችንም በሰንበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እንድንበለጽግና ሁሉንም አዋቂ ከሆነው ጋር በማገናዘብ እምነታችን እንዲናጠናከር ዘንድ ጸሎታችን ነው።

የጀነራል ኮንፈረንስ ሰንበት ትምህርት ክፍል መምሪያ

## ሰንበት፣ ታህሳስ 29፣ 2015

## የመጀመሪያ ሰንበት ሥጦታ በሰሜን ካውካሰስ፣ ሩሲያ ውስጥ በአዲጂያ ውስጥ ላለው የትምህርትና የጤና ማእከል

የሩሲያ ግዛት 17,125,191 ስኩዌር ኪሎ ሜትር (6,612,073 ስኩዌር ማይል) ሲሆን 146,780,000 ህዝብ ብዛት ያለው ሲሆን ከዚህ ውስጥ 111 ሚሊዮን ሩሲያውያን ናቸው። ከቀሪዎቹ 35 ሚሊዮን ውስጥ ከ180 በላይ ብሔር ብሔረሰቦች ተወካዮች ይገኙበታል። ዋናው ሃይማኖት ኦርቶዶክስ ነው (42%) ቀጣዩ እስልምና (30%) ነው። ሌሎች ሃይማኖቶች ካቶሊካዊነት (3%)፣ የድሮ አማኞች (የምስራቅ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ቅርንጫፍ) እና ፕሮቴስታንት (2%)፣ ቡዲዝም፣ የአይሁድ እምነት እና የግሪክ ካቶሊካዊነት (1%) ያካትታሉ።

ከ1925 ዓ.ም ጀምሮ የተሃድሶው መልእክት በጣም አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ እዚህ ታውጇል። ብዙ ወንድሞች በእግዚአብሔር ቃል ምክንያት ታስረዋል። አንዳንዶች ለእውነት ሲሉ ሕይወታቸውን ከፍለዋል። በ1990ዎቹ ቤተ ክርስቲያናችን በነፃነት የመስበክ እድል ነበራት እናም ይህን አጋጣሚ በንቃት ተጠቅመዋል። በጁን 2018 የሩሲያ ህብረት ተደራጅቷል። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ በግልጽ የመስበክ እድላችን በጣም ውስን ስለነበር የካምፕ ስብሰባዎችን ለማካሄድና ለጤና ሚስዮናዊነት ሥራ የምንጠቀምበት ቦታ በተፈጥሮ ውስጥ እየፈለግን ነበር። በአስደናቂው የተራራማ መልክዓ ምድሮች እይታ በካውካሰስ ተራራማ ሥፍራ ላይ 5 ሄክታር የሚሆን ቦታ እንድንገዛ ጌታ ፈቅዶልናል። በተራራማው ክልል ውስጥ ውሃ ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ስለሆነ የመሬቱ ዋጋ ዝቅተኛ ነበር፡፡ ነገር ግን ጌታ ይህንን አክብሶ በእቅዱ ላይ ለመጠጥ ብቻ ሳይሆን ለኩሬም ጭምር የሚሆን የውሃ ምንጭ እንድናገኝ ረድቶናል። ለዚህ ታላቅ በረከቱ እናመሰግነዋለን! በ2019 ክረምት፣ በዚህ ምድር ላይ ምንም እንኳን መገንባት የቻልነዉ ለበጋ ስብሰባዎች ብቻ የሚያገለግሉ መጠለያዎችን፣ የመመገቢያ አዳራሽና ትንሽ ባለ ሁለት ክፍል ቤት ብቻ ቢሆንም የመጀመሪያውን የካምፕ ስብሰባ አደረግን። አንድ ዶክተር እዚያ የጤንነት ሴሚናር እንዲያካሂድ ተጋበዘ። በትንቢት መንፈስ ብርሃን መሰረትና ሁኔታዎቻችንን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ለዚህ አላማ ተስማሚ የሆነ ቦታ ቢገነባ ለህክምና ሚስዮናዊ ስራ ትልቅ አቅም እናያለን።

በእግዚአብሔር ምህረትና ከመላው አለም ባሉ ወንድሞች እርዳታ በአካባቢያችን ያሉ ወንድሞቻችን በራሳቸው መክፈል የማይችሉትን ይህን ፕሮጀክት እንድናሳካ ጌታ እንደሚረዳን እናምናለን። ይህንን ፕሮጀክት በጸሎትና በገንዘብ መደገፍ የምትፈልጉ ሁሉ፤ ጌታ ይባርካችሁ።

ወንድሞችና እህቶች ከሩሲያ ዩኒየን

# የእግዚአብሔር ቃል ዛሬ ለሰው ልጆች

*የመታሰቢያ ጥቅስ፦"እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። በሰው የሚታመን ሥጋ ለባሹንም ክንዱ የሚያደርግ ልቡም ከእግዚአብሔር የሚመለስ ሰው ርጉም ነው።"* (ኤር.17፥5)።

*"እግዚአብሔር በምሕረቱና በታማኙነቱ ብዙ ጊዜ የምንተማመንባቸውን ሰዎች እንዲያሳጡን (እንድከዱን) ይፈቅድላቸዋል፣ ይህም በሰው መታመን ሥጋ ለባሹን ክንዳችን የማድረግን ሞኝነት እንድንማር ነው።"*–The Ministry of Healing, p. 486.

*ለንባብ የተመረጠዉ፡* Counsels to Parexs, Teachers and Students, pp. 460—463; Fundamentals of Christian Education, pp. 129—137.

**እሁድ ታህሳስ 23**

**1. መጽሐፍ ቅዱስ የተሰጠው እንዴት ነው?**

**ሀ. ቅዱሳት መጻሕፍት የተሰጡት በምን መንገድ ነው? (ልዩ ሁኔታዎችን ያቅርቡ።) 2ኛ ጢሞቴዎስ 3:16፤ 2ኛ ጴጥሮስ 1:21፤ ኦሪት ዘኍልቍ 12፡6።**

*በመንፈስ የተነሳሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ቃሎች አይደሉም፣ ነገር ግን በመንፈስ መሪነት የተነሳሱት የጻፉት ሰዎች ናቸው። በመንፈስ መነሳሳት የሚሠራው በሰውየው ቃላት ወይም አገላለጾች ላይ ሳይሆን በራሱ ሰውየዉ ላይ ነው፣ እርሱም በመንፈስ ቅዱስ ተጽዕኖ ውስጥ ሆኖ በሃሳቦች ይሞላል። ነገር ግን ቃላቶቹና የሀሳቦች አገላለጽ የግለሰብን አእምሮ አሻራ ይቀበላሉ። አዕምሮዉ ከመለኮታዊ አእምሮ ጋር ይዋሄዳል። መለኮታዊ አእምሮና ፈቃድ ከሰው አእምሮና ፈቃድ ጋር ይጣመራሉ፤ ስለዚህ የሰው አነጋገር የእግዚአብሔር ቃል ነው።"*–Selected Messages, bk. 1, p. 21.

**ለ. ከአምላክ መመሪያ ስንፈልግ ስለ ሕልምና ራእይ ምን ማስተዋል አለብን? ዘዳግም 13:1-5፤ ኤርምያስ 29:8**

**ሐ. ለህልሞች አንዳንድ ሌሎች ምክንያቶች ምንድናቸው? መክብብ 5:3፣ 7**

**መ. ነቢያትን እንዴት እንፈትናቸው? 1ኛ ቆሮንቶስ 14:32፤ ኢሳይያስ 8:19፣ 20**

## 2. ቅዱሳት መጻሕፍት የማይሳሳቱ ናቸውን?

### ሀ. የእግዚአብሄርን ቃል ንጽሕና እስከምን ድረስ ማመን እንችላለን? መዝሙረ ዳዊት 12:6፣ 7

እጅግ ውድ በሆነ እውነት የተሞላ መጽሐፍ ቅዱስ አለን። በውስጡም የእውቀት አልፋና ኦሜጋን ይዟል።"–Gospel Workers, p. 309

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የማይሳሳት የእግዚአብሔር ምክር አለን። ትምህርቶቹ፣ በተግባር ከተፈጸሙ፣ ለማንኛውም የሥራ (ሥልጣን) ቦታ ተስማሚ ናቸዉ። በየቀኑ ለነፍስ የሚናገር የእግዚአብሔር ድምፅ ናቸዉ። ወጣቶቹ የእግዚአብሔርን ቃል በታላቅ ጥንቃቄ ማጥናትና ስሜቱን በልባቸው ማከማቸት አለባቸው፣ ይህም ትእዛዛቱ ሁሉንም ባሕርያቸዉን እንዲገዙ ነው።"–Testimonies for the Church, vol. 4, p. 441.

እግዚአብሔር በቃሉ በኩል ለደህንነት አስፈላጊውን እውቀት ሁሉ ለሰዎች ሰጥቷል። ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ባለሙሉ ሥልጣን፣ የማይሳሳቱ የፈቃዱ መገለጫዎች መሆናቸዉን መቀበል አለባቸው። እነሱም የባህሪ መመዘኛዎች፣ አስተምህሮዎችን የሚገልጡና የልምድ ፈተናዎች ናቸው።"–The Faith I Live By, p. 13.

[ወጣቶች] የማይሳሳት አማካሪና መሪ ያስፈልጋቸዋል። ይህንንም ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ያገኙታል። የዚህ ቃል ትጉ ተማሪዎች ካልሆኑ በስተቀር በአሁኑም ሆነ በወደፊቱ ሕይወታቸዉ የራሳቸዉንም ሆነ የሌሎችን ደስታ ሊያበላሹ የሚችሉ ከባድ ስህተቶችን ይፈጽማሉ።"–መልእክት ለወጣቶች፣ ገጽ. 328

### ለ. በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙት መሠረታዊ ሥርዓቶች ምን ያህል ዘላቂ ናቸው? ማቴዎስ 24:35፤ መዝሙረ ዳዊት 119:160፤ ኢሳይያስ 40:8

[ክርስቶስ] የእግዚአብሔርን ቃል ሁሉም ሰዉ ሊረዳ በሚችልበት መንገድ አስተምሯል። ቅዱሳን ጽሑፎችን በማያሻማ መንገድ ጠቁሟል፤ እኛም እንዲሁ ማድረግ አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ማለቂያ የሌለው አምላክ ቃል፣ የክርክር ሁሉ መቋጫና የእምነት ሁሉ መሠረት ሆኖ መቅረብ አለበት።"–Christ's Object Lessons, pp. 39, 40

ሙሉ በሙሉ ከተቀበሉና እንደ አምላክ ድምፅ ከተማሩ መጽሐፍ ቅዱስ ለሰበአዊ ቤተሰብ ወደ ዘላለማዊ ደስታ ማደሪያ እንዴት መድረስ እንደሚችሉና የገነትን ውድ ሀብት እንዴት መጠበቅ እንደሚችሉ ይነግራቸዋል።"–Fundamentals of Christian Education, p. 444

በትምህርት ቤቶቻችን የሚሰጠው ትምህርት የበለጠ ከፍ ያለ የእግዚአብሔርን ቃል እውቀት የሚሰጥና ነፍስን ከእግዚአብሔር ጋር ወደ ወሳኝ ግንኙነት የሚያመጣ፣ እግዚአብሔርን በአእምሮ ዓይን ፊት የሚጠብቅና የነፍስን መልካም ስሜትን ሁሉ የሚያነቃቃ ባህርይ ያለዉ መሆን የለበትምን? ይህ እስከ ዘላለማዊነት የሚዘልቅ የትምህርት ዓይነት ነው።"–General Conference Daily Bulletin, March 6, 1899

## 3. በመለኮታዊ አነሳሽነት የተጻፉ ጽሑፎችን መቀበል

### ሀ. እግዚአብሔር በነቢያቱ አፍ ሲናገር ምን ማስተዋል አለብን? ኤርምያስ 1:4-9፤ 1ኛ ተሰሎንቄ 2፡13

ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ አእምሯቸውን ለትምህርት እንዲከፍቱና ለማመን ዝግጁ እንዲሆኑ አስተምሯቸዋል። በእምነት ዓይንና ጆሮ ስላዩና ስለሰሙ ባረካቸው።. . .

እዉነተኛ የእግዚአብሔር ቃል ተማሪ መጽሐፍ ቅዱስን የእግዚአብሔር ድምፅ ለእርሱ እንደሚናገር አድርጎ የሚቀበል ሰዉ ብቻ ነው። በቃሉ ይንቀጠቀጣል፤ ለእርሱ ሕያው እውነት ነውና።"–Christ's Object Lessons, p. 59

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸሐፊው እነደሆነ ይጠቁማል፤ ቢሆንም በሰው እጅ ተጽፎአል፤ እና በተለያዩ የመጻሕፍቱ አጻጻፍ ስልት የበርካታ ጸሃፊዎችን ባህሪያት ይዟል። የተገለጹት እውነቶች በሙሉ "በእግዚአብሔር መንፈስ የተሰጡ ናቸው" (2ኛ ጢሞቴዎስ 3:16)፤ ግን በሰዎች ቃል ተገልጸዋል። ወሰን የሌለው አምላክ በቅዱስ መንፈሱ በአገልጋዮቹ አእምሮና ልብ ውስጥ ብርሃኑን አፍሷል። ህልሞችንና ራእዮችን፣ ምልክቶችንና ምሳሌዎችን ሰጥቷል፤ እነዚያም እውነት የተገለጠላቸው ሀሳቡን በሰው ቋንቋ ጻፉት።"–Selected Messages, bk. 1, p. 25

### ለ. የመለኮትን ሁሉን አዋቂና ዘላለማዊ ማንነት እንድንረዳ ይረዳን ዘንድ እግዚአብሔር በነቢያቱ በኩል ብዙ ጊዜ የሚገልጠው ምንድን ነው? አሞጽ 3:7፤ ኢሳይያስ 46:9፣ 10

የምድር ሁሉ አምላክ በመረጣቸው ብርሃን አብሳሪዎች አማካኝነት ምስጢርን እንደሚገልጥ ታሪክና ትንቢቶች ይመሰክራሉ። ተጠራጣሪዉ ዓለም፣ ስለከፍተኛ ትምህርት ሲናገርና ሲፅፍ፣ ለራሳቸዉ ያልተረዱትን ነገሮች በተግባር ላይ እናዉላለን ብለዉ ይቀባጥራሉ። ስለ አምላክና እርሱ ስለ ላከው ስለ የሱስ ክርስቶስ ፍጹም በሆነ እውቀት ከመረዳት የበለጠ እውነተኛ ከፍተኛ ትምህርት የትም የለም። እውነተኛው የሰው ልጅ ሳይንስ ሁሉ ከሳይንሱ አምላክ (ከእግዚአብሔር) እንደሆነና አምላክ እርሱ በሁሉም ላይ ንጉሥ መሆኑን ለዓለም ያሳየ መሆኑን የተረዱ ጥቂቶች ናቸው።"–Bible Training School, December 1, 1912.

በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ፣ የሀገሮች እድገት፣ የግዛቶች መነሳትና ውድቀት፣ በሰው ፍላጎትና ችሎታ ላይ የተመሰረተ ይመስላል፤ የክስተቶች አወጣጥ በከፍተኛ ደረጃ፣ በኃይሉ፣ በፍላጎት ወይም በእነርሱ ምክንያት የሚወሰን ይመስላል። ነገር ግን በእግዚአብሔር ቃል ላይ መጋረጃው ወደ ጎን ተዘርግቷል፣ ቢሆንም እነሆ ከላይ፣ ከኋላ፣ እና በሁሉም የሰው ልጅ ፍላጎትና ሀይል እንዲሁም በሰዉ ልጅ ፍላጎት ሽሚያ መካከል፣ የመሃሪው አምላክ ወኪሎች፣ በጸጥታና በትዕግስት የእርሱን ፈቃድ ምክሮች ሲፈጽሙ እናያለን።"–Prophets and Kings, pp. 499, 500

## 4. በእኛ በኩል ምን ያስፈልጋል?

### ሀ. መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና ምን ዓይነት ዝንባሌ ሊኖረን ይገባል? ኢሳይያስ 66:1፣ 2፤ ዮሐንስ 7:17፤ የሐዋርያት ሥራ 17:10፣ 11

*ነፍስ ለክርስቶስ በተገዛች ጊዜ አዲስ ኃይል አዲሱን ልብ ይቆጣጠራል። ይህ ሲሆን ሰዉ ሊፈጥረዉ የማይችል ለዉጥ ይከሰታል። ይህ ለዉጥ ከሰበአዊ ተፈጥሮ ጋር መለኮታዊ ባሕርይን የሚያዋሕድ መለኮታዊ ሥራ ነዉ። ለክርስቶስ ያደረች ነፍስ ያለክርስቶስ ሌላ ኃይል የማይታይባት በአመጸኛ ዓለም ዉስጥ የምትገኝ የክርስቶስ የግል ምሽግ ትሆናለች። በሰማይ ተወካዮች እንደዚህ ሆና የተጠበቀች ነፍስ ለሰይጣን አደጋ አትበገርም። እኛም ራሳችንን ለክርስቶስ ካላስገዛን የሰይጣን ተገዢ እንሆናለን።"–የዘመናት ምኞት፣ ገጽ*. 325.

*መቃወም፣ መጠየቅ፣ መተቸት፣ መሳለቅ ብዙዎች የተማሩት ትምህርትና ያፈሩት ፍሬ ነው። ማስረጃ ለመቀበል ፍቃደኛ አይደሉም። ተፈጥሯዊ ልብ ከብርሃን፣ ከእውነትና ከእውቀት ጋር ጦርነት ውስጥ ነው። የሱስ ክርስቶስ በተዝናኑበት በእያንዳንዱ የመኝታ ክፍል ውስጥ ነበር። ከእነዚህ ክፍሎች ውስጥ ምን ያህል ጸሎቶች ወደ ሰማይ ወጥተዋል?"*–The Ellen G. White 1888 Materials, p. 140.

*በየቀኑ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እስካላደረግን ድረስ ትምህርታችን ትክክልና ከገለባና ከስሕተት የጸዳ ለመሆኑ ምንም ማረጋገጫ የለም። ፈቃዱን ካደረግን ትምህርቱን እናውቃለን። እውነትን በተቀደሰ ውበት እናያለን። በአክብሮት እና እግዚአብሔርን በመፍራት እንቀበላለን፣ ከዚያም እውነት መሆኑን የምናውቀውን ለሌሎች እናቀርባለን። በዚህ የተከበረ ሥራ ውስጥ የበላይነት ስሜት ወይም ራስን ከፍ ከፍ ማድረግ መኖር የለበትም።"*–Ibid., p. 46.

### ለ. ከሌሎቹ የበለጠ ጠቃሚ የሆነው የትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው? ሮሜ 15:4፤ ሉቃስ 24:27፤ ኢሳይያስ 28:10

*እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በእግዚአብሔር መንፈስ የተሰጠና ጠቃሚም ነው። ብሉይ ኪዳን ከአዲሱ ያላነሰ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ብሉይ ኪዳንን ስናጠና ግድ የለሽ የሆነዉ አንባቢ ምድረ በዳውን ብቻ ሲመለከት እኛ የሕያዉ የሆኑ ምንጮች ሲፈልቁ እናገኛለን።*

*ብሉይ ኪዳን አዲስ ኪዳን ላይ፣ እንዲሁም አዲስ ኪዳን በብሉይ ላይ ብርሃንን ያበራል። እያንዳንዳቸው በክርስቶስ የእግዚአብሔር ክብር መገለጥ ናቸው።"*–Counsels to Parents, Teachers, and Students, p. 462.

## ሐሙስ                                                                      ታህሳስ 27

## 5. ማንበብ እና ማጥናት ብቻ በቂ አይደለም

### ሀ. ቅዱስ ጽሑፍን ስናጠና በተማርናቸው ነገሮች ምን እናድርግ? ምሳሌ 2:1-5፤መዝሙር 119:11፣16

*መንፈስ ቅዱስ ወጣቶችን ሊመራቸዉና የእግዚአብሔርን ቃል ውድ ሀብትና ውበት ሊገልጥላቸው ይወዳል። በታላቁ መምህር የተነገሩት ተስፋዎች ስሜትን ይማርካሉ፤ እንዲሁም ነፍስን መለኮታዊ በሆነ መንፈሳዊ ኃይል ይሞላሉ። በፍሬያማ አእምሮ ውስጥ ከመለኮታዊ ነገሮች ጋር መተዋወቅ ፈተናዎች ወደ እኛ ሲመጡ እንቅፋት ይሆንባቸዋል።*

*የእውነት ቃላቶች ጥቅማቸዉ ያይላል፣ እና አስበነዉ የማናውቀውን ያህል ስፋትና ሙሉ ትርጉም እናገኛለን። የቃሉ ውበትና ብልጽግና በአእምሮና በባህሪ ላይ ለውጥ ይመጣል። የሰማያዊ ፍቅር ብርሃን እንደ እንደ አንቀሳቃሽ ኃይል በልብ ላይ ይወርዳል።"*–Christ's Object Lessons, p. 132

### ለ. እነዚህን ነገሮች በልባችን ከወሰድን ከምን ጋር እንነጻጸራለን? ሉቃስ 6፡ 46-49

*"በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ባለው ውድ እውነት የተከማቸ ልብ በሰይጣን ፈተና፣ ርኩስ በሆኑ አስተሳሰቦችና ርኩስ ድርጊቶች እንዳያገኙት የሚያደርግ ብርቱ ምሽግ አለዉ።"*–My Life Today, p. 28.

### ሐ. ጌታ እንዲያደርግልን የምንጠይቀው ምንድን ነው - እና ለምን? መዝሙረ ዳዊት 119:133

*መለኮታዊ ጥበብ በእግዚአብሔር የሚታመኑትን ሰዎች እርምጃ ያዘጋጃል። መለኮታዊ ፍቅር ይከብባቸዋል፣ እናም የአጽናኙ የመንፈስ ቅዱስ መገኘትን ይገነዘባሉ።"*–Our High Calling, p. 324.

## ዓርብ                                                                      ታህሳስ 28

## የግል ግምገማ ጥያቄዎች

1. *መለኮታዊ መነሳሳት ለሰው ልጆች የሚሰጠው እንዴት ነው?*
2. *በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ምን ያህል መተማመን እንችላለን? ለምንስ?*
3. *ትንቢታዊ ጽሑፎችን የመስጠት ዓላማ ምንድን ነው? በመንፈስ አነሳሽነት የተጻፉት ሁሉም ጽሑፎችስ ምን ሥልጣን ይዘው መጥተዋል?*
4. *አመለካከት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን የሚነካው እንዴት ነው?*
5. *ሕይወታችንን በአስተማማኝ መሠረት ላይ የምንገነባው እንዴት ነው?*

# ኃያሉ የእግዚአብሔር ቃል

*የመታሰቢያ ጥቅስ፡- አቤቱ፥ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ፥ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ።" (መዝሙረ ዳዊት 51፡10)*

*አብዛኛውን ጊዜ ፈተናዎች መቋቋም የማይቻሉ ይመስላሉ፤ ምክንያቱም ፀሎትንና የመጽሐፍ ቅዱስን ጥናት ቸል በማለቱ ተፈታኙ ሰው የእግዚአብሔርን ተስፋዎች ወዲያውኑ አስታውሶ በመጽሐፍ ቅዱስ [ጥቅስ] መሳሪያዎች ሰይጣንን መፋለም ስለማይችል ነው።"*–The Great Controversy, p. 600.

*ለንባብ የተመረጠዉ፡* Fundamentals of Christian Education, pp. 123—128

**እሁድ ታህሳስ 30**

## 1. የመስቀሉ ወታደሮች

### ሀ. በምድር ላይ በምንኖርበት ጊዜ ሁልጊዜ ምን ማወቅ አለብን? 1ኛ ጴጥሮስ 5:8 ታዲያ ጳውሎስ የአንድን ክርስቲያን ሕይወት እንዴት ያወዳድራል? 2ኛ ጢሞቴዎስ 2:3

*ባጾነቷ ከሚሰማትና ሙሉ በሙሉ በተሰቀለውና በተነሳው አዳኝ ደም ትሩፋቶች ላይ ከምትታመን ነፍስ በላይ ማንም፤ ምንም ነገር ማድረግ የማይችልና ረዳት አልባ ሊሆን አይችልም። የክርስትና ሕይወት የጦርነት፣ የማያቋርጥ የግጭት ሕይወት ነው። ጦርነትና ሰልፍ ነው። ነገር ግን እያንዳንዱ ለክርስቶስ የመታዘዝ ተግባር፣ ለእርሱ ሲል ራስን የመካድ ተግባር፣ እያንዳንዱ የምንታገሰዉ ፈተና፣ እያንዳንዱ በፈተና ላይ የተገኘ ድል፣ የመጨረሻው የድል ክብርን ለማግኘት የሚደረግ ጉዞ አካል ነው።*–That I May Know Him, p. 253.

### ለ. በመጨረሻ አሸናፊዎች የምንሆነው እንዴት ስናደርግ ብቻ ነው? ኤፌሶን 6፡11-17

*የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ የሚለብሱ እና ለማሰላሰልና ለጸሎት እንዲሁም ቅዱሳት መጻሕፍትን በማጥናት በየቀኑ የተወሰነ ጊዜ የሚያጠፉ ከሰማይ ጋር ይገናኛሉ እናም በዙሪያቸው ባሉት ሰዎች ላይ የሚያድንና የሚቀይር ተጽእኖ ይኖራቸዋል። ታላቅ ሀሳቦች፣ የተከበሩ ምኞቶች፣ ስለ እውነትና ለእግዚአብሔር ስላለዉ ግዴታ ግልጽ ግንዛቤዎች ይኖሯቸዋል። ... እነዚህም ወሰን አልባ ወደሆነው ፊት ለመቅረብ የተቀደሰ ድፍረት ይኖራቸዋል። የሰማይ ብርሃንና ክብር ለእነሱ እንደሆነ ይሰማቸዋል፣ እናም በዚህ ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ቅርርብ የነጠሩ፣ ከፍ ያሉና የተከበሩ ይሆናሉ። ይህም የእውነተኛ ክርስቲያኖች ልዩ ጥቅም ነው።"*– Testimonies for the Church, vol. 5, pp. 112, 113

2. **ኃይል በቃሉ ውስጥ**

**ሀ. ቃሉ በእውነት ወደ ነፍስ ሲገባ ምን ያህል ዘልቆ ይገባል? ዕብራውያን 4፡12**

በልብ ውስጥ የሚታሰቡ የመነሳሳት ቃላት ከሕይወት ውሃ ወንዝ እንደሚፈስሱ ጅረቶች ይሆናሉ። ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመረዳት የደቀ መዛሙርቱ አእምሮ እንዲከፈት መድኃኒታችን ጸለየ። በጸሎት ልብ መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና፣ መንፈስ ቅዱስ የምናነበውን ቃል ትርጉም ሊከፍትልን ቅርብ ነው።"– Our High Calling, p. 205.

እውነት በተግባር ወደ ሕይወታችን መምጣት አለበት፣ እና ቃሉ፣ እንደ የተሳለ፣ ሁለት አፍ እንዳለው ሰይፍ፣ በባህሪያችን ውስጥ ያለውን ትርፍ ቆርጦ ማውጣት አለበት።

ቃሉ ትዕቢተኞችን ትሑታን፣ ጠማማዎችን የዋሆችና የሚጸጸቱ፣ የማይታዘዙትን ታዛዥ ያደርጋቸዋል። በሰው ላይ የሚፈጠሩት የኃጢአተኛ ልማዶች ከዕለት ተዕለት ተግባር ጋር የተሳሰሩ ናቸው። ቃሉ ግን የሥጋን ምኞት ይቆርጣል። የአዕምሮ ሃሳቦችንና ዝንባሌዎችን የሚለይ ነው። ጅማትንና ቅልጥምንም ይከፋፈላል፣ የሥጋን ምኞት ያስወግዳል፣ ሰዎችንም ለጌታቸው መከራ ለመቀበል ፈቃደኛ እንዲሆኑ ያደርጋል።The SDA Bible Commentary [E. G. White Com-ments], vol. 7, p. 928.

**ለ. በመጀመሪያ ቃሉ ሰማይንና ምድርን በምን ያህል ፍጥነት ፈጠረ? ዘፍጥረት 1:1፤ መዝሙረ ዳዊት 33:6፣ 9**

**ሐ. እግዚአብሔር ቃሉን ተጠቅሞ ዓለማትን የፈጠረው ከየትኛው ቁሳቁስ ነው? ዕብራውያን 11፡3 ዓለማትን ከፈጠረ በኋላ እግዚአብሔር ፍጥረታት ራሳቸዉን እንዲጠብቅ ተዋቸዉን? ዕብራውያን 1፡3**

ዓለምን ወደ ሕልውና ያመጣው ያው ፈጠሪ ሃይል አሁንም አጽናፈ ሰማይን በመደገፍና የተፈጥሮን ስራዎች ለማስቀጠል ይተጋል። የእግዚአብሔር እጅ ፕላኔቶችን በሰማያት ላይ በሥርዓት ሲጓዙ ይመራቸዋል። ምድር ከአመት አመት በፀሀይ ዙሪያ እንቅስቃሴዋን የምትቀጥልበትና ችሮታዋን የምታፈራው በተፈጥሮ ሃይል አይደለም። የእግዚአብሔር ቃል ንጥረ ነገሮችን ይቆጣጠራል። ሰማዩን በደመናት ይሸፍናል ለምድርም ዝናብን ያዘጋጃል፤ ሣርን በተራሮች ላይ ያበቅላል። መዝሙረ ዳዊት 147:8 ዕፅዋት የሚበቅሉት፣ ቅጠሎቹ የሚወጡትና አበቦቹ የሚያብቡት በእሱ ኃይል ነው።"–Counsels to Parents, Teachers, and Students, pp. 185, 186.

## 3. ኃጢአትን አምኖ መቀበል (እዉቅና መስጠት)

**ሀ. ዳዊት በእግዚአብሔርና በቤርሳቤህ ላይ ኃጢአት ከሠራ በኋላ ምን ፈልጎ ነበር? መዝሙረ ዳዊት 51:1-4**

**ለ. ዳዊት የተናገራቸውን የንስሐ መግለጫዎች በመለኮታዊ መዝገብ ውስጥ ተጠብቀው ቆይተዋል፤ እነዚህም በጣም ያሳሰበው ይኸውም የሚያጋጥመውን መዘዝ ወይም ከአምላክ ጋር ያለውን ዝምድና ማደስ? መዝሙረ ዳዊት 51:5-10**

*የእግዚአብሔርን መከፋት የሚሳይ ዉጫዊ ማስረጃ ባለመኖሩ፤ ዳዊት ከዉድቀቱ በኋላ ለአንድ ዓመት ያህል በተሸለ የደህንነት ስሜት የኖረ መሰለ። ነገር ግን መለኮታዊ ፍርድ በላዩ እያንዣበበ ነበር። ንስሃ የማይቀለብሰዉ፣ ምድራዊ ሕይወቱን አጨልሞ ሐፍረትና መሸማቀቅ የሚያስከትል ፈጣንና እርግጠኛ የፍርድና የበቀል ቀን እየተቃረበ ነበር። የዳዊትን ምሳሌነት እየጠቀሱ ኃጢአታቸዉን ለማቃለል የሚሞክሩ ሁሉ የመተላለፍን ጎዳና ከባድነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች መማር ይችላሉ። ምንም እንኳን እንደ ዳዊት ከክፉት መንገዳቸዉ መመለስ ቢኖርባቸዉም፤ የኃጢአትን ዉጤት መሸከም ከባድና መራር ነዉ።"–አበዉና ነቢያት፣ ገጽ* 400

*የዳዊት ንስሐ ጥልቅና ከልብ የተደረገ ነበር። ወንጀሉን ለማቃለል ምንም ጥረት አላደረገም። ከሚያስፈራዉ ፍርድ ለማምለጥ ምኞት ያልነበረዉ ዳዊት የተላለፈዉን አምላካዊ ሕግ ስፋትና ጥልቀት ተመልክቷል። የነፍሱን መቆሸሽ አስተዉሏል፣ ኃጢአቱንም ተጸይፏል። የጸለየዉ ምህረት ለማግኘት ብቻ ሳይሆን የልብ ንጽህናን ለማግኘት ጭምር ነበር። በትግሉ ተስፋ ያልቆረጠዉ ዳዊት፤ እግዚአብሔር ለተጸጸቱ ኃጢአተኞች በገባዉ ቃል መሠረት ይቅር መባሉንና በጌታ ፊት ተቀባይነት ማግኘቱን አረጋግጧል።"–ኢቢድ፣ ገጽ*. 403

*ዳዊት በንስሐና በጸጸት ልቡን በእግዚአብሔር ፊት ስላዋረደና እግዚአብሔር ይቅር ለማለት የገባው ቃል እንደሚፈጸም ስላመነ በደሉ ይቅርታ ተደረገለት። ኃጢአቱን ተናዞ፣ ተጸጸተ፣ እናም ተመለሰ። ይቅርታ እንደተደረገለት ሲያረጋግጥ በደስታ፣ "መተላለፉ የቀረችለት ኃጢአቱም የተከደነችለት ምስጉን ነው። እግዚአብሔር በደልን የማይቈጥርበት በመንፈሱም ሽንገላ የሌለበት ሰው ምስጉን ነው። መዝሙር* 32:1፣ 2 *በረከቱ የሚመጣው በይቅርታ ነው፤ ይቅርታ የሚመጣው የተናዘዝነው እና የተፀፀትንበት ኃጢያት በታላቁ ኃጢያት ተሸካሚ ላይ እንደሚሆነ ስናምን ነው። ስለዚህ በረከታችን ሁሉ ከክርስቶስ ነው። የእርሱ ሞት ለኃጢአታችን ማስተሰረያ መስዋዕት ነው። እርሱ የእግዚአብሔርን ምሕረትና ሞገስ ያገኘንበት ታላቁ መካከለኛ ነው።"*– Our High Calling, p. 83.

## 4. የሰውን ልብ የሚለወጥ ኃይል

### ሀ. የረከሰውን፣ የኃጢአተኛ ሕይወትን ወደ ንጽህና የመለወጥ ዕድል ምን ተስፋ ይሰጣል? ኢዮብ 14:4፤ ኤርምያስ 13:23፤ ሕዝቅኤል 36:26፣ 27

*እርግጥ ነዉ ያለ ክርስቶስ ለዋጭ ኃይል ዉጫዊ የባሕርይ መልካምነት ሊኖር እንደሚችል አይካድም። በሌሎች ለመታየትና ለመወደስ ያለን ፍላጎት የተስተካከለ የምንለዉን ሕይወት እንድንቀዳጅ ሊያተጋን ይችላል። ለራሳችን ያለን አክብሮት የክፉት መገለጫ እንዳንሆን ሊያግዘን ይችል ይሆናል። ምናልባት ራስ ወዳድ ልብ ለሌሎች መልካም ነገርን ሊያደርግ ይችል ይሆናል። ታዲያ ከማን ወገን እንደሆንን የሚወስነዉ በምን መንገድ ነዉ?”–ወደ ክርስቶስ የሚያመራ መንገድ፣ ገጽ*. 54.

*እግዚአብሔር በዓለም ላይ ካለው ክፉ ነገር ጋር ለመዋጋት የተትረፈረፈ ዘዴ አዘጋጅቷል። መጽሐፍ ቅዱስም ለትግሉ የምንታጠቅበት የጦር ዕቃ ቤት ነው።”*–The Acts of the Apostles, p. 502.

### ለ. የተበላሸ የሰው ልብ በጽድቅ ወደሚደሰት ልብ የሚለወጥበት ብቸኛው መንገድ ምንድን ነው? ዮሐንስ 3፡3

*ቀድሞ ይጠሏቸዉ የነበሩ ነገሮችን አሁን ይወዳሉ፤ ቀድሞ ይወዷቸዉ የነበሩ ነገሮችን አሁን ይጠላሉ። በራሳቸዉ ብቻ የሚታመኑ ልበ ደንዳኖች የነበሩ ትሁትና የተሰበረ ልብ ባለቤት ይሆናሉ። ግብዝነትና ልታይ ባይነት በእዉነተኛነትና በጭምትነት ይተካል። የመጠጥ ሱሰኛዉ ከነበረበት የመጠጥ ሱስ ይላቀቃል፣ አባካኞች ከማባከን ይታቀባሉ።”–ወደ ክርስቶስ የሚያመራ መንገድ፣ ገጽ*. 54.

### ሐ. የዚያ ለውጥ ማስረጃዎች ምንድን ናቸው? ገላትያ 5:22፣ 23

*ከደምና ከሥጋ ፈቃድ የተወለደ አሮጌው ተፈጥሮ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርስ አይችልም። አሮጌው መንገዶች፣ የዘር ውርስ ዝንባሌዎች፣ የቀድሞ ልማዶች መተው (መቅረት) አለባቸው፤ ጸጋ አይወረስምና። አዲስ ልደት አዲስ ተነሳሽነት፣ አዲስ ጣዕምና አዲስ ዝንባሌዎች መኖርን ያጠቃልላል። በመንፈስ ቅዱስ ለአዲስ ሕይወት የተወለዱት፣ የመለኮታዊ ተፈጥሮ ተካፋዮች ሆነዋል፣ እና በሁሉም ልማዶቻቸው እና ልምምዳቸው ከክርስቶስ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማረጋገጫ ይሰጣሉ። ክርስቲያን ነን የሚሉ ሰዎች በተፈጥሮአቸው የባሕርይና የአመለካከት ድክመቶቻቸውን ከያዙ አቋማቸው ከዓለማዊው በምን ይለያል? እውነትን እንደሚቀድስና እንደሚያጠራ አምነዉ አላደነቁም። ዳግመኛ አልተወለዱም።”*–The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 6, p. 1101.

## 5. በእግዚአብሔር ቃል የተወለደ

### ሀ. በተንኮለኛና ክፉ ሰው ልብ ውስጥ እንዲህ ያለ ሥር ነቀል ለውጥ ለማድረግ ኃይል ያለው ምንድነዉ? ሮሜ 1:16፤ ዮሐንስ 1:1፤ 15:3፤ 1ኛ ጴጥሮስ 1፡23

*መጽሐፍ ቅዱስ ከታሪክ ሁሉ የሚበልጥ ድንቅ ነው፣ ምክንያቱም የእግዚአብሔር እንጂ የውስኑ የሰዉ አእምሮ ዉጤት አይደለም። ያለበለዚያ ፈጽሞ ሊታወቅ የማይችለዉን የዘመናት ትዕይንቶችንኛ ታሪክ እያቀረበ በዘመናት ውስጥ ወደ ሁሉም ነገር መጀመሪያ ሊያደርሰን አይችልም ነበር። የወደቀውን ዓለም ለማዳን በሚያደርገው ጥረት የእግዚአብሔርን ክብር ይገልጣል። በቀላል ቋንቋ ሰዎችን ከሰይጣን ሠረገላ ጋር የሚያስረውን ሰንሰለት የሚቆርጥበትን የወንጌል ኃይል ይሰጣል።*–Fundamentals of Christian Education, p. 377

### ለ. ቃሉ በውስጣችን የሚቀሰቅሰው ምንድን ነው? ይህስ ለድል አድራጊ ሕይወት በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው? ሮሜ 10:17፤ 1ኛ ዮሐንስ 5፡4 ለቀሪው ሕይወታችን ያንኑ ዓይነት ድል እንዴት እንጠብቀዋለን? ቆላስይስ 2፡6

*የእዉነት መርሆችን በእምነት ተቀብለን ከሕልዉናችን ጋር ስናዋሕዳቸዉ የሕይወታችን አንቀሳቃሽ ኃይል ይሆናሉ። የእግዚአብሔር ቃል ወደ ልብ ሰርጾ ሲገባ ሀሳብን ያስተካክላል ባሕርይንም ያዳብራል።*

*ያለማቋረጥ በኃይማኖት ዓይን የሱስን በመመለከት ጥንካሬ እናገኛለን። እግዚአብሔር እዉነትን ለተራቡትና ለተጠሙት ልጆቹ እጅግ የተከበረዉን ምስጥሩን ይገልጥላቸዋል። የሱስ የግል አዳኝ መሆኑን ይረዳሉ። ቃሉን እንደተመገቡ መጠን መንፈስና ሕይወት መሆኑን ይገነዘባሉ። ቃሉ ተፈጥሯዊና ምድራዊዩን ባሕርይ ደምስሶ በየሱስ ክርስቶስ አዲስ ሕይወትን ይሰጣል። ቅዱስ መንፈስም ነፍስን ለማጽናናት ይመጣል። የመለወጥ ኃይል ባለዉ ጸጋዉ አማካይነት የእግዚአብሔር ምስል በደቀ መዝሙሩ ላይ ስለሚቀረጽ አማኙ አዲስ ፍጡር ይሆናል። ይህ ሲሆን በጥላቻ ፋንታ ፍቅር ይተካል፣ ልብም የመለኮትን ምሳሌነት ይይዛል።"–የዘመናት ምኞት፣ ገጽ.* 397.

## አርብ ጥር 5

### የግል ግምገማ ጥያቄዎች

1. *ክርስቲያን ከክፉ ጋር የሚያደርገው ጦርነት ምን ያህል አሳሳቢ ነው?*
2. *ቃሉ በዚህ ጦርነት ውስጥ ምን ጠቃሚ ቦታ አለው?*
3. *የኃጢአትን አጥፊ ተፈጥሮ ጥልቀት እንዴት መረዳት ይቻላል?*
4. *የነፍስ ለውጥ እንዴት ይከናወናል?*
5. *ከክርስቶስ ጋር ያለንን ዝምድና ማቆየት የምንችለው እንዴት ነው?*

# እሳታማ እባቦች

የመታሰቢያ ጥቅስ፡- እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ። ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና።" (ማቴ 11፡28-30)።

የእግዚአብሔር ልጅነት ለእኛ ሁሉም ነገር ነው። ነፍሳችንን ከክርስቶስ ጋር፣ በክርስቶስ ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ያቆራኘው የወርቅ ሰንሰለት ነው። ይህ የእኛ ጥናት ይሆናል።"–Selected Messages, bk. 1, p. 244.

ለንባብ የተመረጠዉ፡ የዘመናት ምኞት፣ ገጽ 48፣ 49፣ 114—123።

**እሁድ ጥር 7**

1. **የአብርሃም ዘር**

### ሀ. በመንፈሳዊ ሕይወት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ከባድ አደገኛ አመለካከት ግለጽ። የዮሐንስ ወንጌል 8፡33

### ለ. የኃጢአት ባሪያዎች እንድንሆን የሚያደርገን ምንድን ነው? ዮሐንስ 8:34፣ 39–44

ፈሪሳውያን የአብርሃም ልጆች ነን ባዮች ነበሩ። የሱስ ግን ያ መብት ሊኖራቸዉ የሚችለዉ የአብርሃምን ሥራ ሲሠሩ ብቻ እንደሆነ ነገራቸዉ። እዉነተኛ የአብርሃም ልጆች የሆኑ ሁሉ እርሱ እንዳደረገዉ ለእግዚአብሔር ታዛዥ የሆነ ሕይወት ይኖራሉ እንጂ ከእግዚአብሔረ የተሰጠዉን እዉነት የሚናገርን ሰዉ ሕይወት ለማጥፋት አይሞክሩም። እነዚያ የኦሪት ሕግ ሊቃዉንት በየሱስ ላይ ሲያሴሩ የአብርሃምን ሥራ መሥራታቸዉ አልነበረም። በትዉልድ ብቻ የአብርሃም ዘር መሆን ምንም ፋይዳ የለዉም። እነዚህ ሰዎች የአብርሃም መንፈስ እንዲያድርባቸዉና የእርሱንም ሥራ እንድሠሩ የሚያደርጋቸዉ ከእርሱ ጋር የሚያስተሳስራቸዉ መንፈሳዊ ግንኙነት እስካልኖራቸዉ ድረስ የአብርሃም ልጆች ሊሆኑ አይችሉም።"–የዘመናት ምኞት፣ ገጽ 481

### ሐ. ከዚህ የጨካኝ ጌታ ግፍ እንዴት መታደግ ይቻላል? ዮሐንስ 8:32፣ 36፤ ገላ 3፡29

2. **“ማወቅ” ማለት ምን ማለት ነው?**

## ሀ. ጲላጦስ በፍርድ አዳራሽ ውስጥ ምን በጣም አስፈላጊ ጥያቄ አቀረበ? ዮሐንስ 18፡38 (የመጀመሪያ ክፍል)። የአዳኙን ምላሽ ለማዳመጥ ለአፍታ ጊዜ ቢሰጥ ኖሮ ምን መልስ ይሰጠው ነበር? ዮሐ. 14፡6

ጲላጦስ እውነቱን የማወቅ ፍላጎት ነበረው። ግራ ቢጋባም የሱስ የተናገራቸዉን ቃላት በጉጉት በማዳመጥ እዉነትን ለማወቅና ይህን እዉነት እንዴት ሊያገኘዉ እንደሚችል በነበረዉ ፍላጎት “እዉነት ምንድነዉ” ሲል ጠየቀ። ነገር ግን ለጥያቄዉ መልስ ለመስማት አልተጠባበቀም። ካህናቱ ፈጣን ዉሳኔ እንዲሰጣቸዉ ይጮኹ ስለነበረ ከዉጭ ይሰማ የነበረዉ ሁካታ የወቅቱን ሁኔታ አስታወሰዉ። ስለዚህ አይሁዳዊያዉኑ ወደነበሩበት ወጥቶ “እኔ ምንም ጥፋት አላገኘሁበትም” ሲል በአጽንኦት ተናገረ።”–የዘመናት ምኞት፣ ገጽ. 768.

## ለ. አንድ ሰው እግዚአብሔርን ሳያውቅ ቃሉን የሚያጠና ከሆነ ምን ሊሆን እንደሚችል አስረዳ። ማርቆስ 12:24፤ 2ኛ ጢሞቴዎስ 3:7

ሰዱቃውያን ሰዎች ሁሉ ቅዱሳት መጻሕፍትን አጥብቀው በመጠበቃቸው ራሳቸውን አመሰገኑ። የሱስ ግን ትክክለኛ ትርጉማቸውን እንደማያውቁ አሳይቷል።”–የዘመናት ምኞት፣ ገጽ. 605.

## ሐ. የወደቀው ተፈጥሮአችን ወደማይፈልገው ሰው እንዴት መቅረብ ይቻላል? ዮሐንስ 12:32፤ 8:28፤ ማቴዎስ 11:28-30

ሕግ በሕዝብ ፊት በሚቀርብበት ጊዜ፣ የእውነት መምህር ወደሆነዉ በተስፋ ቃል ቀስተ ደመና ባሸበረቀዉ ዙፋን ላይ ወደ ተቀመጠዉ፣ ወደ ክርስቶስ ጽድቅ ያመልክት። የሕግ ክብር ክርስቶስ ነው፤ እርሱ ሕግን ሊያጎላና ሊያከብር መጣ። ምህረትና እውነት በክርስቶስ አንድ ላይ እንደተገናኙ እና ቅንነትና ሰላምም እርስ በርሳቸው እንደተቃቀፉ ግልጽ አድርጉ። ንስሐህንና ውዳሴህን ለእግዚአብሔር ስታቀርብ፣ ክርስቲያናዊ ባሕርይን ፍጹም አድርገህ ክርስቶስን ለዓለም የምትወክለው ወደ ዙፋኑ ስትመለከት ነዉ። እናንተ በክርስቶስ ስትኖሩ ክርስቶስም በእናንተ ይኖራል፤ አእምሮን ሁሉ የሚያልፍ ሰላም ይኖራችኋል።

በክርስቶስና በሚደንቅ ፍቅሩ ላይ ያለማቋረጥ ማሰላሰል ያስፈልገናል። አእምሮን ወደ የሱስ በመምራት፣ በእርሱ ላይ መጠማጠም አለብን። በእያንዳንዱ ንግግር ውስጥ በመለኮታዊ ባህሪያት ላይ ማትኮር አለብን።”–The Ellen G. White 1888 Ma-terials, p. 730

የመለኮታዊ-ሰበአዊዉን ባህሪይ በጥንቃቄ አጥኑና ያለማቋረጥ ጠይቁ፡- “የሱስ በእኔ ምትክ ቢሆን ምን ያደርግ ነበር?””–The Ministry of Healing, p. 491

## 3. በበረሃ ውስጥ እባቦች

### ሀ. እግዚአብሔር በምድረ በዳ በመርዛማ እባቦች ለተነደፉት ምን መድኃኒት አዘጋጀላቸው? ፈውስ እንዲከሰት ምን አስፈለገ? ዘኍልቍ 21፡ 6–9

በመለኮታዊ ኃይል [የእስራኤል ልጆች] ተጠብቀው ስለነበር በተከታታይ የከበቧቸዉን ስፍር ቁጥር የሌላቸውን አደጋዎች አላስተዋሉም። ምስጋና ቢስና የማያምን መንፈስ የተቆራኛቸዉ እሥራኤላዊያን ሞት ተመኙ። ጌታም የተመኙትን ሞት ፈቀደላቸዉ። በምድረ በዳዉ እጅግ የሚፈሩ ኃይለኛ ተናዳፊ እባቦች ነበሩ። በእነዚህ እባቦች የተነደፈ ሰዉነቱ ያብጥና በቅጽበት ይሞታል። ሕዝቡን ከአደጋ የሚታደገዉ አማላካዊዉ እጅ ከእነርሱ ላይ በተነሳ ጊዜ ከፍተኛ ቁጥር ያለዉ ሕዝብ በተናዳፊዎቹ እባቦች ጥቃት ደረሰበት።. . .

ሙሴ በሕይወት ያለዉን የሚመስል የናስ እባብ እንዲሠራና በሕዝቡ መካከል ለሁሉም በሚታይ ቦታ እንዲሰቅለዉ በመለኮት ታዝዞ ነበር። በእባቡ የተነደፉ ሁሉ ወደ ናሱ እባብ ሲመለከቱ ይድኑ ነበር። በእባብ የተነደፉ ሁሉ የናሱን እባብ ተመለክተዉ ይድኑ ዘንድ ይህ አስደሳች ዜና በመላዉ የእስራኤል ማሕበር ተሰራጨ። በንድፊያ ብዙዎች በማለቃቸዉና የተነደፉት ደግሞ የናሱን አይተዉ ይፈወሱ ዘንድ ሙሴ በእንጨት ላይ ሲሰቅለዉ አንዳንዶች አላመኑም ነበር። እነዚህ ካለማመናቸዉ የተነሳ ጠፉ። ብዙዎች ግን እግዚአብሔር ባዘጋጀዉ መፍትሔ እምነት ነበራቸዉ። . . . እነዚህ በንድፊያዉ የዛሉና ሊሞቱ የተቃረቡ ወገኖች እንደምንም ቀና ብለዉ ሲመለከቱ ፍጹም ይፈወሱ ነበር።

የፈዉስ ኃይል የሚወጣዉ ከእግዚአብሔር ብቻ እንደመሆኑ፤ ከናስ የተሠራዉ እባብ የተነደፈዉን ሰዉ ሊያድን የሚችል ኃይል እንደሌለዉ ሕዝቡ በሚገባ ያዉቅ ነበር። ጌታ በጥበቡ ኃይሉን በዚህ መልኩ መግለጥ መረጠ። በመረጠዉ በዚህ ቀላል መንገድ እስራኤላዊያን በኃጢአታቸዉ ምክንያት ይህ ሥቃይ እንደደረሰባቸዉ ተገነዘቡ። በተጨማሪ እግዚአብሔርን እስከታዘዙ ድረስ፤ እርሱ ጠባቂያቸዉ በመሆኑ፤ የሚፈሩበት አንዳችም ምክንያት ሊኖር እንደማይገባ ማረጋገጫ ተሰጣቸዉ።"–አበዉና ነቢያት ገጽ 62፣ 63 (2)

### ለ. ይህ ሁኔታ በቀደመዉ እባብ ንድፊያ ከሚሰቃዩት (ራእይ 12:9) እና ፈውስ ከሚሹት ጋር የሚመሳሰለዉ እንዴት ነው? ዮሐንስ 3:14፣ 15፤ 1፡ 29።

እርሱን በመመልከት ስለሚለወጥ ንስሃ የሚገባ ኃጢአተኛ ሁሉ "የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ" የሆነዉን የሱስን ይመልከት። ዮሐ. 1፡29። ይህን ካደረገ ፍርሃቱ ወደ ደስታ፣ ጥርጣሬዉም ወደ ተስፋ ይለወጣል። አመስጋኝ ይሆናል። የድንጋይ ልቡ ይሰበራል። የፍቅር ማዕበል ነፍሱን ያጥለቀልቀዋል። ክርስቶስ በዉስጡ ሆና ለዘለዓለም ሕይወት የዉሃ ምንጭ ይሆንለታል።"– የዘመናት ምኞት፣ ገጽ 453

4. **የሱስ ማን ነው?**

## ሀ. ክርስቶስ በምድር ላይ ፍጹም ሕይወት ኖሯል (1ኛ ጴጥሮስ 2:21፣ 22) ሆኖም ወደ እሱና ወደ ታማኝ ተከታዮቹ ከመቅረብ ይልቅ የብዙ ሰዎች ምላሽ ምንድን ነው? 2ኛ ጢሞ 3:12፤ ዮሐንስ 3:19፣ 20

*የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በርግጥም የተለዩ ሕዝቦች ነበሩ። ነቀፋ የሌለው ባህርያቸውና የማይዋዥቀው እምነታቸው የኃጢአተኛውን ሰላም የሚረብሽ ቀጣይ ተግሳጽ ነበር። በቁጥር ጥቂት ቢሆኑም፣ ድሃዎች፣ ደረጃ-የለሽና የክብር ማዕረግ የሌላቸው የነበሩ ቢሆኑም ባህርያቸውና አስተምህሮዎቻቸው በታወቀበት ሥፍራ ሁሉ ለክፉ አድራጊዎች ድንጋጤ ነበሩ። ስለዚህ አቤል የእግዚአብሔር መሰልነት በሌለው ቃየን ይጠላ እንደነበር እነርሱም በኃጢአተኞች ተጠሉ። ቃየን አቤልን ለገደለበት ተመሳሳይ ምክንያት፣ የመንፈስ ቅዱስን ገደብ አሽቀንጥረው መጣል የሚፈልጉ ሁሉ የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ገደሉ። የዚህ ባህርይ ንጽህናና ቅድስና ለራስ ወዳድነታቸውና ለብልሹነታቸው የማያቋርጥ ነቀፋ ስለሆነባቸው፣ አይሁዳውያን የሱስን ያልተቀበሉትና የሰቀሉት በዚሁ ተመሳሳይ ምክንያት ነበር። ከክርስቶስ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ፣ ታማኝ ደቀ መዛሙርቱ የኃጢአትን መንገድ የሚወዱትንና የሚከተሉትን ጥላቻና ተቃውሞ ቀስቅሰዋል።”*–The Great Controversy, p. 46.

## ለ. የሰውን ልጅ የመሳብ አቅም ያለው በአለም አዳኝ ውስጥ የተገለጠው ከፍተኛ ሀይል የትኛው ነው? 1ኛ ጢሞቴዎስ 3:16፤ ዮሐንስ 1:1-3፤ ዕብራውያን 1፡8

*ክርስቶስ ሁሉን ከፈጠረ፣ እርሱ ከሁሉም በፊት ነበር። ይህንን በተመለከተ የተነገሩት ቃላት በጣም ወሳኝ ከመሆናቸው የተነሳ ማንም በጥርጣሬ ውስጥ ሊያስገባ አያስፈልግም። ክርስቶስ በመሠረቱ ፍጹም አምላክ ነበር። እርሱ ከዘላለም ጀምሮ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ከሁሉ በላይ የሆነ አምላክ፣ ለዘላለም የተባረከም ነው።”*–Selected Messages, bk. 1, p. 247.

*እግዚአብሔር በልጁ ላይ የደረሰዉን የመጨረሻ ሰበአዊ ስቃይ በጥቅጥቅ ጨለማ ከለለዉ። ክርስቶስ ሲሰቃይ ያዩት ሁሉ መለኮታዊነቱን አዉቀዋል። ያ ሰበአዊ ፍጡራን ያዩት ፊቱ ፈጽሞ የሚረሳ አልነበረም። የቃየል ፊት ነፍስ ገዳይነቱን እንዳሳወቀበት ሁሉ እንዲሁም በክርስቶስ ፊት ላይ የእግዚአብሔር ገጸ ባሕርይ የሆነዉ ንጽሕና፣ ፍጹም ሰላማዊነትና ርህሩህነት ይታይበት ነበር። የየሱስ ከሳሾች ግን ለሰማይ ማሕተም ደንታ አልነበራቸዉም። የሱስ የሚያፌዙበት ሰዎች ቀና ብለዉ እየተመለከቱት ለረጅም ሰዓታት ሲሰቃይ ቆየ፣ በኋላ ግን እግዚአብሔር በምህረቱ በካባዉ ከለለዉ።”– የዘመናት ምኞት፣ ገጽ.* 799

*የክርስቶስን ውርደት አስብ። የወደቀዉን፣ በኃጢአት የተዋረደዉንና የረከሰውን የሰዉን ልጅ ተፈጥሮ ለራሱ ወሰደ። በደላችንን ተሸክሞ ሀዘናችንንና ሀፍረታችንን ተቀበለ። ሰው የተከበበባቸውን ፈተናዎች ሁሉ ተቋቁሟል። የሰውን ልጅ ከመለኮት ጋር አንድ አደረገ፤ መለኮታዊ መንፈስ በሥጋ ቤተ መቅደስ ውስጥም አደረ።”*–The SDA Bible Com-mentary [E. G. White Comments], vol. 4, p. 1147

## ሐሙስ ጥር 11

### 5. እግዚአብሔር ሥጋ ሆነ

**ሀ. የሰውን ልጅ ከአስጨናቂው ሰቆቃና ተስፋ ቢስ ሁኔታ ለማዳን ይህ መለኮታዊ አካል ምን ሆነ? ዮሐንስ 1:14፤ ዕብራውያን 2፡9**

**ለ. የሱስ ነውር በሌለው መለኮታዊ ማንነቱ ላይ ምን እንደወሰደ ግለጽ። ዕብራውያን 2:10፣11፣14፣17**

**ሐ. የሱስ በቀራኒዮ መስቀል ላይ የሚስበዉ ኃይል እንዲሠራ ምን ያህል ራሱን ዝቅ ማድረግ ነበረበት? ዕብራውያን 2:14፤ ፊልጵስዩስ 2:6–8፤ 2ኛ ጢሞቴዎስ 2:8**

ከዚህ አንፃር ሰዎች አንድ ቅንጣት ያክል ክብር (ከፍ ከፍ ማለት) ሊኖራቸው ይችላልን? መከራና ውርደት የሞላበትን የክርስቶስን ሕይወት ዱካ እንከተላለን እያሉ፤ ፈተና፣ ኀፍረትና ውርደት እንደማይሸከሙ ሆነው በኩራት አንገታቸዉን ቀና ማድረግ ይችላሉን? ለክርስቶስ ተከታዮች እላለሁ፡ ወደ ቀራንዮ ተመልከቱ እና ራሳችሁን ከፍ ከፍ በሚታደርጉበት በራሳችሁ ሀሳብ እፍረት ይሰማችሁ።

የሰማዩ ልዑል የተዋረደበት ይህ ሁሉ ውርደት፤ ለበደለኛዉና ለተወገዘዉ ለሰው ልጆች ነው። የሰውን ልጅ ከሥነ ምግባሩ ርኩሰት ለማንሣት ከዚያ ሊደረስበት የሚቻል ዝቅተኛ ጥልቀት እስከማይገኝበት ድረስ በውርደት እጅግ በጣም ዝቅ አለ።–The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 5, pp. 1127, 1128.

ሁሉን ለእርሱ ስናስረክብ የትኛዉን ነዉ ለራሳችን የምናስቀረዉ? የሱስ በኃጢአት የተበከለዉን ልብ በደሙ ሲያነጻ፣ ሲያጠራና ወደር በሌለዉ ፍቅሩ ሲያድን፣ ሰበአዊ ፍጡር ግን ሁለንተናዉን ለእርሱ ማስረከቡ አስቸጋሪ እንደሆነ አድርጎ ሲያስብ ይስተዋላል። ይህ ሲነገር ሲሰማም ሆነ ሲጽፈዉ ያሳፍረኛል!

እግዚአብሔር አስፈላጊያችን የሆነዉን ማንኛዉንም ነገር እንተዉ ዘንድ አይጠይቀንም። እርሱ የሚያደርገዉ ነገር ሁሉ ለልጆች ደህንነት የሚበጀዉን ነዉ። ክርስቶስን ያልመረጡት ነፍሳት ሁሉ ለራሳቸዉ ጥቅም ከሚሹት ነገር ሁሉ በእጅጉ የላቀዉን ሊሰጣቸዉ የሚችል መሆኑን ሊገነዘቡ ይገባል።"–ወደ ክርስቶስ የሚያመራ መንገድ፣ ገጽ. 43

## አርብ ጥር 12

### የግል የግምገማ ጥያቄዎች

1. የአብርሃም ልጆች ከነበሩት ከአይሁዳውያን ምን ትምህርት እናገኛለን?
2. የመጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና ሃሳቡን ሙሉ በሙሉ ልንስት የምንችለው እንዴት ነው?
3. በምድረ በዳ ከነበሩት ገዳይ እባቦች ምን ትምህርት ማግኘት እችላለሁ?
4. ወደ ቀራኒዮ ሰው መሳብ የሚቻለው በምንድን ነው?
5. የሱስ ኃጢአተኛ የሆነውን ሰብዓዊ ተፈጥሮ የለበሰው ለምንድን ነው?

# በመብራቴ ውስጥ ዘይት ስጠኝ

የመታሰቢያ ጥቅስ፡- በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።” (ዘካርያስ 4፡6)

መቀደሳችን የአብ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ለሚቆራኙት፣ ከእርሱ፣ ከልጁና ከመንፈሱ ጋር በቅዱስ ኅብረት እንደሚያቆማቸዉ እግዚአብሔር የገባው የቃል ኪዳን ፍጻሜ ነው። ዳግመኛ ተወልዳችኋልን? በክርስቶስ የሱስ አዲስ ሰው ሆናችኋልን? ከዚያም እናንተን ወክለው ከሚሠሩት ከሦስቱ ታላላቅ የሰማይ ኃይሎች ጋር ተባበሩ። ይህን በማድረጋችሁ የጽድቅን መመሪያዎች ለዓለም ሁሉ ትገልጣላችሁ።”–The Signs of the Times, June 19, 1901.

ለንባብ የተመረጠዉ፡ The Acts of the Apostles, pp. 47—56.

**እሁድ** **ጥር 14**

1. **መንፈስ ቅዱስ ማን ነው?**

**ሀ. መንፈስ ቅዱስ ከመቼ ጀምሮ ነበረ? ዘፍጥረት 1:2፤ መዝሙረ ዳዊት 51:11፤ ዕብራውያን 9፡14**

**ለ. የእግዚአብሔርን መንፈስ ሰፊ ተፈጥሮ ግለጽና አብራራ። መዝሙር 139:7-12፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 2:9–12፤ 2ኛ ጴጥሮስ 1፡21**

በአይሁዶች ጊዜ በኢኮኖሚያቸዉ ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ ተጽእኖ በታላቅ ሁኔታ ታይቷል፣ ነገር ግን በሙሉ አቅም አልነበረም። አምላክ መንፈሱን ለመስጠት የገባውን ቃል እንዲፈጸም ለብዙ ዘመናት ጸሎቶች ሲቀርቡ ነበር፣ እና ከእነዚህ ልባዊ ልመናዎች መካከል አንዳቸውም አልተረሱም።”–My Life Today, p. 36.

በኃጢአት ከመዉደቁ በፊት አዳም ከፈጣሪው ጋር ግልጽ የሆነ ግንኙነት ነበረው፤ ነገር ግን ሰው ራሱን ከእግዚአብሔር ስለለየው በመተላለፍ የሰው ልጅ ከዚህ ታላቅ መብት ተቆርጠዉ ቀረ። በዳግም ድነት እቅድ ግን፣ የምድር ነዋሪዎች አሁንም ከሰማይ ጋር የሚገናኙበት መንገድ ተከፍቷል። እግዚአብሔር በመንፈሱ ከሰዎች ጋር ተነጋግሯል፣ እና መለኮታዊ ብርሃኑን ለተመረጡት አገልጋዮቹ በመገለጥ ለአለም ሰጥቷል።”–God’s Amazing Grace, p. 190.

## 2.እርሱ አካላዊ ተፈጥሮ ያለዉ ነውን?

### ሀ. የመንፈስ ቅዱስን ባሕርይ የሚያሳዩ አንዳንድ የባሕርይ መገለጫዎችን ጥቀስ።

1. *መንፈስ ያውቃል።* 1ኛ ቆሮንቶስ 2፡9-12
2. *መውደድ የሚችል።* ሮሜ 15፡30
3. *መግባባት የሚችል።* 2ኛ ቆሮንቶስ 13፡14
4. *መግባባት የሚችል ከሆነ መናገር አለበት።* 1ኛ ጢሞቴዎስ 4:1
5. *እንደዚሁ ያስተምር ዘንድ ይችላል።* 1ኛ ቆሮንቶስ 2፡13
6. *እርሱ መመስከር የሚችል ነው።* ሮሜ 8፡16

ክርስቶስ ለተከታዮቹ ከዕርገቱ በኋላ መንፈሱን እንደሚልክላቸው አዎንታዊ ቃል ገባ። "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ [በመለኮት አምላክ]፣ በወልድ [በራሱ አለቃና አዳኝ]፣ በመንፈስ ቅዱስም [ክርስቶስን በመወከል ከሰማይ በተላከው] ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁን ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው። እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" አላቸው።"–The Review and Herald, October 26, 1897.

እንደ እግዚአብሔር አካል የሆነ አካል የሆነው መንፈስ ቅዱስ በእነዚህ መሠረቶች እየተመላለሰ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባናል።

*መንፈስ ቅዱስ አካል ነው፣ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራልና። ይህ ምስክርነት ሲሰጥ የራሱን ማስረጃ ይይዛል። በዚህ ጊዜ እኛ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን እናምናለን እናም እርግጠኞች እንሆናለን።...*

*መንፈስ ቅዱስ ባህሪ አለው፣ይህ ካልሆነ ግን እኛ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ለመንፈሳችን እና ከመንፈሳችን ጋር መመስከር አይችልም። እርሱ ደግሞ መለኮታዊ አካል መሆን አለበት፣ አለበለዚያ በእግዚአብሔር አእምሮ ውስጥ የተደበቁትን ምስጢሮች ማወቅ አይቻለዉም። በሰዉ ውስጥ ካለው ከራሱ መንፈስ በቀር ስለግለሰቡ የሚያውቅ ሌላ ሰው ማን ነው? እንደዚሁም የእግዚአብሔርን ሃሳብ ከእግዚአብሔር መንፈስ ሌላ ማንም አያዉቅም።*"–Evangelism, pp. 616, 617

በሰውነት ተሞልቶ፣ ክርስቶስ በሁሉም ቦታ በአካል ሊሆን አልቻለም። ስለዚህ እነርሱን ትቶ ወደ አባቱ ሲሄድና መንፈስ ቅዱስን በምድር ላይ ተተኪ እንዲሆን ሲልክላቸው በአጠቃላይ ለጥቅማቸው ነበር። መንፈስ ቅዱስ ራሱ ከሰው ልጅ ማንነት የተለየ እና ራሱን የቻለ ነው። እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በሁሉም ቦታ እንዳለ፣ በሁሉም ቦታ እንደሚገኝ ራሱን ይገልጻል።"–Manuscript Releases, vol. 14, p. 23.

ከመለኮታዊ ሦስቱ ሕያዋን አካላት ውስጥ ሦስትም ሕያዋን ናቸው፡ በነዚህ በሦስቱ ታላላቅ ኃይላት-አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ስም ክርስቶስን በሕያው እምነት የተቀበሉ ይጠመቃሉ፣ እናም የሰማይ ተገዢዎች በክርስቶስ አዲስ ሕይወት ለመኖር በሚያደርጉት ጥረት እነዚህ ኃይላት ታዛዥ ከሆኑት ጋር ይተባበራሉ።"–Evangelism, p. 615.

## 3. እርሱ አካላዊ ተፈጥሮ ያለዉ ነውን? (የቀጠለ)

### ሀ. የመንፈስ ቅዱስን ባሕርይ የሚያሳዩ ሌሎች ባሕርያት የትኞቹ ናቸው?

1. በምንጸልይበት ጊዜ ስለ እኛ ይማልዳል። ሮሜ 8:26፣ 27
2. የልዩ ስጦታዎች አከፋፋይ ነው። 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡7–11
3. ኃጢአተኛውንም ወደ ንስሐ ይጋብዛል። ራእይ 22፡17።
4. ኃጢአተኛውን ንስሐ እንዲገባ መጋበዙ ብቻ ሳይሆን በእምነትም ያትመዋል ወይም ያጸናዋል።ኤፌሶን 1፡13
5. እርሱ ስለሚያትመን ወይም ስለሚያጸናን፣ ምን እንዳናደርግ ማስጠንቀቂያ ነው የተሰጠን? ኤፌሶን 4፡30
6. አካላዊ ማንነት ስለሆነ የሱስ "እርሱ" እና "እሱ" የሚለውን የግል ተውላጠ ስም ለመንፈስ ቅዱስ 24 ጊዜ ተጠቀሞበታል። ከእነዚህ ምሳሌዎች አንዱ ዮሐንስ 14:16፣ 17 ነው።

አማላጃችን ክርስቶስ እና መንፈስ ቅዱስ ስለ ሰው ዘወትር ይማልዳሉ፤ ነገር ግን ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የፈሰሰ ደሙን እንደሚያቀርብ እንደ ክርስቶስ ስለ እኛ አይማልድም። መንፈስ በልባችን ላይ ይሰራል፣ ወደ ጸሎትና ወደ ንስሃ፣ ወደ ዉዳሴና ወደ ምስጋና ልባችን ይስባል። ከከንፈሮቻችን የሚፈሰው ምስጋና መንፈስ ቅዱስ የነፍስን ክሮች በቅዱስ ትውስታ በመነካካት የልብን ዜማ ሲያነቃቃ የሚገኝ ውጤት ነው።The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 6, pp. 1077, 1078.

ደስታ በጥቃቅንና በታላላቅ ነገሮች ስብጥር ነዉ። . . . እንደ ክርስቶስ በመሆን የእርሱን ባሕርይ መዉረስ ከፈለግን ነፍስን በየዕለቱ በትንንሽ ነገሮች መቀደስን ማሰልጠን አለብን። የምናባክነዉ ጊዜ የለንም። በሰም ላይ ግልጽ የሆነ የማሕተሙን ምልክት ለማግኘት የሚፈልግ ሰዉ ማኅተሙን በኃይል በሰሙ ላይ አይጫነዉም (አይጥለዉም)፤ ነገር ግን ማህተሙን በጥንቃቄና በጥብቅ ያስቀምጣል፤ ከዚያም ሰሙ የማህተሙን ቅርጽ እስኪያገኝ ድረስ በእርጋታ ይጫነዋል እንጂ። ልክ እንደዚሁ ነዉ ጌታ ከነፍሳችን ጋር የሚገናኘዉ።"–In Heavenly Places, p. 66.

መንፈስ ቅዱስ ሁሉንም እውነተኛ ጸሎት ይመራል። በምልጃዎቹ ሁሉ መንፈስ ስለ እኔና ስለ ቅዱሳን ሁሉ እንደሚማልድ አውቃለሁ። ነገር ግን ምልጃው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ ከፈቃዱ ፈጽሞ የሚቃረን አይደለም። "መንፈስ ደግሞ ድካማችንን ያግዛል። መንፈስም እግዚአብሔር ስለሆነ የእግዚአብሔርን አሳብ ያውቃል። ስለዚህ ለታመሙ ወይም ለሌሎች ፍላጎቶች በምናቀርባቸዉ ጸሎቶች ሁሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ መታከል ይኖርበታል።"–The Signs of the Times, October 3, 1892.

4.*ሥራው ምንድን ነው?*

**ሀ. የሱስ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ሆኖ ስለ እኛ ሊማልድ እንደሄደ፣ መንፈስ ቅዱስ የአዳኙ የግል ተወካይ መሆኑን የሚያሳየው ምንድን ነው? ዮሐንስ 15:26፤ 16:13፣ 14**

**ለ. የምንወደው ወዳጃችን በሌለበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ለብቸኛ ልባችን ምን ይሰጣል? ዮሐንስ 16፡7**

**ሐ. ወደ መለወጥ እንዴት ይመራናል? ዮሐንስ 16:8 (ህዳግ)፤ ዘካርያስ 4፡6**

*መንፈስ ቅዱስ የተሰጠዉ ምዕመናንን ለማደስና ለማነቃቃት ሲሆን ያለመንፈስ ቅዱስ ክርስቶስ የከፈለዉ መስዋዕት ዉጤት አይኖረዉም። የሰይጣን ኃይል ለብዙ ዘመናት እየተጠናከረ የመጣ ሲሆን ሰዎች ለዚህ ሰይጣናዊ ኃይል ያሳዩት የተገዥነት መንፈስ አስገራሚ ነዉ። ኃጢአትን መከላከልና ማሸነፍ የሚቻለዉ ከሶስቱ ስላሴዎች አንዱ በሆነዉና ሙሉ መለኮታዊ ኃይል ባለዉ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ብቻ ነዉ። የዓለም መድህን የሆነዉ ጌታ የሱስ ክርስቶስ የሠራዉን ሁሉ ለዉጤት የሚያበቃዉ መንፈስ ቅዱስ ነዉ። ልብ የሚነጻዉም በመንፈስ ቅዱስ ነዉ። አንድ አማኝ የመለኮታዊ ባሕርይ ተሳታፊ የሚሆነዉ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነዉ። ክርስቶስ መለኮታዊ ኃይል ያለዉን ቅዱስ መንፈስ የሰጠበት ምክንያት ሰዎች በዘር ዉርስም ሆነ በልምድ ያካበቱትን ኃጢአት የመስራት ዝንባሌ ለማሸነፍ እንዲችሉና የእርሱን ባሕርይ በቤተክርስቲያኑ ላይ ለማተም ነዉ።"–የዘመናት ምኞት፣ ገጽ.* 707፣ 708

*በልብ ላይ የተቀረጸው የክርስቶስ ምስል በባህሪ፣ በተግባራዊ ህይወት፣ ከእለት ከእለት ይገለጣል፣ ምክንያቱም እኛ አዳኙን እንወክላለን። መንፈስ ቅዱስ እንዲሰጣቸዉ ለሚለምኑት ሁሉ እንደሚያገኙ ቃል ገብቷል። ቅዱሳት መጻሕፍትን ስትመረምር፣ መንፈስ ቅዱስ ወደ የሱስ ክርስቶስ እያመለከተ ከጎንህ ይሆናል።"*–General Conference Daily Bulletin, February 15, 1895.

*ያለ መንፈስ ቅዱስ መገኘትና እርዳታ ቃሉን መስበክ ምንም አይጠቅምም፤ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ብቸኛው የመለኮታዊ እውነት አስተማሪ ነውና። እውነት ሕሊናን የሚያነቃቃው ወይም ሕይወትን የሚለውጥዉ ወደ ልብ ሲገባ በመንፈስ ቅዱስ ከታጀበ ብቻ ነው። አንድ አገልጋይ የእግዚአብሔርን ቃል ደብዳቤ ማቅረብ ይችል ይሆናል፤ እሱ ሁሉንም ትእዛዛቱን እና ተስፋዎቹን ሊያውቅ ይችላል፤ ነገር ግን ይህ ዘር በሰማይ ጠል ወደ ሰዎች ሕይወት ካልገባ በቀር የወንጌል ዘር መዝራቱ የተሳካ አይሆንም። ያለ እግዚአብሔር መንፈስ ትብብር፣ ምንም ዓይነት ትምህርት፣ ምንም ዓይነት ጥቅም፣ ምንም ያህል ትልቅ ቢሆንም እንኳ አንድን ሰው የብርሃን መስመር ሊያደርገው አይችልም።"*–Gospel Workers, p. 284.

**ሐሙስ** **ጥር 18**

### 5. መንፈስ ቅዱስ ከቤተክርስቲያን ጋር ያለው ግንኙነት

**ሀ. አንድ ሰው የእውነትን ሙሉ እውቀት ማግኘት የሚችለው እንዴት ነው? ዮሐንስ 16፡13**

**ለ. ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ስለሆነ እኛ እውነተኛይቱን ቤተ ክርስቲያን እንድናገኝ ሲረዳን ሚናዉ ምንድን ነው? 1ኛ ጢሞቴዎስ 3:15**

**ሐ. መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ውስጥ ሊኖረን በጣም አስፈላጊ ስለሆነ፣ የመንፈስ ቅዱስን ሙሉ ኃይል ለማግኘት ምን ማድረግ አለብን? ሉቃስ 11:9-13**

*"የክፉው ኃይል አለቃ የሚገታዉ በእግዚአብሔር ኃይል በመለኮት ሦስተኛ አካል በሆነው በመንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው።"*–Evangelism, p. 617.

*ቤተክርስቲያን በጥቃቅን ነገሮች እስከረካች ድረስ፣ የእግዚአብሔርን ታላቅ ነገር ለመቀበል ብቁ አትሆንም። ነገር ግን ልብ ንጹሕ የሚሆንበት መንገድ ይህ ነውና የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ለምን አንራብምና አንጠማምም? መለኮታዊ ኃይል ከሰው ጥረት ጋር እንዲተባበር ጌታ ያቅዳል። ጌታችን የሱስ ለሁለተኛ ጊዜ ከመምጣቱ በፊት የመንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል ትርጉም ለክርስቲያን መረዳቱ በጣም አስፈላጊ ነው። ተነጋገሩበት፣ ስለርሱም ጸልዩ፣ ስለ እርሱ ስበኩ። ምክንያቱም ወላጆች ለልጆቻቸው መልካም ስጦታን ለመስጠት ከሚጓጉት በላይ ጌታ ለእኛ መንፈስ ቅዱስን ለመስጠት ፈቃደኛ ነውና።"*–The Review and Herald, No-vember 15, 1892

**አርብ** **ጥር 19**

### የግል ግምገማ ጥያቄዎች

1. *መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ዘመን ንቁ ወኪል እንደነበረ እንዴት እናውቃለን?*
2. *የመንፈስ ቅዱስ የባሕርይ መገለጫዎች ምንድን ናቸው?*
3. *በክርስቶስ የምልጃ ሥራ እና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?*
4. *በመዳን እቅድ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ አንዳንድ በጣም አስፈላጊ ሚናዎች ምንድን ናቸው?*
5. *ሰዎች እውነተኛይቱን ቤተ ክርስቲያን እንዲረዱ የመንፈስ ቅዱስ ተሳትፎ ምንድን ነው?*

## ሰንበት፣ ጥር 27፣ 2015

## የመጀመሪያ ሰንበት ሥጦታ ለአለም የአደጋ እፎይታ

በአለም አቀፍ ደረጃ የተፈጥሮ አደጋዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ ተደጋጋሚና ከባድ እየሆኑ መጥተዋል። እነዚህም—የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ሱናሚዎች፣ አውሎ ነፋሶች፣ ማዕበሎች፣ ከፍተኛ አውሎ ነፋሶች፣ ጎርፍና የእሳተ ገሞራ ፍንዳታዎችን የሚያካትቱ ቢሆንም በዚህ ብቻ የተወሰኑ አይደሉም። ከተሰወረ ማደሪያውም ዐውሎ ነፋስ፥ ከሰሜንም ብርድ ይወጣል። . . . ለተግሣጽ ወይም ለምድሩ ወይም ለምሕረት ቢሆን፥ ሰው በሚኖርበት ዓለም ላይ ያዘዘውን ሁሉ ያደርግ ዘንድ ፈቃዱ ወደ መራችው ይዞራል።" (ኢዮብ 37፥9-13)።

ሁሉን ቻይ የሆነው የዚህች ውብ ፕላኔትና የፈጠራቸው ፍጥረታት የመጨረሻ ጥቅሞችን በአእምሮው ይይዛል - ዛሬም ፣ ብዙ እንግዳ እና ከባድ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ከነፍሳት ዋና ጠላት ጦር መሳሪያ ሆነዉ እየመጡ ነው።

"[ሰይጣን] በሽታዎቻቸውን ሁሉ መፈወስ የሚችል ታላቅ ሐኪም እንደሆነ አድርጎ ለሰው ልጆች ቢታይም ብዙ ሕዝብ የሚኖርባቸው ከተሞች እስኪወድሙና ምድረበዳ እስኪሆኑ ድረስ በሽታንና ጥፋትን ያመጣል። አሁን እንኳ፣ በዚህች ሰዓት በሥራ ላይ ነው። በየብስና በባህር አደጋዎችና ጥፋቶች፣ በታላላቅ አውዳሚ እሳቶች፣ በኃይለኛ ነፋስ (tornedo)ና በረዶ፣ በውሽንፍር፣ በጎርፎች፣ በአውሎ ነፋሳት፣ በውኃ ማዕበል፣ በመሬት መንቀጥቀጥ፣ በእያንዳንዱ ሥፍራ በሺህ አይነት መንገድ ሰይጣን ኃይሉን እየተጠቀመ ነው። እየጎመራ ያለውን አዝመራ ጠራርጎ ይወስደውና ረሃብና ጭንቀት ይከተላል። ለአየሩ ገዳይ ብክለት ይሰጥና በሺዎች የሚቆጠሩ በወረርሽኙ ይረግፋሉ። እነዚህ ጥፋቶች የበለጠ ተደጋጋሚና አስከፊ እየሆኑ የሚሄዱ ናቸው። ውድመት በሰውና በእንስሳ ላይ ይሆናል። "ምድርም አለቀሰች ረገፈችም። ታላላቆች ደከሙ። ምድርም ከሚቀመጡባት በታች ረክሳለች፤ ሕጉን ተላልፈዋልና፣ ስርዓቱንም ለውጠዋልና፣ የዘላለሙንም ቃል ኪዳን አፍርሰዋልና" [ኢሳ 24÷4፣5]።"–The Great Controversy, pp. 589, 590.

ምንም ይሁን ምን፣ በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት ለሚደርሰው ከፍተኛ ሰብዓዊ ሥቃይ የአምላክ ልጆች ምላሽ እንዲሰጡ የተጠሩት እንዴት ነው?

ጌታ በምድር ላይ በተገኘበት ቦታ ሁሉ መከራን ለማስታገስ የራሱን ምሳሌ እንድንከተል አዞናል። የተፈጥሮ አደጋ በሚከሰትበት ጊዜ ለሕይወት የሚያስፈልጉት መሠረታዊ ነገሮች በድንገት ይጠፋሉ፣ ስለዚህ በማንኛውም ቦታ መርዳት ክርስቲያናዊ ግዴታችን ነው። ለአለም የአደጋ እፎይታ ያደረጋችሁት ለጋስ ሥጦታ ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ይረዳል።

በቅድሚያ እናመሰግናለን!

ወንድሞቻችሁ ከጀነራል ኮንፈራንስ

# ወንጌል በብሉይ ኪዳን

*የመታሰቢያ ጥቅስ፡-* *"በመጽናትና መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአልና።"* (ሮሜ 15፡4)

*የሱስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ህዝቡን ከኃጢአታቸው ለማዳን ነው። እርሱ የኃጢአት አገልጋይ አይደለምና በኃጢአታችን አያድነንም። ለክርስቶስ መለኮታዊ ጥሪ ምላሽ ልንሰጥና ከኃጢአታችን ንስሐ መግባትና ቅርንጫፉ ከወይኑ ጋር አንድ እንደሆነ ራሳችንን ከክርስቶስ ጋር አንድ ማድረግ አለብን።"*–The Signs of the Times, February 15, 1892.

*ለንባብ የተመረጠዉ፡ አበዉ እና ነቢያት፣ ገጽ* 63—70።

**እሁድ ጥር 21**

1. **ትምህርት ከታሪክ**

### ሀ. ታሪክን በተለይም ቅዱስ ታሪክን ማጥናት የሚያስፈልገን ዋናው ምክንያት ምንድን ነው? መክብብ 3:15

*በእያንዳንዱ ታላቅ ተሐድሶ ወይም ሐይማኖታዊ እንቅስቃሴ፣ ከዘመን ዘመን እግዚአብሔር በምድር ላይ የሚሰራው ሥራ አስደናቂ ተመሳሳይነት እንዳለው ያሳየናል። እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ግንኙነት የሚያካሂድባቸው መርሆዎች ሁል ጊዜም አንድ አይነት ናቸው። የዚህ ዘመን አስፈላጊ እንቅስቃሴዎች በፊት ከነበሩት ጋር የሚነፃፀሩ ናቸው፤ እናም በጥንት ዘመናት ቤተ ክርስቲያን የነበራት ተሞክሮ ለዚህ ለእኛ ዘመን ታላቅ ዋጋ የያዘ ትምህርት አለው።"*–The Great Controversy, p. 343.

### ለ. የታሪክ ጥናት የወንጌልን ተስፋ ስለሚያሰፋ (ሮሜ 15፡4) ይህ ተስፋ በኃጢአት ለታመመች ነፍስ ምን ይሰጣል? ሮሜ 1:16፤ ሉቃስ 19፡10

*እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በእግዚአብሔር መንፈስ የተሰጠና ጠቃሚም ነው። ብሉይ ኪዳን ከአዲሱ ያላነሰ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ብሉይ ኪዳንን ስናጠና ግድ የለሽ የሆነዉ አንባቢ ምድረ በዳውን ብቻ ሲመለከት እኛ የሕያዉ የሆኑ ምንጮች ሲፈልቁ እናገኛለን።"–ትምህርት፣ ገጽ*. 213.

2. **የፍጥረት ፍፁምነት**

**ሀ. የመጀመሪያዎቹ ወንድና ሴት በፈጣሪያቸው እጅ ገና እንደተፈጠሩ ምን ዓይነት ባሕርይ ነበራቸው? ዘፍጥረት 1:31፤ መክብብ 7:29**

*ሰው በመልኩና በጸባዩ በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጠረ። ክርስቶስ ብቻ "የእግዚአብሔር ነጸብራቅ" ነዉ (ዕብራዊያን* 1፡3)። *ሰዉ ግን በእግዚአብሔር አምሳያ ተፈጠረ። ተፈጥሮዉም ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ስምሙ ነዉ። አዕምሮዉ መለኮታዊ ነገሮችን ለመረዳት ይችላል። ስሜቶቹ ንጹህ ነበሩ ፍላጎቱም በዓላመዉ ቁጥጥር ሥር ነበር። የእግዚአብሔርን አምሳል በመልበሱ ቅዱስና ደስተኛ ለአምላካዊዉም ፈቃድ ፍጹም ታዛዥ ነበር።"–አበዉና ነቢያት፣ ገጽ*. 36 (1)

**ለ. የሰው ዘር በዚህ ፍጹም ሁኔታ ውስጥ ለዘላለም እንዲኖር ምን አስፈለገ? ዘፍጥረት 2:16፣ 17(ህዳግ)**

*ክርስቶስ የሕጉን ጥያቄዎችን አልቀነሰም። በማያሻማ ቋንቋ ለእርሱ መታዘዝን እንደ የዘላለም ሕይወት ቅድመ ሁኔታ አቅርቧል–በኃጢአት ከመውደቁ በፊት ከአዳም እንደሚፈለገው በተመሳሳይ ሁኔታ አቅርቧል። ጌታ በገነት ከሰው ከጠበቀው ከነፍስ ፍፁም ታዛዥነትና ነቀፋ ከሌለበትን ፅድቅ ያነሰ ነገር አሁን ከእኛ አይጠብቅም።*

*በጸጋው ቃል ኪዳን ሥር ያለው መስፈርት በኤደን ከተሰጠው መስፈርት ጋር ተመሳሳይ ነው–ቅዱስ፣ ጻድቅና መልካም ከሆነው ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር የሚስማማ ነው።"*–Christ's Object Lessons, p. 391

**ሐ. ሰው ስለወደቀ/ኃጢአት ስለሠራ (ዘፍጥረት 3) በመጀመሪያ ወላጆቻችን ላይ ብቻ ሳይሆን በመላው የሰዉ ዘር ላይ ምን መዘዝ አስከተለ? ሮሜ 5:12፤ 6:23**

*የእግዚአብሔርን ህግ በመታዘዝ ሰው እንደ ቅጥር ተከቦ ከክፉትም ይጠበቃል። ይህንን በመለኮታዊነት የቆመውን አጥር በአንድ ነጥብ የሚያፈርስ ማንም እርሱን ከክፉ የሚጠብቀዉን ኃይሉን ያጣል፤ ጠላት ሊያፈርስና ሊያጠፋ የሚገባበትን መንገድ ከፍቷልና።*

*በአንድ ነጥብ ላይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ችላ በማለት፣ የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን በዓለም ላይ የወዮታን በሮች ከፍተዋል። እና የእነሱን ምሳሌ የሚከተል እያንዳንዱ ግለሰብ ተመሳሳይ ውጤት ያጭዳል። የእግዚአብሔር ፍቅር የሕጉን ትእዛዛት ሁሉ ይደነግጋል፣ ከትእዛዙም የሚርቅ የራሱን ሐዘንና ጥፋት በራሱ እጅ ይሠራል።"*–Thoughts From the Mount of Blessing, p. 52.

3. **ኃጢአት ተገለፀ**

### ሀ. የአዳም መተላለፍ የእግዚአብሔርን ህግ መጣስ እንደሚጨምር እንዴት እናውቃለን? ሮሜ 7:7፤ ከዘጸአት 20:17፤ 1ኛ ዮሐንስ 3፡4

የእግዚአብሔር ህግ በሰዎች ላይ የአስገዳጅነት ዉጤት እንደሌለዉ የሚሰብኩ ወገኖች የእርሱን ሕግ ማክበር የማይቻል እንደሆነ ይናገራሉ። ይህ እዉነት ቢሆን ኖሮ አዳም ሕጉን በመተላለፉ ስለምን ቅጣት ተቀበለ!የቀደሙት ወላጆቻችን ኃጢአት በዓለም ላይ ጥፋተኝነትንና ሐዘንን አስከተለ። እንደ እግዚአብሔር ቸርነትና እንደ ምህረቱ ባይሆንማ ኖሮ ሰበአዊዉ ዘር ተስፋ ቢስ ሆኖ በቀረ ነበር። “የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነዉ” ሮሜ 6፡23። በሰዉ ልጆች አባት ላይ ቅጣት ከተበየነም በኋላ የእግዚአብሔር ሕግ ሊጣስ አይችልም።”–አበዉና ነቢያት፣ ገጽ. 56 (1)

ያለ ሕጉ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ንጽህናና ቅድስና እንዲሁም ስለ ራሳቸው ኃጢአትና እድፍ ትክክለኛ መረዳት አይኖራቸውም። እውነተኛ የኃጢአተኛነት ስሜት አይኖራቸውም፤ የንስሐም አስፈላጊነት አይታያቸውም። የእግዚአብሔርን ሕግ ተላላፊ ሆነው የጠፉ መሆናቸው ስለማይታያቸው የሚያስተሰርየው የክርስቶስ ደም እንደሚያሻቸው አያስተውሉም። የመዳን ተስፋ ያለ ፍፁም የልብ ለውጥ ወይም ያለ ሕይወት ተሐድሶ ተቀባይነት ያገኛል። በእንዲህ ሁኔታ የላይ ላይ መለወጦች በስፋት ይንሰራፋሉ፤ ከክርስቶስ ጋር ፈጽሞ ህብረት አድርገው የማያውቁ እልፍ አዕላፋት የቤተ ክርስቲያን አባል ይሆናሉ።”–The Great Controversy፣ p. 468.

### ለ. እነዚህን ጥቅሶች ስናነብ፣ የሱስ ከሕግ መተላለፍ ሊያድነን እንደመጣ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያሳየው እንዴት ነው? ማቴዎስ 1፡21

የሱስ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ለማዳን ሞተ፣ በክርስቶስም መቤዠት ማለት የእግዚአብሔርን ሕግ መተላለፍ ትቶ ከኃጢአት ሁሉ ነጻ መውጣት ማለት ነው። በእግዚአብሔር ሕግ ላይ በጠላትነት የሚነሣሣ ልብ ከክርስቶስ ጋር የሚስማማ አይደለም፣ እርሱም በቀራንዮ መከራን ከተቀበለ በኋላ ሕጉን በአጽናፈ ዓለም ፊት ሕጉን ለማጽናትና ከፍ ከፍ ለማድረግ ከተሠቃየ ከክርስቶስ ጋር አይስማማም።”–Faith and Works, p. 95.

ህዝቡን ከህግ መተላለፍ ለማዳን የመጣ ድንቅ ወዳጅ የሱስ አለን። ኃጢአት ምንድን ነው? የኃጢአት ብቸኛ ፍቺ ሕግን መተላለፍ ነው። እንግዲህ እዚህ ላይ የሱስ ክርስቶስ ነው፣ በትክክል መጥቶ ጽድቁን ለእኛ የሚሰጠን፤ በእርሱ በማመን እንጂ በራሳችን ሃይል ማሸነፍ አንችልም። በየሱስ ክርስቶስ ካመንህ እርሱን ዛሬ ታገኘዋለህ። አሁን አዳኝህ እንደሆነ ማመን አለብህ፣ ምክንያቱም እሱ የሞተልህና ጽድቁን የሚቆጥርልህ፤ እሱ ለተጣሰው የእግዚአብሔር ህግ መስፈርቶች ሁሉ ታዛዥ በመሆኑ ነው። ይህን ካደረግህ፣ ስለ የሱስ ክርስቶስ የማዳን እውቀት ይኖርሃል። አዳምና ሔዋን ሕጉን ስለጣሱ ኤደን ገነትን አጥተዋል ነገር ግን አንተ ሕጉን ከተላለፍክ መንግሥተ ሰማያትን ታጣለህ።”–The Ellen G. White 1888 Materials, p. 128.

4. **የአማኞች አባት**

## ሀ. ለምን የብሉይ ኪዳን አበዉ አብርሃም የአማኞች ሁሉ አባት በመባል ይታወቃል? ገላትያ 3፡6-9

*የአብርሃም ፈተና በሰው ልጅ ላይ ሊመጣ ከሚችለው ፈተና ሁሉ እጅግ የከፋ ነው። በዚህም ፈተና ወድቆ ቢሆን ኖሮ የአማኞች ሁሉ አባት ተብሎ አይመዘገብም ነበር። ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ቢያፈነግጥ ኖሮ፣ ዓለም የማያጠራጥር እምነትና ታዛዥነትን የሚያሳይ አበረታች ምሳሌ ታጣ ነበር። ለእግዚአብሔር ሊሰጥ ከሚችለው በላይ ውድ ነገር እንደሌለ እንድንማር ትምህርቱ በየዘመናቱ እንዲበራ ተሰጥቷል። እያንዳንዱን ስጦታ ለአገልግሎቱ ጥቅም ላይ የሚውል፣ እንደ ጌታ ንብረት ስንመለከት ነው፣ ሰማያዊውን በረከት የምናገኘው። በአደራ የተሰጠህን ርስትህን ለእግዚአብሔር መልሰህ ስጥ፣ ብዙም አደራ ይሰጥሃል። ንብረቶቻችሁን ለራሳችሁ አኑሩ፣ ያኔ በዚህ ህይወት ምንም አይነት ሽልማት አታገኙም፣ የሚመጣውን ህይወት ሽልማትንም ታጣላችሁ።*”–The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 1, p. 1094.

*መቅደሱ የተገነባበት ቦታ ለረጅም ጊዜ እንደ የተቀደሰ ቦታ ይቆጠር ነበር። ቦታዉም የአማኞች ሁሉ አባት አብርሃም ለእግዚአብሔር ትዕዛዝ በመታዘዝ ብቸኛዉን (አንዲያ) ልጁን መስዋዕት ለማድረግ ፈቃዱን ያሳየበት ቦታ ነበር። እዚህ ላይ አምላክ ከአብርሃም ጋር የበረከት ቃል ኪዳንን አድሶ ነበር፤ እሱም በልዑል ልጅ መሥዋዕት አማካኝነት ለሰው ልጆች የሚሰጠውን ክቡር መሲሐዊ ተስፋን ይጨምራል።*”–Prophets and Kings, p. 37.

## ለ. የዘሩ ተስፋ በአብርሃም ዘመን እንኳን የወንጌልን ስብከት የሚያሳየው እንዴት ነው? ዘፍጥረት 22:15–18፤ ገላትያ 3፡16

*የምድር አሕዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ የሚለው ቃል ኪዳን ለአብርሃም ታደሰ። ዘፍጥረት* 22፡18 *ይህ ተስፋ ክርስቶስን ያመለክታል። ስለዚህም አብርሃም ተረድቶታል (ገላትያ* 3፡8, 16 *ተመልከት)፣ እናም ለኃጢአት ይቅርታ በክርስቶስ አምኗል። ይህ እምነት ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት። ከአብርሃም ጋር የገባው ቃል ኪዳንም የአምላክን ሕግ ሥልጣንን አስጠብቆታል።”–አበዉና ነቢያት፣ ገጽ*. 370.

## ሐ. አብርሃም ወንጌልን የተቀበለ ተብሎ ተለይቷል፣ እና በዘመኑ የነበሩት ሌሎች ብዙዎች ግን እንደዚህ አልተባሉም፤ ለምን? ዘፍጥረት 26:5፤ ያዕቆብ 2፡19-24

*አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ። ማመኑን እንዴት እናውቃለን? ሥራው የእምነቱን ባሕርይ ይመሰክራል፣ እምነቱም ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት።*The SDA Bible Commentary [E. G. White Com-ments], vol. 7, p. 936

5. **ሕግ በቀሪው የብሉይ ኪዳን ክፍሎች**

**ሀ. ሕጉ እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ቃል በቃል ከመናገሩ በፊት እንደነበረ ሌላ ምን ምሳሌዎች አሉን? (ዘዳ 5፡22-26) ዘጸአት 15:26፤ 16፡28።**

እስራኤላውያን በምድረ በዳ በነበራቸው ረጅም ጉዞ በየሳምንቱ በሚያደርጉት ጊዜያዊ ቆይታ የሰንበትን ቅዱስነት እንዲያስተዉሉ ለማድረግ በዕለቱ ሦስት እጥፍ ተዓምራቶችን እንዲታዘቡ ይደረጉ ነበር። ከወትሮዉ እጥፍ መጠን ያለዉ መና በስድስተኛዉ ቀን ሲወርድላቸዉ በሰንበት ቀን ግን አንድም አይኖርም። ለሰንበት ቀን የሚያስፈልጋቸዉ መጠን ጣፋጭና ንጹህ ሆኖ ይቆያቸዉ የነበረ ሲሆን፤ ነገር ግን በሌሎቹ የሳምንቱ ቀናት በዕለቱ የሰበሰቡትን መና ለቀጣዩ ቀን ቢያስቀምጡ ይበላሽባቸዉ ነበር።

ለእስራኤላዊያኑ ይወርድ ከነበረዉ መና በተያያዘ መመለከት እንደምንችለዉ አንዳንዶች እንደሚሉት ሰንበት የተቋቋመዉ ትዕዛዛቱ በሲና በተሰጡ ጊዜ አልነበረም። እስራኤላዊያን ወደ ሲና ከመምጣታቸዉ አስቀድሞ ሰንበት በእነርሱ ላይ አስገዳጅነት እንዳለዉ አስተዉለዋል። ሰንበት ዝግጅት ሲያደርጉ አርብ ዕለት እጥፍ መሰብሰባቸዉና በነጋታዉ ከሰበሰቡት አንዱም ተበላሽቶ አለመጣሉ፤ ቅዱስ የሆነዉ የእረፍት ቀን ተፈጥሮ ያለማቋረጥ በአዕምሮአቸዉ ተጽዕኖ አድርጎባቸዉ ነበር። ከሕዝቡም አንዳንዶቹ መና ሊሰበስቡ በሰንበት በወጡ ጊዜ ጌታ ፡- "ትእዛዜንና ሕጌን ለመፈጸም እስከ መቼ እምቢ ትላላችሁ?" ሲል ሙሴን ጠየቀዉ።"–አበዉና ነቢያት፣ ገጽ. 331 (1)

**ለ. አምላክ እስራኤላዊያን በንግግርና በጽሑፍ የሰፈረውን የአሥርቱ ትእዛዛት የሥነ ምግባር ሕግ ምን እንዲያደርጉ አስቦ ነበር? ዘዳግም 6:1-9**

**ሐ. ጌታ ይህንን አቋም እስከ ብሉይ ኪዳን መጨረሻ ድረስ እንደጠበቀው እንዴት እናውቃለን? ሚልክያስ 4:4፤ 3፡6።**

**አርብ ጥር 26**

**የግል የግምገማ ጥያቄዎች**

1. የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ መሠረታዊ ሥርዓቶች በእኛ ጊዜ የሚሠሩት እንዴት ነው?
2. አምላክ እንደማይለወጥ የሚያሳየው ከኤደን ወዲህ ምን መሥፈርት ነው?
3. ከኃጢአት ችግር ጋር በተያያዘ የሱስ ወደዚህ ዓለም የመጣበት ዓላማ ምንድን ነው?
4. የአብርሃም እምነት በሥራው የተገለጸው እንዴት ነው?
5. ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር ያለን ግንኙነት ምን መሆን አለበት?

# የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ሕግ

*የመታሰቢያ ጥቅስ፡- "ትእዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና፤ ትእዛዛቱም ከባዶች አይደሉም።"* (1ኛ ዮሐንስ 5፡3)።

*[ክርስቶስ] እርሱ እንደወደደን እርስ በርሳችን እንድንዋደድ አዞናል። ሃይማኖት በእግዚአብሔር ፍቅር ላይ የተመሰረተ ነው፣ ይህም ደግሞ እርስ በርስ እንድንዋደድ ይመራናል። በምስጋና፣ በትህትና፣ በትዕግስት የተሞላ ነው። እራስን መስዋእት የሚያደርግ፣ ታጋሽ፣ መሐሪና ይቅር ባይ ነው። ህይወቱን በሙሉ ይቀድሳልና በሌሎች ሰዎችም ላይ ተጽእኖዉን ያሳድራል።"*–Testimonies for the Church, vol. 4, p. 223.

*ለንባብ የተመረጠዉ፡ አበዉ እና ነቢያት፣ ገጽ* 303—314።

**እሁድ ጥር 28**

## 1. የማይለወጥ ፈጣሪ

**ሀ. ክርስቶስ የሰው ልጅ ሆኖ በዚህ ምድር ሲኖር ከእግዚአብሔር የሥነ ምግባር ሕግ ጋር ስላለው ግንኙነት ምን ማስተዋል አለብን? ማቴዎስ 5:17፣ 18**

**ለ. የሕጉን ውጫዊ አከባበር በተመለከተ የአይሁድ መሪዎች ምን ያህል ልዩ ነበሩ? ማቴዎስ 23:23፤ ፊልጵስዩስ 3፡4**

*[የአይሁድ መሪዎች] ቅዱስ ለመምሰል መንፈሳዊ ቅንዓት ነበራቸዉ፤ ነገር ግን የልብን ቅድስና ችላ አሉ። ሕግ አክባሪዎች በመምሰል አክራሪዎች ሲሆኑ የሕጉን መንፈስ ግን ዘዉትር ይሽሩት ነበር። ትልቁ ፍላጎታቸዉ ክርስቶስ ለኒቆዲሞስ ይገልጽለት የነበረዉ ለዉጥ ነበር፤ ይህም አዲስ የግብረገብነት ልደትን፤ ከኃጢአት መጽዳትን፤ የእዉቀትና የቅድስና መታደስን ያካትታል።"–የዘመናት ምኞት፣ ገጽ*. 161

**ሐ. የሱስ ሕግን የሚጥስ እንዳልነበር ከሚገልጸው የፍርድ ሂደቱ ጋር በተያያዘ ምን ልንመለከት እንችላለን? ማቴዎስ 26:59፣ 60**

*አዳኙም ሆነ ተከታዮቹ የሰንበትን ህግ አልጣሱም። ክርስቶስ ሕያው የሕግ ወኪል ነበር። የቅዱስ ትእዛዛቱን መጣስ በሕይወቱ ውስጥ አልተገኘም። እርሱን የሚኮንኑበት ምክንያት የሚሹትን ሕዝብ ተመልክቶ ማንም ሳይጠይቀዉ እንዲህ አላቸዉ፡- ከእናንተ ስለ ኃጢአት የሚወቅሰኝ ማን ነው? ዮሐንስ* 8:46፣ R.V.–Ibid., p. 287.

1. **ሕጉ በየሱስ ልብ ውስጥ**

## ሀ. የሱስ ወደ ምድር ሲመጣ ምን ተዘጋጅቶለታል? ዕብራውያን 10፥5-10

የአለም አዳኝ አክሊሉን ጥሎ፣የንግሥና ልብሱን ጥሎ፣ እና ሰው ሆኖ ወደ ዓለማችን እንዲመጣ ዕቅድ እንጂ አጋጣሚ አልነበረም። በሰው ልጅ ፋንታ ይቆም ዘንድ መለኮታዊነቱን ሰበአዊነትን አለበሰው፣ ሰውነቱ በዘር በአዳም አለመታዘዝ ከወደቀዉ ሰብአዊነት ጋር ተቀላቀለ።"–The Southern Work, p. 85.

## ለ. ስለ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን ያለውን ተመሳሳይ ክፍል ስናነብ በልቡ ውስጥ ምን እንደሚሆን ነዉ የተተነበየው? መዝሙረ ዳዊት 40:6-8

ኃጢአትን፣ ሀዘንንና ሞትን ያስከተለው የህግ መተላለፍ ነው። ሰይጣን እግዚአብሄር ለፈጠራቸው ዓለማቶችና ለሰማያዊ አእምሮዎች የእግዚአብሔርን ህግ መጠበቅ የማይቻል መሆኑን እንደሚያረጋግጥ ተናገረ። አዳም ለጠላት ፈተና ተሸንፎ ከከፍታውና ከቅድስናው በወደቀ ጊዜ ሰይጣንና መላእክቱ ደስ አላቸው። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ዙፋን በጣም ምስጢራዊ ቃላትን የሚናገር ድምፅ ተሰማ። (መዝሙር 40:6—8 ተጠቅሷል።] ሰው ሲወድቅ ክርስቶስ የሰው ምትክና ዋስ የመሆኑን ዓላማ አስታውቋል።"–The Review and Herald, September 3, 1901.

## ሐ. ክርስቶስን ወደ ልባችን ስንቀበል ከእርሱ ጋር የማይነጣጠል ምን እየተቀበልን ነው? መዝሙር 119:70፣ 72፣ 77፣ 174

ከአገልግሎት ጋር የሚያስተሳስረዉ ቀንበር የእግዚአብሔር ሕግ ነው። ሰበአዊ ሠራተኛዉን ከእግዚአብሔር ፍቃድ ጋር የሚያስተሳስረዉ በኤዴን ገነት የተገለጸዉ በሲና ተራራ ላይ በይፋ የታወጀዉና በአዲሱ ቃል ኪዳን መሠረት በሰዎች ልብ ላይ የተጻፈዉ ሕግ ነዉ። የራሳችንን ዝንባሌ እንድንከተልና ፍላጎታችን ወደሚመራን አቅጣጫ ሁሉ እንድንሔድ ቢደረግ ኖሮ የሰይጣን ጭፍራዎችና የእርሱ ባሕርይ አንጸባራቂዎች በሆንን ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር ከፍ ባለዉ፣ በተከበረዉና ወደ ላይ በሚስበዉ ፈቃዱ ክልል ዉስጥ እንድንወሰን አደረገን። የአገልግሎት ተግባራችን በትዕግሥትና በአስተዋይነት እንድንቀበል ፍላጎቱ ነዉ። ክርስቶስ ራሱ የአገልግሎትን ቀንበር ሰዉ ሆኖ ተሸክሞታል።"–የዘመናት ምኞት፣ ገጽ. 332

ጽድቅ ማለት መቀደስ ነዉ፣ እግዚአብሔርንም መምሰል ነው፣ ‹እግዚአብሔር ፍቅር ነው›። 1ኛ ዮሐንስ 4፡16 ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር መስማማት ነው፣ ምክንያቱም "ትእዛዛትህ ሁሉ ጽድቅ ናቸው" (መዝሙር 119፡172) እና "ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው" (ሮሜ 13፡10)። ጽድቅ ፍቅር ነው ፍቅርም የእግዚአብሔር ብርሃንና ሕይወት ነው። የእግዚአብሔር ጽድቅ በክርስቶስ የተገለጠ ነው። እርሱን በመቀበል ጽድቅን እናገኛለን።"–Thoughts From the Mount of Blessing, p. 18.

## 2. እንደ ህጉ እና እንደ ነቢያት

### ሀ. የሱስ ሕይወቱ እርሱ መሲሕ መሆኑን የሚያሳይ ሕያው ማስረጃ እንደሆነ ለደቀ መዛሙርቱ ሲገልጽላቸው የትኞቹን ጥቅሶች ተጠቅሟል? ሉቃስ 24:27፣ 44

እውነት በአዕምሯቸው ጠንካራ ሥር እንዲሰድ የተመኘው በራሱ ግላዊ ምስክርነት በመደገፋቸው ምክንያት ብቻ ሳይሆን እርግጥ በሆኑት፣ ወደፊት ሊሆን ላለው ጠቋሚ በነበረው የሕጉ ተምሳሌቶችና ጥላዎች፣ እንዲሁም በብሉይ ኪዳን ትንቢታት ጭምር ነበር። የክርስቶስ ተከታዮች በእውቀት ላይ የተመሠረተ እምነት ያስፈልጋቸዋል፤ ይህም ለግላቸው ብቻ ሳይሆን የክርስቶስን እውቀት ወደ ዓለም እንዲያሰራጩት ነው። ይህንንም እውቀት ለማካፈል እንደመንደርደሪያ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ወደ "ሙሴና ነብያት" አመላከታቸው። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አስፈላጊነትና ዋጋ፣ በእንዲህ መልኩ በተነሳው አዳኝ ምስክርነት ምን ያህል እንደሆነ ታይቷል።"–The Great Controversy, p. 349.

### ለ. ደቀ መዛሙርቱ የወንጌልን መልእክት ሲሰብኩ የሱስ ቃል የተገባዉ መስሑ መሆኑን ያረጋገጡት እንዴት ነው? የሐዋርያት ሥራ 28:23

የእግዚአብሔር መንፈስ ከተነገሩት ቃላት ጋር አብሮ ነበር፣ እናም ልቦች ተነኩ። ሐዋርያው ከብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ያቀረበው ማስረጃ እና እነዚህም በናዝሬቱ የሱስ አገልግሎት ፍጻሜያቸውን እንዳገኙ መናገሩ ተስፋ የተጣለበትን መሲሕ መምጣትን የሚናፍቁ ብዙ ነፍሳትን አምጥቷል። "የድኅነት የምሥራች" ለአይሁድም ለአሕዛብም እንደ ሆነ የተናገረ የኤርምያስ ማረጋገጫ ቃል በሥጋ ከአብርሃም ልጆች ጋር ላልተቆጠሩት ተስፋንና ደስታን አምጥቷል።"–The Acts of the Apostles, pp. 172, 173.

ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች ሲሰብክ፣ ስለ መሲሑ የተነገሩትን የብሉይ ኪዳን ትንቢቶችን አቀረበ። ክርስቶስ በአገልግሎቱ ውስጥ ለእነዚህ ትንቢቶች የደቀ መዛሙርቱን አእምሮ ከፈተላቸው። ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ አብራራላቸው። ሉቃስ 24፡27 ጴጥሮስ ክርስቶስን ሲሰብክ ማስረጃውን ከብሉይ ኪዳን አሳይቷል። እስጢፋኖስም ተመሳሳይ አካሄድ ተከትሏል። እና ጳውሎስ በአገልግሎቱ የክርስቶስን ልደት፣ መከራ፣ ሞት፣ ትንሳኤ እና ዕርገት የሚናገሩትን ቅዱሳት መጻህፍት ያቀርብ ነበር። በሙሴና በነቢያት በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት የሰጡት ምስክርነት የናዝሬቱን የሱስ መሲሑ መሆኑን በግልጽ አረጋግጧል፤ ከአዳም ዘመን ጀምሮ በአባቶችና በነቢያት ሲናገር የነበረው የክርስቶስ ድምፅ እንደሆነም አሳይቷል።"–Ibid., pp. 221, 222.

## 3. ህግ እና እምነት

### ሀ. በየሱስ እንደ ግል አዳኛችን ማመን ሕጉን ያስወግዳልን? ከሆነ ለምን ወይም ካልሆነስ ለምን አይሆንም? ሮሜ 3፡31

### ለ. በትዕዛዝ ጠባቂዎች ላይ ምን በረከት ተነግሯል? ራእይ 22:14

የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በመተላለፍ በአዳምና በሔዋን ላይ እርግማን ወረደባቸው፣ እናም የሕይወትን ዛፍ የማግኘት መብታቸውን ተነፍገዋል። ክርስቶስ ሰውን ለማዳን ሞቷል፣ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ህግ ክብር ይጠብቃል። “ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስ ሥልጣን እንዲኖራቸው በደጆችዋም ወደ ከተማይቱ እንዲገቡ ትእዛዙን የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው” ይላል። የእግዚአብሔር ልጅ እዚህ ላይ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት መፈጸም ለሕይወት ዛፍ የመብት ቅድመ ሁኔታ አድርጎ አቅርቧል። የእግዚአብሔርን ትእዛዛት መተላለፍ ሰውን ወደ ሕይወት ዛፍ የመድረስ መብትን ያሳጣል። ክርስቶስ የሞተው በደሙ አማካኝነት ለእግዚአብሔር ህግ መታዘዙ ሰውን ለሰማያዊው በረከት ብቁ እንዲሆን እና እንደገናም ለሕይወት ዛፍ መብት እንዲሰጠው ነው።”–Spiritual Gifts, vol. 3, p. 88

በብርጭቆዉ ባህር ላይ እየተራመድን ወደ ከተማዋ መግቢያ በራፍ ስናመራ መላዕክት ከበዉን ነበር። የሱስ ኃያልና ባለግርማ ክንዱን አንስቶ ያንን የተንቆጠቆጠ በራፍ በመክፈት “ልብሶቻችሁን በደሜ በማጠባችሁን ለእዉነትም በጽናት ለመቆማችሁ - እነሆ ግቡ” አለን። እኛም ሁላችን ወደ ዉስጥ በማለፍ ከተማዋ የመግባት በእርሷ ላይ ፍጹም ባለ መብት እንደሆንን ተሰማን።”–ቅድመ ጽሑፎች፣ ገጽ. 17.

### ሐ. ይህ አምላክ ፈጽሞ እንደማይለወጥ የሚያሳየው እንዴት ነው? ዕብራውያን 13፡8

ግዴታችንን በታማኝነት ከተወጣን የሱስ ታላቅ ነገርን ያደርግልናል። ፈቃዳችንን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ማስገዛት አለብን። ትንንሽ ነገሮች ብለን በምንጠራቸው ነገሮችም ቢሆን ጌታን ሁሉንም ትእዛዛቱን በመታዘዝ ማክበር አለብን። እውነት፣ ልክ እንደ መለኮታዊው ደራሲዉ፣ በሚፈልገው መስፈርት የማይለወጥ ነው፣ ትናንትም፣ ዛሬም እና ለዘላለም ያው ነው። ከሰዎች ወጎች ጋር አይጣጣምም፣ ከአስተያየታቸው ጋር አይጣጣምም። እውነት በእግዚአብሔር ሕዝብና በዓለም መካከል መለያየትን አምጥቷል። ይሁን እንጂ ቀደም ባሉት ዓመታት፣ ለአምላክ የተለየ ሕዝብ በመሆናችን በአምላክ ዘንድ ተቀባይነትን ካገኘን ታዲያ እርሱ አሁን ያለንበትን ቦታ እንዴት ይመለከተዋል? ከቀድሞ ቀላልነታችን ከተውን በኋላ መንፈሳዊነትን አግኝተናልን?”–The Signs of the Times፣ May 25, 1882.

4. **በልብ ውስጥ ተጽፏል**

**ሀ. የሱስ ባደረገበት መንገድ የእግዚአብሔር ሕግ በሕይወታችን ውስጥ እንዴት ሊናሳይ እንችላለን? ዕብራውያን 10:16፤ 8፡10።**

እግዚአብሔር የተቀደሰዉን ሕጉን የሰጠን ሰበአዊ ዘርን ስለሚወድ ነዉ። እኛ ሕግን በመተላለፍ ከሚደርስብን ጥፋት እንድንድን ሲል የጽድቅ መርሖችን ይገልጽልናል። ሕግ የእግዚአብሔር ሀሳብ መግለጫ ነዉ፤ እኛም ሕጉን በክርስቶስ አማካይነት ስንቀበል የእኛ ሀሳብ ይሆናል። ለተፈጥሯዊ ምኞቶች፣ መጥፎ ዝንባሌዎችና ወደ ኃጢአት ለሚመሩን ፈተናዎች ተገዥ እንዳንሆን ያደርገናል።"– የዘመናት ምኞት፣ ገጽ. 306

**ለ. ይህን የሰማይ ጉዞ ከመጀመራችን በፊት እንኳን እግዚአብሔር ምን ያሳየናል? 1ኛ ዮሐንስ 4:19፣ 8**

ምድርም ስለእግዚአብሔር በትክክል ካለ፤መረዳት የተነሳ ጨለመች። ጨለማዉ እንዲገፍና ዓለምም ወደ እግዚአብሔር እንድትመለስ ለማድረግ የሰይጣን ኃይል መሻር ነበረበት። ይህም በኃይል አልነበረም የሚፈጸመዉ። በኃይል መጠቀም ከእግዚአብሔር መንግሥት መርሖ ጋር ይጋጫል። እግዚአብሔር የሚሻዉ ከፍቅር የመነጨ አገልግሎትን ነዉ። ፍቅር በትዕዛዝ ወይም በኃይል አይገኝም። ፍቅር የሚገኘዉ ከፍቅር ነዉ። እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት እርሱን ማፍቀር ነዉ። ይህን ሥራም ሊያደርግ የቻለዉ በዩኒቨርስ ብቸኛና ሕያዉ የሆነዉ ፈጣሪ ብቻ ነዉ። የእግዚአብሔርን ፍቅር ስፋትና ጥልቀት ለመግለጽ የሚችለዉ ይህን ፍቀር ያወቀ ብቻ ነዉ።"–ኢቢድ፣ ገጽ. 11.

**ሐ. ይህ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ውስጥ ካደረ በኋላ ምን ሊሆን ይችላል? ዮሐንስ 14፡15-17**



**የግል የግምገማ ጥያቄዎች**

1. የሱስ በሰው ልጆች መካከል ሲኖር የእግዚአብሔርን ባሕርይ የጠበቀው እንዴት ነው?
2. በእውነተኛ አማኞች ዘንድ ተመሳሳይ የክርስቶስ ባሕርይ እንዴት ይገለጣል?
3. የሱስ መሲሕ መሆኑን በትክክል ለማመን ከየትኞቹ ትንቢቶች ጋር በደንብ መተዋወቅ አለብን?
4. ኃጢአተኛ የሰው ልጆች በኃጢአት የተከለከሉበትን የሕይወት ዛፍ የማግኘት መብት እንዴት ሊያገኙ ቻሉ?
5. እውነተኛ ታዛዥነትን ማግኘት የምንችልበት ብቸኛው መንገድ ምንድን ነው?

## የወንጌል ምስጢር

*የመታሰቢያ ጥቅስ፡- ለእነርሱም እግዚአብሔር በአሕዛብ ዘንድ ያለው የዚህ ምሥጢር ክብር ባለ ጠግነት ምን እንደ ሆነ ሊያስታውቅ ወደደ፥ ምሥጢሩም የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በእናንተ ዘንድ መሆኑ ነው።”* (ቆላ 1፡27)።

*ከእስካሁን ድረስ ከእኛ ጋር ያለውን ግንኙነት እና እርሱ የተነሳሳበትን ምክንያቶች መረዳት እንችላለን፣ ገደብ የለሽ ፍቅር እና ምሕረት ከዘላለማዊ ኃይል ጋር የተዋሃደ መሆኑን እንገነዘባለን። ለማወቅ የምንችለውን ያህል የእርሱን ዓላማዎች መረዳት እንችላለን፤ እናም ከዚህ ባሻገር አሁንም በሁሉን ቻይ ሀይል፣ የአብና የሁሉም ልዑል ገዢ ፍቅርና ጥበብ ላይ መተማመን አለብን።”*–Testimonies for the Church, vol. 5, p. 699.

*ለንባብ የተመረጠዉ፡ ሥነ ትምህርት፣ ገጽ* 169—172።

**እሁድ የካቲት 5**

### 1. ለመረዳት የሚከብዱ ቅዱሳት መጻሕፍት

**ሀ. ጴጥሮስ ስለ አንዳንድ የጳውሎስ ጽሑፎች ምን ተመልክቷል? 2ኛ ጴጥሮስ 3፡14-17 በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ስለ አንዳንድ ነገሮች ምን ማስተዋል አለብን? ዘዳግም 29፡29**

*ችሎታ ያላቸው ሰዎች የህይወት ዘመናቸውን ያጠናሉ እና ጸሎትን ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመመርመር ሰጥተዋል፣ ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ያልተመረመሩ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ። አንዳንድ የቅዱሳት መጻሕፍት ምንባቦች በወደፊት ሕይወት ክርስቶስ እስኪያብራራላቸው ድረስ ፍጹም በሆነ መረዳት አይረዱትም። የሚፈቱ እንቆቅልሾች አሉ፣ ከሰው አእምሮ ጋር ሊጣጣሙ የማይችሉ መግለጫዎች አሉ። ጠላትም በነዚህ ዉይይት ሳይደረግባቸዉ ቢቀሩ የተሻለ በሚሆኑ በነዚህ ነጥቦች ላይ ክርክር ለመቀስቀስ ይሞክራል።”*–Gospel Workers, p. 312.

**ለ. ቅዱሳን ጽሑፎችን መቅረብ ያለብን በምን ዓይነት ዝንባሌ ነው? ዮሐንስ 7፡17**

*ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመመርመር የመጣህበት መንፈስ ከጎንህ ያለውን የረዳትነት ባሕርይ ይወስናል። ከብርሃን አለም የመጡ መላእክት በትህትና መለኮታዊ መመሪያን ከሚፈልጉ ጋር ይሆናሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በአክብሮት በጎደለዉ ሁኔታ፣ በራስ በመመካት ስሜት፣ ልብ በጭፍን ጥላቻ በተሞላበት ሁኔታ ከተከፈተ፣ ሰይጣን ከጎንህ ነው፣ እናም የእግዚአብሔርን ቃል ጠማማ በሆነ መንገድ በፊታችን ያስቀምጣል።*Testimonies to Ministers, p. 108

## 2. የክብር ሚስጥሮች

### ሀ. አምላክ ለተቀረው ዓለም እንዲያካፍል ሲል ለጳውሎስ የትኞቹን ልዩ ነገሮች ገለጠለት? ሮሜ 16:25፣ 26፤ ቆላስይስ 1፡27

"ለጳውሎስ የቀራንዩ መስቀል ብቸኛው ትልቁ ርዕስና ውስጣዊ ፍላጎቱ ነበር። የተሰቀለውን የናዝሬቱን የሱስ ተከታዩችን ከሚያሳድድበትና ከሚያሰቃይበት ተመልሶ ስራውን ሁሉ እርግፍ አድርጎ በመተዉ ለክርስቶስ ከተገዘበት ሰዓት ጀምሮ በዚያኔ ለተገለጠለት ወሰን ለሌለው ለእግዚአብሔር ፍቅር ራሱን ጨርሶ አሳልፎ ሰጠ። የክርስቶስን ሞት በተመለከተ ጊዜ በጳውሎስ ህይወት አስገራሚ ለውጥ ተከሰተ፣ የራሱን እቅድ እርግፍ አድርጎ በመተዉ ከሰማይ እቅድ ጋር ተስማማ። ከዚያ ሰዓት ጀምሮ በክርስቶስ አዲስ ሰው ሆነ፣ ኃጢአተኛ እግዚአብሔር በልጁ መስዋዕትነት ያደረገውን አስገራሚ ፍቅር በተገነዘባ ጊዜ የሚሰማውን ጥልቅ ስሜት፣ አስገራሚ መለኮታዊ ተጽዕኖንና በልብ ውስጥ ስለሚሆነው ፍጹም ለውጥ ጳውሎስ በህይወቱ በተግባር አይቷል። ክርስቶስ ልብን ከተቆጣጠረ በኋለ ሌላ ተቀናቃኝ ሃይል ስለማይኖር ክርስቶስ በሰው ህይወት ሁሉም በሁሉ ይሆናል፤ ይህም ጳውሎስ በተግባር ያየው እውነት ነው።"–The Acts of the Apostles, p. 245.

### ለ. በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ አንድ ነገር ለመረዳት የሚያስቸግር ከሆነ በጉዳዩ ላይ ምርምር ለማድረግ እንኳን ለምን እንሞክራለን? 2ኛ ጢሞቴዎስ 3:16፣ 17

የክርስቶስ መስቀል በሁሉም ነቀፋና መገለል የተሸፈነ ነው፣ ነገር ግን እርሱ ለሰው ልጅ የመኖር ተስፋ ነው። የክርስቶስን መስቀል ለመሸከም የሚያፍር ማንም እግዚአብሔርን የመምሰል ምስጢር ሊረዳው አይችልም። ተከታዮቹ እንዲሆኑ ምድራዊ ሀብትን በደስታ ለመሠዋት ፈቃደኛ ካልሆኑ በስተቀር ማንም ሰው ክርስቶስ ለራሱ ወሰን በሌለው ዋጋ የገዛቸውን በረከቶች ማስተዋልና ማድነቅ አይችልም። እያንዳንዱ ራስን መካድ እና ለክርስቶስ የተከፈለ መስዋዕትነት ሰጪውን ያበለጽጋል፣ እናም ስለ ዉድ ስሙ የሚታገሰው መከራና ስድብ ሁሉ በክብር መንግሥት ውስጥ የመጨረሻውን ደስታና የማይሞት ሽልማትን ይጨምራል።"–Confrontation, p. 93

### ሐ. ትክክለኛ መደምደሚያ ላይ ለመድረስ የሚያስፈልገንን ነገር ያብራሩ። ዮሐንስ 16፡13

ያለ መንፈስ ቅዱስ ምሪት ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማጣመም ወይም በተሳሳተ መንገድ ለመተርጎም ያለማቋረጥ ተጋላጭ እንሆናለን። ጥቅም አልባ የሆነና በብዙ አጋጣሚዎች አዎንታዊ ጉዳት ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ አለ። የእግዚአብሔር ቃል ያለ አክብሮትና ያለ ጸሎት ሲከፈት፤ ሀሳቡ እና ፍቅር በእግዚአብሂር ላይ ካልተመሰረቱ ወይም ከፈቃዱ ጋር በማይጣጣሙበት ጊዜ አእምሮ በጥርጣሬ ይደመናል። እናም ጥናቱ ይበልጥ ጥርጣሬዎችን የሚያጠናክር ይሆናል። ጠላት ሐሳብን ይቆጣጠርና ትክክለኛ ያልሆኑትን ትርጓሜዎችን ይጠቁማል።"–Testimonies for the Church, vol. 5, pp. 704, 705

## 3. የንጉሣዊው የሞራል ሕግ

### ሀ. ከተለመዱት እምነት በተቃራኒ የአሥሩ ትእዛዛት ህግ በመስቀል ላይ እንዳልጠፋ እንዴት እናውቃለን? ያእቆብ 2:8፣ 9

*"ብዙ ኃይማኖታዊ አስተማሪዎች ክርስቶስ በሞቱ ሕጉን እንደሻረውና በዚህም ምክንያት ሰዎች ከመጠይቁ ነፃ እንደሆኑ አስረግጠው ይናገራሉ። አንዳንዶች ከባድ ቀንበር እንደሆነ በማመልከት፣ ከሕጉ ባርነት በተቃራኒ በወንጌሉ ስር ሊጣጣም የሚገባውን ነፃነት ያስተምራሉ።*

*ነብያትና ሐዋርያት ግን የእግዚአብሔርን ቅዱስ ሕግ በእንዲህ ሁኔታ አላዩትም ነበር። ዳዊት እንዲህ አለ፦ "ትእዛዛትህን ፈልጌያለሁና አስፍቼ [በነፃነት] እሄዳለሁ*/And I will walk at liberty for I seek thy precepts" [*መዝ* 119÷45]። *ከክርስቶስ ሞት በኋላ የፃፈው ሐዋርያው ያዕቆብ ስለ አሥርቱ ትዕዛዛት ሲናገር፦ "የንጉሥ ሕግ እንዲሁም ነፃ የሚያወጣውን ፍፁሙን ሕግ" በማለት ይገልፀዋል* [*ያዕ* 2÷8፤1÷25]። *ከስቅለት ግማሽ ምዕተ ዓመት በኋላ፣ ምስጢር ገላጩ [ክርስቶስ] "ትዕዛዛቱን የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው ስልጣናቸው በሕይወት ዛፍ ላይ ይሆን ዘንድ በደጅም ወደ ከተማ ይገባሉ"* [*ራዕ* 22÷14] *በማለት በረከትን ያውጅላቸዋል።"*–The Great Controversy, p. 466.

*አንድ ሰው ራሱን ለክርስቶስ አሳልፎ ሲሰጥ አእምሮው በሕግ ቁጥጥር ስር ይሆናል፤ ነገር ግን ለታሰሩት ሁሉ ነጻነትን የሚያውጅ የንጉሣዊ ሕግ ነው። ሰው ከክርስቶስ ጋር አንድ በመሆን ነፃ ወጥቷል። ለክርስቶስ ፈቃድ መገዛት ወደ ፍጹም ሰውነት መመለስ ማለት ነው።"*–The Ministry of Healing, p. 131

### ለ. ባልንጀራችንን እንደ ራሳችን መውደድን የሚገልጸው የትኛው ህግ ነው? ሮሜ 13:9፤ ከዘጸአት 20:1–17 ጋር አወዳድር።

*ከአስርቱ ትእዛዛት የመጀመሪያዎቹ አራቱ "እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ ዉደድ" በሚል ይጠቃለላሉ። የመጨረሻ ስድስቱ ሕግጋት ደግሞ "ሰዉን ሁሉ እንደ ራስህ አድርገህ ዉደድ" በሚል ተጠቃልሏል። እነዚህ ሁለቱ ሕግጋት የፍቅር መሠረታዊ ደንብ መግለጫ ናቸዉ። የመጀመሪያዉን ጠብቆ ሁለተኛዉን መሻር ወይም ሁለተኛዉን አክብሮ የመጀመሪያዉን መጣስ አይቻልም። እግዚአብሔር በልባችን ዉስጥ ትክክለኛዉን ቦታ ከያዘ ለባለእንጀራዎቻችን ማለትም ለሰዎች ትክክለኛዉ ቦታ ይሰጣቸዋል። ይህም ማለት ሰዉን ሁሉ እንደ ራሳችን አድርገን እንወዳለን ማለት ነዉ። ሰዉን ያለ አድልዎ ለመዉደድ የምንችለዉ እግዚአብሔርን ከሁሉም አስበልጠን የወደድን እንደሆን ብቻ ነዉ።. . .*

*ክርስቶስ የእግዚአብሔር ህግ አንዱ ከሌላዉ ጋር ግንኙነት የሌለዉና አንዱ ከሌላዉ የሚበልጥ ሌላዉ ግን አስፈላጊነቱ ዝቅተኛ በመሆኑ ችላ ቢባል ቅጣት የማያስከትል የተላያየ ትዕዛዝ አለመሆኑን ለአድማጮቹ አስተምሯቸዋል። ጌታችን የመጀመሪያ አራቱንና የመጨረሻ ስድስቱን ትዕዛዛት መለኮታዊ አንድነትን በማሳወቅ እግዚአብሔርን መዉደድ የሚገለጸዉ ትዕዛዛቱን በመጠበቅ መሆኑን አስተምሯል።"– የዘመናት ምኞት፣ ገጽ.* 630፣ 631

## 4. በሕግ ይፈረዳል

**ሀ. በሰው ልጆች ላይ የሚደርሰውን ፍርድ ሰፋ ባለ መጠን ያብራሩ። መክብብ 11:9፤ ሮሜ 14:10፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 5:10፤ ዕብራውያን 9:27**

*ሁሉም በተሰጠው ብርሃን መሰረት ይፈረድባቸዋል። ጌታ በመልእክተኞቹ የመዳንን መልእክት ይልካል፣ የሚሰሙትም የባሪያዎቹን ቃል በሚይዙበት መንገድ ተጠያቂ ይሆናል። እውነትን ለማግኘት ከልባቸው የሚፈልጉ ሁሉ ከአምላክ ቃል አንጻር የቀረቡትን ትምህርቶች በጥንቃቄ ይመረምራሉ።"*– The Acts of the Apostles, p. 232.

**ለ. በፍርዱ ውስጥ ምን መመዘኛ ጥቅም ላይ ይውላል? ያዕቆብ 2፡12**

**ሐ. ይህ የትኛው ህግ ነው? ያዕቆብ 2:11፤ ከዘፀአት 20 ጋር አወዳድር።**

*በትምህርቱ፣ ክርስቶስ ከሲና የተነገሩት የህግ መርሆች ምን ያህል ዘላቂ እንደሆኑ አሳይቷል። በዚያ ሕግ ሕያው ተፈጻሚነት የሰጠው መሠረታዊ ሥርዓቶቹ ታላቁን የጽድቅ መስፈርት–ለፍርድ በሚቀመጥበት በዚያ ታላቅ ቀን ሁሉም የሚፈረድበት፣ መጻሕፍትም የሚከፈቱበት መለኪያ ነው።"*– Selected Messages, bk. 1, p. 211..

*የእግዚአብሔር ህግ ባህሪያቸዉና የሰዎች ህይወት በፍርድ የሚፈተኑበት መለኪያ ነው። ጠቢቡ እንዲህ ይላል፡- "እግዚአብሔርን ፍራ÷ ትእዛዙንም ጠብቅ ይህ የሰው ሁለንተናዊ ግዴታ ነውና። እግዚአብሔር ሥራን ሁሉ ወደ ፍርድ ያመጣዋልና። መክብብ* 12:13፣ 14 *ሐዋርያው ያዕቆብ ወንድሞቹን እንዲህ ሲል መክሯቸዋል፡- "በነጻነት ሕግ ፍርድን እንደሚቀበሉ ሰዎች ተናገሩ፣ እንዲሁም አድርጉ። ያዕቆብ* 2:12"–The Great Controversy, p. 482.

*ፍርዱ ተቀምጦ መጻሕፍቱ ሲከፈቱ÷ ሰውም ሁሉ በመጻሕፍት እንደ ተጻፉት ፍርድ በሚቀበሉበት ጊዜ÷ በዚያን ጊዜ በእግዚአብሔር የተሸሸጉት የድንጋይ ጽላቶች የጽድቅ መለኪያ ሆነዉ ወደ ዓለም ፊት ይቀርባሉ። ያን ጊዜ ወንዶችና ሴቶች የመዳናቸው ቅድመ ሁኔታ ለእግዚአብሔር ፍጹም ሕግ መታዘዝ እንደሆነ ያያሉ። ማንም ለኃጢአት ሰበብ አያገኝም። በዚያ ሕግ የጽድቅ መሠረታዊ መርሆ መሠረት፣ ሰዎች የሕይወት ወይም የሞት ፍርድ ይቀበላሉ።"*–Selected Messages, bk. 1, p. 225

**ሐሙስ** **የካቲት 9**

## 5. ህጉ እንደ አስተማሪ

### ሀ. ህግን የመረዳት ወይም እውነትን የማወቅ አላማ ምንድን ነው? ዮሐንስ 3:18-21፤ ሮሜ 7፡7

ከእግዚአብሔር ጋር የመታረቅ የመጀመሪያው እርምጃ ኃጢአተኛ መሆንን ማወቅ ነው። “ኃጢአትም እርሱ ሕግን መተላለፍ ነው”፤ “ኃጢአት በሕግ ይታወቃልና” [1ኛ ዮሐ 3÷4፤ ሮሜ 3÷20]። ኩነኔውን ማየት ይችል ዘንድ ኃጢአተኛው በእግዚአብሔር በታላቁ የጽድቅ ሚዛን ደረጃ ባህርይውን መፈተን አለበት። የጽድቅ ባህርይን ፍጽምና የሚያሳይ መስታዎት ነውና በራሱ ያለውን ጉድለት እንዲያስተውል ያስችለዋል።”– The Great Controversy, p. 467.

### ለ. የእኛን ተጨባጭ ሁኔታ በማጋለጥ ሕጉ ያንን መገለጥ ምን ያደርጋል? ገላ 3፡24።

“በገላትያ ሰዎች ሕግን በተመለከተ ተጠይቄ ነበር፡፡ እኛ ወደ ክርስቶስ እንድንመጣ መምህራችን የሚሆንን ሕግ ምንድነዉ? እኔም መለስኩ: ሁለቱም፤ ሜዳዊ ሕግና የአሥርቱ ትዕዛዛት የግብረገብ ደንቦች ናቸዉ።

ክርስቶስ የአይሁድ ኢኮኖሚ ሁሉ መሠረት ነበር። የአቤል ሞት ቃየን የእግዚአብሔርን እቅድ በታዛዥነት ትምህርት ቤት በየሱስ ክርስቶስ ደም ለመዳን፣ ክርስቶስን በሚያመለክት መስዋዕት ለመቀበል እምቢ በማለቱ ምክንያት ነው። ቃየን ለዓለም የሚፈስ የክርስቶስን ደም የሚያመለክተውን ደም ማፍሰስ አልተቀበለም። ይህ ሁሉ ሥርዓት በእግዚአብሔር የተዘጋጀ ነበር እና ክርስቶስ የስርዓቱ ሁሉ መሠረት ሆነ። ይህም ኃጢአተኛ ሰብዓዊ ወኪሎችን ወደ ክርስቶስ ሀሳብ የማምጣት ሥራው መጀመሪያ ነው።”–The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 6, p. 1109.

**አርብ** **የካቲት 10**

## የግል የግምገማ ጥያቄዎች

1. መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት ልባችንን ማዘጋጀት ምን ያህል አስፈላጊ ነው?
2. የመዳን ወንጌልን ያህል ሚስጥራዊ የሆነን ነገር በትክክል መረዳት የሚቻለው እንዴት ነው?
3. ከመስቀል በኋላ የእግዚአብሔር ሕግ አሁንም በሥራ ላይ መሆኑን የምንረዳባቸው ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
4. ለዘላለማዊ ህይወት ቅድመ ሁኔታ የሆነው ታላቁ የባህርይ መለኪያ ምንድን ነው?
5. ሕጉ ለምን አስፈለገ፣ የእኛ አዛዥ ሆኖ፣ እኛን ወደ ክርስቶስ እንዲያመጣን?

# በመስቀሉ ላይ የተቸነከረ

*የመታሰቢያ ጥቅስ፡- በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው። እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል።”* (ቆላስይስ 2፡14)

*የአስሩ ትእዛዛት ህግ አለ፤ ዘላለምም ዘመን ይኖራል። የክርስቶስ ሞት ምሳሌ ሆኖ የነበረዉ የመሥዋዕት አገልግሎት አስፈላጊነት ጥላው ከዋናዉ ጋር በተገናኘ ጊዜ ቆመ። የእግዚአብሔር በግ ሙሉና ፍጹም መስዋዕት ነበር።”*–The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 6, p. 1116.

*ለንባብ የተመረጠዉ፡* Selected Messages, bk. 1, pp. 229—235.

**እሁድ** **የካቲት 12**

1. **ሌላ ህግ**

**ሀ. ከእኛ ጋር የሚቃረን እና በመስቀል ላይ የተቸነከረውን ህግ መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት ይገልጸዋል? ቆላስይስ 2:14፤ ኤፌሶን 2፡15 የአሥሩ ትእዛዛት መሠረታዊ ሥርዓቶች በኤደን ፍጹምነት ውስጥ ስለነበሩ ይህ መግለጫ እነዚያን ሕጎችንም የሚያመለክት እንዳልሆነ እንዴት እናውቃለን? ዘፍጥረት 1፡31**

**ለ. በዚህ የሥርዓት ሕግ ውስጥ የተካተቱት አንዳንድ ልዩ ነገሮች ምንድን ናቸው? ቆላስይስ 2:16፣ 21 እነዚህ ሰንበትና ሌሎች ሕጎች በፍጥረት ላይ ከተሰጠው የመጀመሪያ የሥነ ምግባር ሕግ ጋር የተያያዙ ናቸው ወይስ ከተሰጡ በኋላ ወደፊት ለሚመጣው ክስተት ጥላ ናቸው? ቆላስይስ 2፡17**

*እግዚአብሔር ሰባተኛዉን ቀን በኤደን ገነት በመባረክ ለፍጥረት ሥራዉ መታሰቢያ አድርጎ አቆመዉ። ሰነበት የመላዉ የሰዉ ዘር አባትና ተወካይ ለሆነዉ ለአዳም ተሰጠ። ሰንበትን ማክበር በምድር ላይ የሚኖሩ ፍጥረታት ሁሉ እግዚአብሔር እዉነተኛና ኃያል ፈጣሪያቸዉ መሆኑን የሚያሳዩበትና ሁሉም የእጆቹ ሥራ ዉጤት መሆናቸዉን በመመስከር ለእግዚአብሔር ምስጋናቸዉን የሚያቀርቡበት ነዉ። በመሆኑም ሰንበት በመታሰቢያነት ለመላዉ የሰዉ ዘር ተሰጠ። ከዚህ ዉጭ እንደ ጥላ የቀረበበት ወይም ለተወሰኑ ሕዝቦች ብቻ የተሰጠበት ሁናቴ የለም።”*–አበዉና ነቢያት፣ ገጽ. 39.(1)

2. **የመተዳደሪያ ህግ**

**ሀ. እነዚህ የኋለኛው ክስተት ጥላ የነበሩት ነገሮች በእርግጥ እንደ ህግ ተጠርተዋል - እና ከሆነስ ምን አይነት ህግ ነው? ዕብራውያን 10፡1**

የእግዚአብሔር ልዩ ሀብቱ ብሎ የሚጠራቸው፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ፣ ሁለት ዓይነት የሕግ ሥርዓት ተሰጥቷቸዋል። ሥነ ምግባራዊ እና ሥነ ሥርዓታዊ። አንደኛዉ ዓለምን የፈጠረውን ሕያው እግዚአብሔርን ለማሰብ ወደ ፍጥረት እየጠቆመ፣ የይገባኛል ጥያቄው በሁሉም ወቅቶች በሰዎች ላይ የሚፈጸም፣ እና ለዘላለም እና ለዘላለም የሚኖረው ሲሆን ሌላው፣ የሰው ልጅ የሥነ ምግባር ህግን በመተላለፉ ምክንያት የተሰጠው መታዘዝ፣ መስዋዕቶችን እና መባዎችን ያካተተ መታዘዝ የወደፊቱን ቤዛነት የሚያመላክተዉ ነዉ። እያንዳንዳቸው ግልጽና አንዳቸዉ ከአንዳቸዉ የተለዩ ናቸው።"–The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 6, p. 1094.

**ለ. ሊመጣ ያለውን የእግዚአብሔር በግ መሥዋዕትን ለማስረዳት (እንደ ጥላ) የእንስሳት መሥዋዕት ለጥንቶቹ ዕብራውያን ተሰጥቷል፣ ከዚህ ምን ነጥብ እንረዳለን? ዕብራውያን 10:2–4፣ 6**

ክርስቶስ ራሱ የአይሁድ የአምልኮ ሥርዓት ጀማሪ ነበር፣ ለዚያም በአይነትና በምልክት መንፈሳዊና ሰማያዊ ነገሮች ጥላ ነበሩ። ብዙዎች የእነዚህን መስዋዕቶች እውነተኛ ጠቀሜታ ረስተዋል፤ በክርስቶስ ብቻ የኃጢአት ስርየት እንዳለ ታላቁ እውነት ጠፋባቸው። የመሥዋዕቱ መብዛት፣ የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን ሊያስወግድ አልቻለም።"–Ibid., vol. 7, p. 933.

**ሐ. ከኃጢአት ጥፋተኝነት ለማንጻት ኃይል ያለው ምንድን ነው? 1ኛ ዮሐንስ 1፡7**

በእያንዳንዱ መስዋዕት ውስጥ ትምህርት ተካቷል፣ በእያንዳንዱ ሥነ ሥርዓት ዉስጥም አጽንኦት ተሰጥቶታል። . . . ይህም የኃጢአት ስርየት የሚያስገኘዉ የክርስቶስ ደም ብቻ መሆኑ ነው።"–Ibid.

የየሱስ ክርስቶስ ለሰው ቤዛነት መሞቱ መጋረጃውን ያነሳል እና የብርሃን ጎርፍን ከመቶ አመታት በፊት በነበረዉ በአጠቃላይ የአይሁድ የሃይማኖት ተቋም ላይ ያንጸባርቃል። ያለ ክርስቶስ ሞት ይህ ሁሉ ሥርዓት ከንቱ ነበር። አይሁዶች ክርስቶስን ይቃወማሉ፣ ስለዚህም ሁሉም የሃይማኖታቸው ስርዓታቸው ለእነርሱ ግልጽ ያልሆነ፣ የማይገለጽና እርግጠኛ ያልሆነ ነው። ጥላ ያልነበረውን ነገር ግን እንደ አምላክ ዙፋን የጸና እውነት የሆነውን አስርቱ ትእዛዛት ህግ እንደማድረግ ባለቤቱን ወይም ዋናዉን ላገኙት ጥላ ለነበሩት ሥነ ሥርዓቶች ትልቅ ቦታ ይሰጣሉ።"–Ibid., vol. 6, p. 1097.

## 3. የክብረ በዓል ስርዓት

### ሀ. በዚህ መንገድ የእንስሳትን መሥዋዕት ካቀረቡት መካከል ማን ነበር? ዘፍጥረት 3:21፣ 24፤ 4:2–4፤ ዕብራውያን 11፡4

*የሰዉ ልጅ የኃጢአት መስዋዕት እንዲያቀርብ በእግዚአብሔር የተሰጠዉ ድንጋጌ ሰበአዊዉ ፍጡር መተላለፉን ሁል ጊዜ በማስታወስና በደለኝነቱን በማመን ቃል ለተገባዉ አዳኝ በታማኝነት የኃጢአት ኑዛዜ እንዲያቀርቡ ታስቦ ነዉ። ሰዎች መስዋዕት እንዲያቀርቡ የተጠየቁበት ምክንያት ኃጢአት ሞትን ለማስከተሉ አጽንኦት ለመስጠት ነበር። አዳም የመጀመሪያዉን መስዋዕት ሲያቀርብ ያ ሥርዓት ለእርሱ በእጅጉ አስጨናቂና ስቃይ የበዛበት ነበር። እግዚአብሔር ብቻ ሊሰጥ የሚችለዉን ሕይወት ለማጥፋት እጁን መሰንዘር የነበረበት አዳም ሞትን ሲመለከት የመጀመሪያዉ ነበር። እርሱ ለእግዚአብሔር ታማኝ ቢሆን ኖሮ በሰዉም ሆነ በእንስሳት ሞት ባልደረሰ እንደነበረ አወቀ። ጥፋት ያልነበረበትን እንስሳ ሲያርድ፤ የእርሱ ኃጢአት እንከን የሌለበትን የእግዚአብሔርን ልጅ ደም የግድ ማፍሰስ እንዳለበት ሲያስብ ሰዉነቱ ራደ። የእግዚአብሔርን የከበረ ልጅ ሞት የጠየቀ ትዕይንት የመተላለፉን ግዝፈት ይበልጥ ግልጽ አድርጎ አሳየዉ። ከዚያም በደለኛዉን ለማዳን ሲል እንዲህ ያለዉን መቀጮ ለመክፈል ፈቃደኛ በሆነዉ ዘላለማዊ ቸር አምላክ ማንነት በእጅጉ ተደነቀ። በድቅድቅና አስፈሪዉ የወደፊት ሁናቴ ላይ የተስፋ ኮከብ ፈነጠቀለት። በኃዘን የቀረዘዘ ማንነቱም መረጋጋት አገኘ።”*–አበዉና ነቢያት፣ ገጽ. 66(1)

### ለ. ሰዎች በሲና ተራራ ላይ የተሰጠውን የመዳን እቅድ ስላልተረዱ በኋላ ምን ዓይነት ሥርዓት ተፈጠረ? ዘጸአት 25፡8

### ሐ. ደም ማፍሰስ ለምን አስፈለገ? ዕብራውያን 9:22 የመሥዋዕቱ በግ ምልክት ምን ነበር? 1ኛ ቆሮንቶስ 5:7፤ 1ኛ ጴጥሮስ 1:19፤ የዮሐንስ ወንጌል 1፡29

*ሰሚዎቹን በሥነ ሥርዓት ሕግ ዓይነቶች እና ጥላዎች ለክርስቶስ - ወደ ስቅለቱ፣ ወደ ክህነቱ እና ወደ መቅደሱ አገልግሎቱ- ጥላውን ወደ ኋላ ወደ አይሁድ ዘመን የጣለውን ታላቁን ነገር አወረደ። እሱ፣ እንደ መሲህ፣ የሁሉም መስዋዕቶች ምሳሌ ነው። ሐዋርያው እንደ ትንቢቶቹና አይሁዳውያን እንደሚጠብቁት ሁሉ መሲሑ የአብርሃምና የዳዊት ዘር እንደሚሆን አሳይቷል። ከዚያም በንጉሣዊ መዝሙረኛው በኩል ከታላቁ አባት ከአብርሃም ዘር ተገኘ። በቅዱሳን ነቢያት እንደተመሰከረለት የተስፋው መሲህ ባሕርይና ሥራ ምን እንደሚሆን ከቅዱሳት መጻሕፍት አረጋግጧል፣ እንዲሁም በምድር ላይ ያለውን አቀባበል አረጋግጧል። ከዚያም እነዚህ ትንቢቶች በየሱስ ሕይወት፣ አገልግሎት እና ሞት ፍጻሜያቸውን እንዳገኙ አሳይቷል፣ ስለዚህም እርሱ በእርግጥ የዓለም ቤዛ እንደሆነ አሳይቷል።”*–Sketches From the Life of Paul, pp. 103, 104.

4. **ለምን ጠፋ (ቀረ)?**

**ሀ. ሥርዓቱ ያለማቋረጥ በቤተ መቅደሱ ውስጥ እስካለ ድረስ፣ እስራኤላውያን የመዳን ተስፋቸውን በምን አመኑ? ኢሳይያስ 1:10-15**

*የእግዚአብሔር ልጅ ሁሉንም አሠራሮች የሚሸፍን የታላቁ የቤዛነት እቅድ ማእከል ነው። እርሱም ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የታረደው በግ ነው። በሁሉም የሰው ልጆች የፈተና ዘመን ውስጥ የወደቁትን የአዳም ወንዶችና ሴቶች ልጆች ቤዛ ነው። ... ክርስቶስ ጥላውን ወደ ቀደመው ዘመን የሚጥል ንጥረ ነገር ወይም አካል ነው። ክርስቶስ ሲሞት ጥላው ቀረ። በክርስቶስ ሞት ዓይነተኛ ሥርዓት ተወግዷል፣ ነገር ግን በመጣሱ የመዳንን ዕቅድ አስፈላጊ ያደረገው የእግዚአብሔር ሕግ ከፍ ከፍ ያለና የተከበረ ሆነ። ወንጌል ለአዳም፣ ለኖህ፣ ለአብርሃም እና ለሙሴ ታላቅ ደስታ የምስራች ነበር፤ የሚመጣውን አዳኝ አስቀድሞ አሳይቷቸዋልና።"*–The Signs of the Times, February 20, 1893.

*"የሩሳሌም የአይሁዶች ዋና ከተማ ሲሆን ታላቁ ግለኝነት ወይም ለብቻ መሆንና አክራርነት መሠረት ነበር፡፡ የአይሁድ ክርስትያኖች ቤተ መቅደሱን በየዕለት ኑሯቸዉ ስለሚያዩት በተፈጥሮ አዕምሯቸዉ አይሁድ እንደ ሕዝብ ወደሚያገኛቸዉ ልማዳዊ ልዩ መብቶች ይመለስ ነበር፡፡ የክርስትያን ቤተክርስትያን ከእነዚህ ከአይሁድ ሥርዓቶችና ልማዶች እየተለየችና በአዲሱ ኃይማኖት ብርሃን ሲታዩ እነርሱ በተለምዶ በአይሁድ ልማዶች የሚገኝ ቅድስና ስለሚደበዝዝባቸዉ፣ ለዚህ ለዉጥ ጉልህ ሚና ከተጫወተዉ ጳዉሎስ ላይ ቁጣቸዉ ነደደ፡፡ ... አንዳንዶቹ ለአይሁድ ሥርዓት የሚቀኑ ነበሩ።"*— Sketches From the Life of Paul, p. 71.

**ለ. ከመሥዋዕቱ ሁሉ ይልቅ፣ እግዚአብሔር የሚፈልገው ምን ነበር? ኢሳይያስ 1:16–18፤ መዝሙረ ዳዊት 51:17-19**

**ሐ. የመሥዋዕቱ ሥርዓት ማድረግ ያልቻለውን በየሱስ ክርስቶስ ደም የመዳን ዕቅድ ምን ያመጣል? የሐዋርያት ሥራ 4:12፤ ዕብራውያን 7:28፣ 19**

*የበለጠ ግልጽና የከበረ ብርሃን አሁን በክርስቲያኑ ላይ ይበራል። ከክርስቶስ መምጣት በፊት የኖሩት በእምነት የእርሱን መምጣት በጉጉት ይጠባበቁ ነበር፣ ነገር ግን በእነሱ በእምነት ልንይዘው የሚገባው ለእኛ ማረጋገጫ ነው። በነቢያት እንደተነገረው ክርስቶስ እንደ መጣ እናውቃለንና። የጥንት ሰዎች በመሥዋዕታቸው የተመሰለውን አዳኝ እንደሚመጣ ማመን ወደ ምድር በመጣውና መስዋዕታችንን በሞተልን በቤዛችን ላይ እምነት እንዲኖረን አስፈላጊ ነው።*The Signs of the Times, February 20, 1893.

**ሐሙስ** **የካቲት 16**

5. **ዛሬ የሥነ ሥርዓት ሕግ ያስፈልገናለን?**

**ሀ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተመዘገቡት የሥርዓት ሕጎች ለምን አሉን? 2ኛ ጢሞቴዎስ 3:16**

**ለ. የሱስ ዛሬ በሰማይ ምን እያደረገ ነው? ዕብራውያን 8:1-5፤ 3፡1።**

**ሐ. ይህ አዲስ ሥርዓት በሰማይ በንቃት እንደሚሠራ ካወቅን ምን ማድረግ አለብን? ዕብራውያን 4፡14-16**

ባለማወቅ እስካሁን እንደ ጠቃሚ ነገር በማሰብ ከተጣበቁበት ሥርዓቶችና በዓላት ራሳቸዉን እንዲያላቅቁና ወንጌል የመቀበል ሕደት ምንም ዓይነት ጉልበት የታከለበት እንዳይሆንባቸዉ በሚያስፈልጋቸዉ ጊዜ ሁሉ እንድጠቅማቸዉ ይህንን ትዕዛዝ ለደቀ መዛሙርት መተዉ የክርስቶስ ምኞት ነበር፡፡ እነዚያን ሥርዓቶች ማስቀጠል ጀሆቫን መሳደብ ነዉ፡፡"–The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 5, pp. 1139, 1140.

የመስቀሉ መልእክተኞች በንቃትና በጸሎት ራሳቸውን ያስታጥቁ እንዲሁም በእምነትና በድፍረት ወደፊት ሁልጊዜ በየሱስ ስም እየሰሩ መሄድ አለባቸው። የብሉይ ኪዳን ዘመን መሥዋዕቶች ሁሉ ያተኮሩበትና በሥርየት መስዋዕቱ የእግዚአብሔርን ሕግ ተላላፊዎች ሰላምና ይቅርታ የሚያገኙበት በሰማያዊው መቅደስ የሰው ዘር አማላጅ የሆነዉን ክርስቶስን ከፍ ከፍ ማድረግ አለባቸው።"–The Acts of the Apostles, p. 230

**አርብ** **የካቲት 17**

**የግል የግምገማ ጥያቄዎች**

1. የሰባተኛው ቀን ሰንበት በብሉይ ኪዳን ጥላዎች ውስጥ እንዳልተካተቱ እንዴት እናውቃለን?

2. የሁለቱ ሕጎች ልዩ ገጽታዎች ምንድን ናቸው–የሥነ ምግባርና የሥነ ሥርዓት?

3. ሞት በሙብዛቱ ምክንያት እንስሳ ሲሞት ምን ዓይነት ዝንባሌ አጥተናል?

4. በቤተ መቅደሱ አቅራቢያ የሚኖሩ አይሁዳውያን ሥርዓቱ መጠናቀቁን እንዳይገነዘቡ ያደረጋቸዉ ነገር ምንድን ነው?

5. ዛሬ የቤተ መቅደስን አገልግሎት በማጥናታችን ምን ጥቅም እናገኛለን?

## ሰንበት፣ የካቲት 25፣ 2015

## የመጀመሪያ ሰንበት ሥጦታ በሰሜን ህንድ ዩኒየን በፓታንኮት ውስጥ ላለው የጸሎት ቤት

*ፓታንኮት በህንድ ፑንጃብ ግዛት ውስጥ ያለ ከተማ ነው። በምዕራብ ከፓኪስታን ጋር ስለምዋሰን የፑንጃብ፣ የሂማካል ፕራዴሽ እና የጃሙና ካሽሚር ግዛቶች የጉዞ ማዕከል ነው።*

*የተሃድሶው መልእክት እ.ኤ.አ. በ2015 እዚህ ደርሷል፣ እና አባላታችን ባለፉት አመታት አድጓል። በሰንበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርታችን ስርጭት ምክንያት፣ ብዙ ውድ አዳዲስ ነፍሳት የወቅቱን እውነት ለማወቅ በጉጉት ይፈልጋሉ።*

*እ.ኤ.አ. በ2011 የፓታንኮት ከተማና አካባቢ 159,909 ህዝብ ነበራት እንዲሁም ከነዚህም ማንበብና መጻፍ የሚችሉት 88.71% ናቸዉ። በሁለቱም በኩል በሺቫሊክ ክልል (የሂማላያስ ግርጌ ክፍል) እና በቻኪ ወንዝ ተከቧል። በፓታንኮት አቅራቢያ ያሉ ታዋቂ ቦታዎች ሻህፑር ካንዲ ለቱሪስቶች የተንጠለጠለ ማረፊያ ቤት እና ራንጂት ሳጋር ግድብ፣ በእስያ ከፍተኛው የስበት ኃይል (gravity dam) ግድብን ያካትታሉ። በአካባቢው ከሚገኙት ኢንዱስትሪዎች መካከል ወተት፣ ስንዴ፣ ሩዝ፣ ጨርቃጨርቅ፣ የልብስ ስፌት ማሽኖች፣ የስፖርት ዕቃዎች፣ ስኳር፣ ስታርች፣ ማዳበሪያ፣ ብስክሌት፣ ሳይንሳዊ መሣሪያዎች፣ የኤሌክትሪክ ዕቃዎች፣ የማሽን መሣሪያዎች እና የጥድ ዘይት ማምረቻ ይገኙበታል።*

*በፓታንኮት ውስጥ ያሉት ሃይማኖቶች ሂንዱይዝም 88.89%፣ ሲክሂዝም 8.01%፣ እና ክርስትና 1.73%፣ በመቀጠል እስልምና እና ሌሎች ሃይማኖቶች ናቸዉ።*

*በካንግራና ዳልሆውዚ በሚያማምሩ ተራሮች ግርጌ ላይ የምትገኝ፣ ቻኪ ወንዝ በአቅራቢያው የሚፈስስበት፣ ይህች ከተማ ብዙውን ጊዜ ወደ ጃሙ እና ካሽሚር፣ ዳልሃውዚ፣ ቻምባ፣ ካንግራ፣ ዳራምሻላ፣ ማክሊዮድጋንጅ፣ ጆዋላጂ፣ ቺንትፑርኒ እና ተጨማሪ ወደ ሂማላያ ተራሮች ከመሄዳቸዉ በፊት ለእንግዶች እንደ ማረፊያ ቦታ ትጠቀማለች። ብዙ የአጎራባች ክልሎች የገጠር ተማሪዎች ለትምህርት ወደ ፓታንኮት ይመጣሉ።*

*ፓታንኮት በባቡርና በመንገድ ከተቀረው የሕንድ ክፍል ጋር በጥሩ ሁኔታ የተገናኘ ነው፣ እና በፑንጃብ፣ በሂማሻል ፕራዴሽ፣ በዴሊ፣ በሃሪያና፣ በጃሙ እና በካሽሚር ውስጥ ከሚገኙ ሌሎች ከተሞች ጋር በሰፊው የግልና የህዝብ ዘርፍ የአውቶቡስ አገልግሎት የተገናኘ ነው። አስፈላጊ መዳረሻዎች ዴሊ፣ ማናሊ ቻንዲጋርህ፣ ጃሙ፣ ዳራምሻላ፣ ዳልሆውዚ እና አምሪሳር ይገኙበታል።*

*ስለዚህ፣ ልክ በየሱስ ዘመን እንደነበረው ቅፍርናሆም፣ ፓታንኮት ለመንገደኞች እንደ መስቀለኛ መንገድ ሆኖ ያገለግላል - እናም ወንጌልን ለመስበክ የሚያችል ሁነኛ አቅም አላት! እኛ መሬት የምንገዛበትና ቤተክርስቲያን የምንገነባበት የራሳችን ሃብት የለንም። ስለዚህ በፓታንኮት ህንድ ለጌታ ሃውልት ለመስራት በትህትና ስጦታችሁን እንድትልኩልን የወንድሞቻችንን እና እህቶቻችንን ድጋፍ እንፈልጋለን። “እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳል።” (2ኛ ቆሮንቶስ 9፡ 7) ስለዚህ በዚህ ተስፋ ጌታችን የሱስ እያንዳንዳችሁን በታላቅ በረከት እንዲባርክ እንጸልያለን።*

*ወንድሞችና እህቶች ከፓታንኮት ቤተክርስቲያን*

## ብንናዘዝ

የመታሰቢያ ጥቅስ፡- “በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።” (1ኛ ዮሐንስ 1፡9)።

ኃጢአታችሁን ይቅር ለሚለው ለእግዚአብሔር ተናዘዙ፤ እንዲሁም እርስ በርሳችሁ ተናዘዙ።”–Steps to Christ, p. 37.

ለንባብ የተመረጠዉ፡ ወደ ክርስቶስ የሚመራ መንገድ፣ ገጽ 23—35፣ 37—41፤Testimonies for the Church, vol. 5, pp. 635—650

**እሁድ የካቲት 19**

1. **በአዲሱም በአሮጌዉም (በብሉይ) ተመሳሳይ ዘዴ**

**ሀ. እግዚአብሔር ስለማይለወጥ (ሚልክያስ 3፡6፣ ዕብራውያን 13፡8) የፈጠረውን ነፍስ ሁሉ መዳን በተመለከተ ስላለው ፍላጎት ምን ልንገነዘብ ይገባናል? መዝሙረ ዳዊት 78:38፤ ሕዝቅኤል 18:32፤ 2ኛ ጴጥሮስ 3፡9**

[እግዚአብሔር] ማንም እንዲጠፋ አይፈልግም፣ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ ሲመጡ ማየትን ይናፍቃል።... ነጻ ይወጡ ዘንድ የፍትህ ሰይፍ በክርስቶስ ላይ ወደቀ። እነርሱ በሕይወት ይኖሩ ዘንድ እርሱ ሞተ።”–God’s Amazing Grace, p. 326

**ለ. ሰሎሞን ባሠራው ቤተ መቅደስ ምርቃት ወቅት፣ እግዚአብሔር ይቅር ለማለት ፈቃደኛ መሆኑን የሚገልጸው የትኛው ታላቅ የብሉይ ኪዳን ክፍል ነው? 2ኛ ዜና 7፡12-14 ይህ በአዲስ ኪዳን እንዴት ተስተጋብቷል? 1ኛ ዮሐንስ 1:9፤ 2፡1።**

የግል ባሕርይ ኃጢአት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው ብቸኛ አማላጅ ለሆነው ለክርስቶስ መናዘዝ ያስፈልጋል። . . . ኃጢአት ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ የሚፈጸም በደል ነው፣ እና በክርስቶስ በኩል ለእርሱ መናዘዝ አለብን። እያንዳንዱ ግልጽ ኃጢአት በግልጽ የተናዘዘ መሆን አለበት። በባልንጀራ ላይ የተፈፀመ ስህተት ከተበደለው ሰው ጋር በመሆን መስተካከል አለበት። ጤናን የሚፈልጉ ሁሉ በክፉ ንግግር ጥፋተኛ ከሆኑ፣ በቤት፣ በጎረቤት ወይም በቤተ ክርስቲያን አለመግባባትን ከዘሩ፣ መለያየትንና መቃቃርን ካደረጉ፣ በማናቸውም የተሳሳተ አሠራር ሌሎችን ኃጢአት እንዲሠሩ ካደረጉ፣ እነዚህ ነገሮች በእግዚአብሔር ፊትና በተበደሉ ሰዎች ፊት መናዘዝ አለባቸው።”–Gospel Workers, pp. 216, 217.

## 2. ይቅርታን ለመቀበል የመጀመሪያው እርምጃ

### ሀ. የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በልብ ላይ እምነትን ማምጣት እንደሆነ (ዮሐንስ 16፡8) የመጀመሪያው ምላሽ ምን መሆን አለበት? መዝሙረ ዳዊት 86:5

*አዕምሮና ልብ በኃጢአት የተሞሉ መሆናቸዉን ያምናሉ (ይቀበላሉ)። ኃጢአተኛዉ የእግዚአብሔርን ጻዲቅነት ስለሚያስተዉልና ልብን ከሚመረምረዉ አምላክ ፊት ለመቅረብ የኃጢአተኛነትና የመጉደፍ ስሜት ስለሚኖረዉ በአምላክ ፊት ለመቅረብ ፍርሃት ያድርበታል። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፍቅር፣ የቅድሰናዉን ዉበትና ንጽህና ባስተዋለ ጊዜ ከኃጢአቱ ለመንጻትና ከሰማይ ጋር ዳግም አንድ ለመሆን ይናፍቃል።"–ወደ ክርስቶስ የሚመራ መንገድ፣ ገጽ*. 22.

*በመለኮታዊ ጸጋ በልብ ተጽዕኖ የሚመነጨው ንስሐ ኃጢአትን መናዘዝንና መተውን ያስከትላል። ሐዋርያው በቆሮንቶስ አማኞች ሕይወት ውስጥ ታይቷል ብሎ የተናገረባቸው ፍሬዎች እንደዚህ ያሉ ነበሩ።"*–The Acts of the Apostles, p. 324.

### ለ. በጴንጤቆስጤ ቀን ምሳሌውን ስንመለከት፣ ኃጢአት መሥራቱን ለመረዳት ኅሊና ሲነቃ ምን ይሆናል? የሐዋርያት ሥራ 2:36፣ 37

*ኃጢያትን በመናዘዝና በመተው፣ ከልብ በመጸለይና ራሳቸውን ለእግዚአብሔር በመቀደስ ነበር፣ የቀደሙት ደቀ መዛሙርት በጰንጠቆስጤ ቀን ለመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ የተዘጋጁት። ይኸው ሥራ፣ በከፍተኛ ደረጃ፣ አሁን መሠራት አለበት።"*–Testimonies to Ministers, p. 507.

### ሐ. ወደ ሕይወት ለውጥ የሚመራውን የጥፋተኝነት ውሳኔ እንዴት ልንገልጸው እንችላለን? የሐዋርያት ሥራ 2፡38

*"[እስራኤላውያን] እውነተኛ ሰላም ከማግኘታቸው በፊት ጥፋተኛ የሆኑበትን የሠሩትን ኃጢአት እንዲያዩና እንዲናዘዙ መመራት አለባቸው።"–የሃይማኖት አባቶችና ነቢያት፣ ገጽ*. 614.

*እውነተኛ ኑዛዜ ሁል ጊዜ የአንድ የተወሰነ ባሕርይ ነው፣ እና ልዩ ኃጢአቶችን ይቀበላል። ምናልባት በአምላክ ፊት ብቻ መቅረብ ያለባቸዉ፣ ወይም በእነርሱ ምክንያት ጉዳት በደረሰባቸው ሰዎች ፊት መናዘዝ ያለባቸው በደል ወይም በጉባኤው ውስጥ መታወቅ ያለበት አጠቃላይ ዓይነት ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን ጥፋተኛ የሆናችሁበትን ኃጢያት እውቅና በመስጠት ሁሉም ኑዛዜዎች ግልጽና እስከ ነጥብ ድረስ መሆን አለባቸው።"*–Testimonies for the Church, vol. 5, p. 639.

## 3. የሐሰተኛ ንስሐ ምሳሌ

### ሀ. ይሁዳ ክርስቶስን ለካህናት አለቆች አሳልፎ በመስጠቱ ንስሐ ገብቷልን? (ማቴዎስ 26፡14–16፣ 47–49) ለምን ወይም ለምን አይሆንም? ማቴዎስ 27:3፣ 4

*ከዚያ በኋላ ይሁዳ በየሱስ እግር ስር ወድቆ የሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን እንደሚያዉቅ በመግለጽ ራሱን እንዲያድን ለመነዉ። አዳኛችን ይሁዳ ንስሃ እንዳልገባ ቢያዉቅም አልገሰጸዉም። ይሁዳ የተናዘዘዉ የእስራኤል ቅዱስ የተባለዉን ጌታ ስላካደና ነዉር የሌለበትን የእግዚብሔርን ልጅ አሳልፎ ስለሰጠ ጥልቅ ሃዘን ተሰምቶት ሳይሆን የሕሊና ወቀሳ ስላስገደደዉና የሚደርስበት ፍርድ ስለታየዉ ነዉ። ቢሆንም የሱስ ይሁዳን በርህራሄ ዓይን እየተመለከተ ለዚህ ነዉ ወደ ዓለም የመጣሁት አለ እንጂ አላወገዘዉም።”–የዘመናት ምኞት፣ ገጽ*. 762.

*ኃጢያት ግብረገባዊዉን አመለካከት ሙት በሚያደርገዉ ጊዜ በደለኛዉ የባሕሪዉን ጉድለት ለይቶ መመለከት አይችልም ወይም የሠራዉ ክፋት ምን ያህል ግዙፍ እንደሆነ መገንዘብ ይቸግረዋል። ጥፋተኝነቱን ሊያመላክተዉ ለሚችለዉ ለመንፈስ ቅዱስ ኃይል መንገድ ካልከፈተ በቀር በከፊል ታዉሮ ኃጢአቱን ሳያይ ይቀራል። የእንዲህ ዓይነቱ ግለሰብ ንስሃ ከልብ የመነጨና ፅኑ ዓላማ ላይ የተመሠረተ ባለመሆኑ “ይህ ባይደርስብኝ ኖሮ እንዲህ ባለደረግኩ ነበር” በማለት ለሠራዉ ስህተትና ለኃጢአቱ ሁሉ ምክንያት ይደረድራል።”–ወደ ክርስቶስ የሚመራ መንገድ፣ ገጽ*. 37

*በእምነትና በጸሎት ሁሉም የወንጌልን መስፈርቶች ሊያሟሉ ይችላሉ። ማንም ሕግን ለመተላለፍ ሊገደድ አይችልም። የግል ፈቃዱን በመጀመሪያ ማግኘት አለበት፤ ስሜት በምክንያት ላይ ከመግዛቱ ወይም በሕሊና ላይ በደል ከመሸነፉ በፊት ነፍስ የኃጢአተኛውን ተግባር ማቀድ አለባት። ፈተና ቢበረታም ለኃጢአት ሰበብ አይሆንም።”*–Testimonies for the Church, vol. 5, p. 177.

### ለ. ይህ ወደ ዘላለማዊ ሕይወት የሚመራ የንስሐ ዓይነት መሆኑን ወይም አለመሆኑን አስረዳ። ማቴዎስ 27:5፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 7፡8-11

*ብዙዎች እራሳቸውን በማታለል ውስጥ ናቸው፣ እና ጌታ ምንም ጉዳይ ወደሌለበት ነገር ውስጥ ገብተዋል። ነገር ግን መከተል ያለብን ብቸኛው አስተማማኝ መንገድ የጌታን ቃል መታዘዝ ነው። ብዙዎች ይህን ከማድረግ ይልቅ አስደናቂ ነገሮችን ለመሥራት ሐሳብ ያቀርባሉ። ራሳቸውን ባዶ አድርገው ለእግዚአብሔር ልብን፣ አእምሮንና ፈቃድን ከመገዛትና በሚፈጥረውና በሚያጠፋው ኃይል ለመቀረጽ ከመገዛት ይልቅ ለወደፊት ትልቅ ነገርን ማቀድ ይቀላቸዋል። ወጣቶቹ በጸሎትና ቅዱሳን ጽሑፎችን በመመርመር ውስጣዊ ምኞታቸውን በትችት ይመርምሩ፤ እንዲሁም የራሳቸው ፈቃድና ዝንባሌ ከአምላክ መሥፈርቶች የሚያርቃቸዉ እንደሆነ ይመለከቱ።”*–The Youth’s Instructor, March 23, 1893.

## 4. የእውነተኛ ንስሐ ምሳሌ (መዝሙረ ዳዊት 51)

**ሀ. ኃጢአታችንን በእግዚአብሔር ፊት አምነን ሳንናገር ዝም ካልን ምን ይሆናል? መዝሙረ ዳዊት 32:3፣ 4**

**ለ. ነቢዩ ናታን የዳዊትን ኃጢአት ከገለጸ በኋላ (2ኛ ሳሙ. 12፡1-12) ንጉሡ ምን ምላሽ ሰጠ? 2ኛ ሳሙኤል 12፡ 13**

*የነቢዩ ተግሣጽ የዳዊትን ልብ ነክቶታል፤ ሕሊናዉ ተነሳሳ፤ የጥፋቱ ግዝፈት ጎልቶ ታየዉ። ነፍሱ በንስሐ በእግዚአብሔር ፊት ወደቀች።"– የሃይማኖት አባቶችና ነቢያት፣ ገጽ.* 722.

*የዳዊት ንስሐ ጥልቅና ከልብ የጠደረገ ነበር። ወንጀሉን ለማቃለል ምንም ጥረት አላደረገም። ከሚያስፈራዉ ፍርድ ለማምለጥ ምኞት ያልነበረዉ ዳዊት የተላለፈዉን አምላካዊ ሕግ ስፋትና ጥልቀት ተመልክቷል። የነፍሱን መቆሸሽ አስተዉሏል፣ ኃጢአቱንም ተጸይፏል። የጸለየዉ መህረት ለማግኘት ብቻ ሳይሆን የልብ ንጽህናን ለማግኘት ጭምር ነበር። በትግሉ ተስፋ ያልቆረጠዉ ዳዊት፤ እግዚአብሔር ለተጸጸቱ ኃጢአተኞች በገባዉ ቃል መሠረት ይቅር መባሉንና በጌታ ፊት ተቀባይነት ማግኘቱን አረጋግጧል።"–ኢ.ቢ.ድ፣ ገጽ.* 725.

**ሐ. ይህ ደግሞ በቢታንያ በስምዖን ልብ ውስጥ እንዴት ሆነ? ሉቃስ 7፡40-48 ሰላምና ዕርቅ ሊመጣ የሚችለው በምን መንገድ ብቻ ነው? መዝሙረ ዳዊት 32:5፤ ኤርምያስ 3:13፤ 1ኛ ዮሐንስ 1፡9**

*ነቢዩ ናታን የዳዊትን ኃጢአት በምሳሌ እንዳስረዳዉ ሁሉ እንዲሁም ክርስቶስ ስምዖን እንዲረዳዉ የፈለገዉን መልዕክት በምሳሌ ነገረዉ። የሱስ በራስ ላይ የመፍረድን ኃላፊነት በአስተናጋጁ ላይ ጣለበት። ስምዖን አሁን በንቀት ዓይን የሚያያትን ሴት ኃጢአት እንድትሠራ አድርጓት ነበር። ከፍተኛ የሆነ በደል አድርሶባታል። በምሳሌዉ የተጠቀሱት ሁለት ባለዕዳዎች የስምዖንና የሴትዮዋ ምሳሌዎች ናቸዉ። የሱስ ያን ምሳሌ የተናገረዉ ሁለቱ ተበዳሪዎች ሊከፈሉ የማይችሉት ዉለታ እንደነበረባቸዉ ለማሳየት እንጂ የግዴታቸዉን (የዕዳቸዉን) ልዩነት ለማሳየት አልነበረም። ስምዖን ከማርያም የተሸልሁ ጻዲቅ ነኝ ይል ስለነበረ የሱስ የእርሱ ኃጢአት ምን ያህል ትልቅ እንደነበረ ሊያሳየዉ ፈለገ። አምስት መቶ ብር ከሃምሳ የሚበልጠዉን ያህል የስምዖን ኃጢአት ከማሪያም ኃጢአት እንደሚበልጥ ሊያስረዳዉ አሰበ።*

*ስምዖን ከድሮ የተለየ አኳኋን ማየት ጀመረ።. . . ከእርሱ በላይ የሆነ ጌታ ፊት እንዳለ በተገነዘበ ጊዜ ሐፍረት ተሰማዉ። . . . የሱስ በእንግዶቹ ፊት በይፋ ስላልዘለፈዉ ስምዖን በየሱስ ደግነት ልቡ ተነካ። . . . ትዕግሥት በተሞላበት መንገድ የተሰጠዉ ምክር ስህተቱን እንዲያምን አደረገዉ። ለጌታ የሚከፍለዉ ዕዳ ምን ያህል ብዙ እንደሆነ አወቀ። ትዕቢቱ ወደ ትሕትና ተለዉጦ ንስሃ ስለገባ እብሪተኛዉ ፈሪሳዊ አንገቱን የደፋና ሕይወቱን ለመሰዋት የተዘጋጀ ደቀ መዝሙር ሆነ።"– የዘመናት ምኞት፣ ገጽ* 583—584

**ሐሙስ** **የካቲት 23**

5. **የይቅርታ ስጦታ**

**ሀ. ከባድ በደል የበደልን ከሆነ ከኃጢአታችን ወደ ልባዊና እውነተኛ ሐዘን የምንመራው እንዴት ነው? ሥራ 5:30፣ 31፤ ኢሳይያስ 55:6፣ 7፤ ዕብራውያን 4፡ 16**

እንደዚህ ዓይነቱን ንስሐ ማንም ከራሱ ሊያመነጨዉ አይችልም። ነገር ግን ወደ ላይ ከፍ ብሎ ባረገዉና ለሰዎች ስጦታን በሰጠዉ በክርስቶስ ብቻ ነዉ የሚገኘዉ።"–ወደ ክርስቶስ የሚመራ መንገድ፣ ገጽ. 24

ሰዉ ኃጢአተኛነቱን ማየት ከቻለ ራሱን እስኪያስተካክል ድረስ መቆየት የለበትም። "ወደ ክርስቶስ ለመምጣት ብቁ አይደለንም" ብለዉ የሚያስቡ ስንቶች ናቸዉ? ለመሆኑ እርስዎ በራስዎ ጥረት የተሻሉ ሰዉ መሆን እንደሚችሉ አድርገዉ ያስባሉ? "በውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዝንጉርጉርነትን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን?" በዚያን ጊዜ ክፋትን የለመዳችሁ እናንተ ደግሞ በጎ ለማድረግ አትችሉም። ኤር 13፡23። ለእኛ እርዳታ የሚገኘዉ ከእግዚአብሔር ብቻ ነዉ። ወደ ክርስቶስ ለመምጣት ጠንከር ያለ አሳማኝ ነገር እስክናገኝ፣ የተሻለ ዕድል እስክገጥመን ወይም በዉስጣችን ቅዱስ ስሜት እስክሰማን ድረስ መጠበቅ የለብንም። እኛ በራሳችን ልናደርግ የምንችለዉ አንዳች ነገር ባለመኖሩ፤ ከእኛ የሚጠበቀዉ ባለንበት ሁኔታ ወደ ክርስቶስ መምጣት ብቻ ነዉ።–ወደ ክርስቶስ የሚመራ መንገድ፣ ገጽ 29

**ለ. ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ለእኛና በእኛ ውስጥ እንዲደረግ ምን ያህል ተጠንቅቀን መጠበቅ እንችላለን? ዕብራውያን 12:12፤ ፊልጵስዩስ 1፡ 6**

ንስሐ፣ እንዲሁም ይቅርታ፣ በክርስቶስ በኩል የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። በኃጢአት እንደተፈረደብንና ይቅርታ እንደሚያስፈልገን የሚሰማን በመንፈስ ቅዱስ ተጽእኖ ነው። ይቅርታን የሚያገኙት የተጸጸቱት እንጂ ሌሎች አይደሉም፤ ልብን እንድጸጸት የሚያደርግ ግን የእግዚአብሔር ጸጋ ነው። እርሱ ሁሉንም ድክመቶቻችንንና ጉድለቶቻችንን ያውቃል፣ እናም እርሱ ይረዳናል።"–Selected Messages, bk. 1, p. 353

**ሐ. የዚህ ዓይነቱ እውነተኛ ኑዛዜ ውጤቱ ምን ይሆን? ሮሜ 8፡1**

**አርብ** **የካቲት 24**

**የግል የግምገማ ጥያቄዎች**

1. ሰሎሞን በቤተ መቅደሱ ምረቃ ላይ ካቀረበው ጸሎት በግለሰብ ደረጃ ምን እንማራለን?
2. በኋለኛው ዝናብ ኃይል ሥር በአምላክ ሥራ መጠናቀቅ ላይ መካፈል ከፈለግን በቁም ነገር ልንወስዳቸው የሚገቡ እርምጃዎች የትኞቹ ናቸው?
3. ኃጢአታችንን ለእግዚአብሔር መናዘዝ ለምን አስፈለገ? ለኃጢአት ሥራ ምን ያህል ተጠያቂ ነን?
4. አንድ ሰው ጥፋተኛ መሆኑን ለማሳየት ምን ያህል መጠንቀቅ አለብን?
5. ኃጢአተኛ ንስሐ መግባት የሚችለው እንዴት ነው?

## "በእውነትህ ቀድሳቸው"

*የመታሰቢያ ጥቅስ፡-"የጻድቃን መንገድ ግን እንደ ንጋት ብርሃን ነው፥ ሙሉ ቀን እስኪሆንም ድረስ እየተጨመረ ይበራል።"* (ምሳ 4፡18)።

*እራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ስንሰጥና ሙሉ በሙሉ ስናምን የክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻል። ሕሊና ከውግዘት ሊላቀቅ ይችላል። በደሙ ባለ እምነት ሁሉም በክርስቶስ የሱስ ፍፁም ሊሆኑ ይችላሉ። የማይቻሉ ነገሮችን ስላላስተናገድን እግዚአብሔር ይመስገን። እንቀደስ ይሆናል። የአምላክን ሞገስ እናገኝም ይሆናል። መጨነቅ ያለብን ክርስቶስና እግዚአብሔር ስለእኛ ስለሚያስቡት ነገር ሳይሆን እግዚአብሔር ተተኪያችን ስለሆነው ስለ ክርስቶስ ስላለው አመለካከት ነው።"*–Selected Messages, bk. 2, pp. 32, 33

*ለንባብ የተመረጠዉ፡* The Acts of the Apostles, pp. 557—567.

**እሁድ                                                    የካቲት 26**

### 1. መጽደቅ

**ሀ. ኃጢአታችንን ስንናዘዝና ሕይወታችንን ለየሱስ አሳልፈን ስንሰጥ - በክርስቲያናዊ ልምምዳችን መጀመሪያ ላይም ሆነ በእያንዳንዱ ደረጃ - ከእግዚአብሔር ምን እናገኛለን? ሮሜ 3፡24-26**

*አዳም በኃጢአት ከመዉደቁ በፊት ለእግዚአብሔር ሕግ በመታዘዝ ጻዲቅ ባሕርይን ማሳየት ይችል ነበር። ነገር ግን እርሱ ይህን ስላላደረገና ከእርሱ ወድቀትም የተነሳ የእኛ ተፈጥሮ በኃጢአት ስለጎደፈ ራሳንን ልናጸድቅ አልቻልም። ኃጢአተኞች፣ ቅድሰና የጎደለንና በኀጢአት የረከስን እንደመሆናችን፣ ቅዱሱን ሕግ በፍጽምና ልንታዘዘዉ አንችልም። የእግዚአብሔር ሕግ የሚጠይቀዉን ለማሟላት የራሳችን የሆነ ጽድቅ ባይኖረንም ክርስቶስ ግን ማምለጫዉን መንገድ አዘጋጀልን። እርሱ በኖረዉ ምድራዊ ሕይወቱ እኛ በምናልፈበት ፈተናና መከራ ዉስጥ አልፏል። ይሁንና ኃጢአት የሌለበትን ሕይወት ኖረ። ስለዚህም ስለእኛ ሞቶ ኃጢአታችንን ለመዉሰድ ራሱን በመስጠት ጽድቁን አወረሰን። ራሳችሁን ለእርሱ ብትሰጡና እንደ አዳኛችሁ ብትቀበሉት የፈለገዉን ያህል ኃጢአተኛ የነበራችሁ ቢመስላችሁም፤ ስለ ራሱ ሲል እንደ ጽድቅ ይቆጥራችኋል። የክርስቶስ ባሕርይ በእናንተ ምትክ ተቆጥሮ በእግዚአብሔር አብ ፊት ምንም ኃጢአት እንዳልሠራ ሰዉ ሆናችሁ እንድትታዩ ያደርጋችኋል።"– ወደ ክርስቶስ የሚመራ መንገድ፣ ገጽ* 58

**ለ. ይህ ጉዞ የሚቆየው እስከ መቼ ነው? ምሳሌ 4:18፤ ማርቆስ 13:13**

## 2. የክርስትናን ጸጋዎች ማሻሻል

### ሀ. ከይቅርታ/መጽደቅ በተጨማሪ እግዚአብሔር ሊሰጠን የሚፈልገው ሌላ ምንድ ነው? 2ኛ ቆሮንቶስ 7:1፤ ዕብራውያን 6:1፤ ፊልጵስዩስ 3፡12-14

በዮሐንስ ሕይወት ውስጥ እንደሚታየው ዓይነት የባህሪ ለውጥ ከክርስቶስ ጋር የመገናኘት ውጤት ነው። በአንድ ግለሰብ ባህሪ ውስጥ ጉልህ ጉድለቶች ሊኖሩ ይችላሉ፣ ነገር ግን እውነተኛ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር በሚሆንበት ጊዜ፣ የመለኮታዊ ጸጋ ኃይል ይለውጠዋል እና ይቀድሰዋል። የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጨ ሲያይ የሚወደውን እርሱን እስኪመስል ድረስ ከክብር ወደ ክብር ይለወጣል።"–The Acts of the Apostles, p. 559.

ያለ ክርስቶስ ጸጋ፣ ኃጢአተኛው ተስፋ በሌለው ሁኔታ ውስጥ ነው። ለእሱ ምንም ማድረግ አይቻልም፤ ነገር ግን በመለኮታዊ ጸጋ፣ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ኃይልን ለሰው ይሰጣል፣ እናም በአእምሮ፣ በልብና በባህሪይ ይሠራል። ኃጢአት በጥላቻ ተፈጥሮው የሚታወቀዉና በመጨረሻም ከነፍስ ቤተመቅደስ የሚባረረዉ የክርስቶስን ጸጋ ስንካፈል ነው።"–Selected Messages, bk. 1, p. 366

የሰውን ልብ ሊያድስና ነፍሳትን በክርስቶስ ፍቅር ሊሞላው የሚችል ከመለኮታዊ ሃይል በቀር ምንም ነገር የለም፣ ይህም ለሞተላቸው በፍቅር እራሱን ይገለጣል። የመንፈስ ፍሬ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የዋህነት፣ ራስን መግዛት ነው። አንድ ሰው ወደ እግዚአብሔር ልጅነት ሲለወጥ፣ አዲስ የሞራል ጣዕም ይቀርባል፣ አዲስ ተነሳሽነት ኃይል ይሰጠዋል፣ እና እግዚአብሔር የሚወዳቸውን ነገሮች ይወዳል፤ ሕይወቱ ከየሱስ ሕይወት ጋር በማይለወጥ የተስፋ ቃል የወርቅ ሰንሰለት የታሰረ ነውና። ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ እና የማይገለጽ ምስጋና ነፍስን ያበዛል፣ የተባረከ ሰው እንደበትም ይህ ይሆናል፣ "ተግሳጽህም ታላቅ አድርጎኛል" (መዝሙረ ዳዊት 18:35)።–Ibid., p. 336

### ለ. ወደ መንግሥተ ሰማያት በሚወስደው መንገድ ላይ ለክርስቲያናዊ ጸጋዎች መሻሻል አንዳንድ ደረጃዎች ምንድናቸው? 2ኛ ጴጥሮስ 1:5-11

ምድርን ከሰማይ ጋር የሚያገናኘው መሰላል ክርስቶስ ነው። መሰረቱ በሰብአዊነቱ ውስጥ በምድር ላይ በጥብቅ ተተክሏል፤ ከላይ የመጨረሻዉ የመሰላሉ ደረጃ በመለኮቱ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ይደርሳል። የክርስቶስ ሰብአዊነት የወደቀውን የሰውን ልጅ አቅፎ፣ አምላክነቱ ደግሞ የእግዚአብሔር ዙፋን ይዟል። እኛም የዳንነዉ መሰላሉን በመውጣት፣ ክርስቶስን በመመልከት፣ ከክርስቶስ ጋር በመጣበቅ፣ ደረጃ በደረጃ ወደ ክርስቶስ ከፍታ በመውጣት ጥበብና ጽድቅ ቅድስናና ቤዛነትም ስለተደረገልን ነዉ።–Testimonies for the Church, vol. 6, p. 147.

3. **በእግዚአብሔር ቃል የሚገኝ ኃይል**

**ሀ. ክርስቲያናዊ እድገት ያለማቋረጥ እንዲቀጥል አምላክ አእምሮአችንን የሚያበራልን እንዴት ነው? 2ኛ ቆሮንቶስ 4፡4–6፤ መዝሙር 119:105፤ ዘሌዋውያን 20:7፣ 8**

*የሰው ፈቃድ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ሲተባበር ሁሉን ቻይ ይሆናል። በትእዛዙ የሚደረግ ማንኛውም ነገር በእርሱ ጥንካሬ ሊፈጸም ይችላል። ሁሉም ትዕዛዞቹ የሚቻሉ ናቸው።”*–Christ’s Object Lessons, p. 333

*የባህርይ ፍፁምነት ክርስቶስ ለእኛ በሆነው ላይ የተመሰረተ ነው። በአዳኛችን ትሩፋት ላይ የማያቋርጥ ጥገኛ ከሆንንና በእርሱ ፈለግ ከተጓዝን እንደ እርሱ ንፁህና እርኩሰት የሌለብን እንሆናለን።*

*አዳኛችን የማንንም ነፍስ መጥፋትን አይፈልግም። ለደቀ መዛሙርቱ አንድን ነገር እንዲያደርጉ ጸጋንና ጥንካሬን ሳይሰጣቸው ምላሽን ከእነርሱ አይጠብቅም። እርሱ በትእዛዙ መሠረት ሁሉንም የጸጋ ፍጽምናን ባያደርግ ኖሮ ፍጹማን እንዲሆኑ አይጠራቸውም ነበር። ወላጆች ለልጆቻቸው መልካም ስጦታ ለመስጠት ከምጓጉት ይልቅ እርሱን ለሚለምኑት መንፈስ ቅዱስን ለመስጠት የበለጠ ፈቃደኛ እንደሆነ አረጋግጦልናል።”*–That I May Know Him, p. 130

**ለ. ይህንን የክርስቲያኖች በቃሉ ኃይል በእውነት የማደግ ሂደት ምን እንላለን? ዮሐንስ 1:14፤ 17፡17።**

*“እውነት በህይወት ውስጥ ጸንቶ የሚኖር መርህ ሲሆን ነፍስ ዳግመኛ ትወለዳለች ከሚጠፋ ዘር ሳይሆን ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል። ይህ አዲስ ልደት ክርስቶስን እንደ እግዚአብሔር ቃል የመቀበል ውጤት ነው። በመንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ እውነቶች በልብ ላይ ሲደነቁ፣ አዳዲስ ሐሳቦች ይነሳሉ፣ እናም እስከ አሁን ተኝቶ የነበረው ኃይል ከእግዚአብሔር ጋር ለመተባበር ይነሳሳል።”*–The Acts of the Apostles, p. 520.

*የቤተክርስቲያን መቀደስ ከህዝቡ ጋር ባለው ግንኙነት ሁሉ የእግዚአብሔር ዓላማ ነው። ለዘላለም ቅዱሳን ይሆኑ ዘንድ መረጣቸው። ከራስ ታናሽነት ሁሉ ተለይተው ለእውነት በመታዘዝ ይቀደሱ ዘንድ ልጁን ስለ እነርሱ እንዲሞት አሳልፎ ሰጠ። ከእነርሱም የግል ሥራን፣ የግል እጅ መስጠትን (ራስን አሳልፎ መስጠትን) ይጠይቃል። በእርሱ አምነናል በሚሉት ሰዎች ሊከብሩት የሚችሉት በአምሳሉ እንደተፈጠሩና በመንፈሱ ቁጥጥር ስር ሲሆኑ ብቻ ነው። ከዚያም፣ ለአዳኝ ምስክሮች፣ መለኮታዊ ጸጋ ያደረገላቸው ምን እንደሆነ ማሳወቅ ይችላሉ።”*–Ibid., p. 559.

4. **የውሸት የይገባኛል ጥያቄዎች**

**ሀ. በመጽሐፍ ቅዱስ በዘመናት ሁሉ የነበሩትን የአምላክ ቅዱሳን ሰዎች ስንመለከት፣ የመጨረሻውን ድል ስለመቀዳጀት ምን መረዳት አለብን? 1ኛ ዮሃንስ 1:8፣ 10፤ ሮሜ 7:18፤ ገላትያ 6፡14**

ለዳንኤል የተሰጠው ክብር የመንግሥቱ መሪዎችን ቅናት ቀስቅሷል። ፕሬዚዳንቶቹ እና መኳንንቱ በእሱ ላይ ቅሬታ ለማቅረብ ፈለጉ። "ነገር ግን ምንም ምክንያት ወይም ስህተት ማግኘት አልቻሉም፤ የታመነ ነበርና ስህተትና በደል አልተገኘበትም" (ዳንኤል 6፡4)።

ለመላው ክርስቲያኖች ምን ትምህርት ቀርቧል? በዳንኤል ላይ የቅንዓት ዓይኖች ዕለት ዕለት ይታዩ ነበር። እይታቸው በጥላቻ ተሳለ፤ ነገር ግን በሕይወቱ ውስጥ አንድም ቃል ወይም ድርጊት ስህተት መስሎ ሊያገኙ አልቻሉም። እና አሁንም እርሱ ስለቅድስናዉ አልተናገረም፣ ነገር ግን እጅግ በጣም ጥሩ የሆነውን አደረገ–በታማኝነትና በመቀደስ ሕይወት ኖረ።"–The Sanctified Life, p. 42.

የዉሸት ቅድስና ከመጽሐፍ ቅዱስ ዉጪ ይመራል። ኃይማኖት ወደ ተረትነት ይወርዳል። ስሜቶች መስፈርቶች ይሆናሉ። ኃጢአት የሌለባቸው ነን ብለው በጽድቃቸው ሲመኩ፣ የመቀደስ ጥያቄ አቅራቢዎች ሰዎች የእግዚአብሔርን ሕግ ለመተላለፍ ነፃነት እንዳላቸውና ሥርዓቱን የሚታዘዙ ከጸጋ እንደወደቁ ያስተምራሉ። የይገባኛል ጥያቄዎችን ማቅረቡ ተቃውሚቸውን ያስነሳልና ቁጣንና ንቀትን ያነሳሳል። ስለዚህ ባህሪያቸው በግልጽ ይታያል፣ ምክንያቱም "ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና፥ መገዛትም ተስኖታል።" (ሮሜ 8፡ 7)።–Faith and Works, p. 53.

**ለ. የመቀደስ አስፈላጊነት እናምናለን ማለት መዳናችንን በራሳችን ማግኘት አለብን ማለት ነውን? ዮሐንስ 14:15፤ 1ኛ ዮሐንስ 3:5፣ 6**

ጽድቅ መነሻው እግዚአብሔርን በመምሰል ነው። ማንም ሰው በእግዚአብሔር ላይ እምነት ከሌለውና ከእርሱ ጋር ያለውን ግንኙነት ካላስጠበቀ ጻድቅ ሊሆን አይችልም። የሜዳ አበባ በአፈር ውስጥ ሥር እንዳለው፤ አየርን፣ ጤዛን፣ ዝናብንና ፀሐይን መቀበል እንዳለበት እንዲሁ የነፍስን ሕይወት የሚያገለግለውን ከእግዚአብሔር መቀበል አለብን። ትእዛዙን ለመታዘዝ ኃይልን የምንቀበለው የእሱ ባሕርይ ተካፋዮች በመሆን ብቻ ነው። ማንም ሰው ከፍተኛም ሆነ ዝቅተኛ፣ ልምድ ያለው ወይም ልምድ የሌለው፣ ህይወቱ ከክርስቶስ ጋር በእግዚአብሔር ካልተሰወረ በቀር በባልንጀሮቹ ፊት ንፁህ፣ ሃይለኛ ህይወትን በቋሚነት ሊጠብቅ አይችልም። በሰዎች መካከል ያለው እንቅስቃሴ በጨመረ መጠን የልብ ቁርኝት ከእግዚአብሔር ጋር መቀራረብ ይኖርበታል።"–Testimonies for the Church, vol. 7, p. 194

5. **ስለ መቀደስስ ምን ማለት ይቻላል?**

**ሀ. መቀደስ—በክርስቲያናዊ ባሕርይ ማደግ—በተለይ ይህ እየተፈጸመ ላለበት ግለሰብ ይታወቀዋልን? ማርቆስ 4:26-29 ለሌሎችስ?**

*ያልተጠና፣ አዉቀዉ የማያደርጉት* (unconscious) *የቅድስኛ ህይወት ተጽእኖ ለክርስትና ጥቅም ሊሰጥ የሚችል እጅግ አሳማኝ ስብከት ነው። ክርክር፣ መልስ በማይሰጥበት ጊዜ እንኳን፣ ተቃውሞን ብቻ ሊያስነሳ ይችላል፤ ነገር ግን አምላካዊ ምሳሌነት ሙሉ በሙሉ ለመቃወም የማይቻል ኃይል አለው።”*– The Acts of the Apostles, p. 511

**ለ. ይህ እድገት ቀጣይነት ያለው መሆኑንና በእድገታችንና በስኬቶቻችን ረክተን ማረፍ እንደማንችል የሚያሳየው ምንድን ነው? 1ኛ ቆሮንቶስ 15:31፤ ማቴዎስ 10:22፤ ፊልጵስዩስ 3፡12-16**

*እግዚአብሔር ሁሉም ወንድና ሴት ልጆቹ ደስተኛ፣ ሰላማዊና ታዛዥ እንዲሆኑ ይፈልጋል። . . . በእምነት እያንዳንዱ የባሕርይ ጉድለት ይሞላል፣ እያንዳንዱ ቆሻሻ ይጸዳል፣ እያንዳንዱ ስህተት ይስተካከላል፣ እንዲሁም እያንዳንዱ መልካም ችሎታ ይጎለብታል።*–The Acts of the Apostles, p. 564.

*መቀደስ የአንድ አፍታ፣ የአንድ ሰዓት፣ የአንድ ቀን ስራ አይደለም፣ ነገር ግን የህይወት ዘመን ስራ ነው። በደስተኛ የስሜት በመዋኘት ሳይሆን ያለማቋረጥ ለኃጢአት በመሞትና ለክርስቶስ ያለማቋረጥ የመኖር ውጤት ነው። በደካማ፣ አልፎ አልፎ በሚደረጉ ጥረቶች ስህተቶችን ማስተካከልም ሆነ ማሻሻያዎችን ማድረግ አይቻልም። የምናሸንፈው በረጅም፣ ጽናት ባለው ጥረት፣ በከባድ ተግሣጽና በከባድ ግጭት ብቻ ነው። ግጭታችን በሚቀጥለው ጊዜ ምን ያህል ጠንካራ እንደሚሆን አንድ ቀን አናውቅም። ሰይጣን በሚነግሥበት ጊዜ ሁሉ፣ ራሳችንን በመካድ ኃጢአትን ለማሸነፍ ጥረት እናደርጋለን። ሕይወት እስካለች ድረስ፣ መቆሚያ ቦታ አይኖርም፣ ሙሉ በሙሉ ደረስኩበት የምንልበት ነጥብ የለም። መቀደስ የዕድሜ ልክ መታዘዝ ውጤት ነው።”*– Ibid., pp. 560, 561.



**የግል የግምገማ ጥያቄዎች**

1. *እያንዳንዱን የጽድቅ ቅጽበትን በተመለከተ በእግዚአብሔር ዘንድ ምን ዓይነት አያያዝ ይኖረናል?*

2. *አምላክ ለእኛ ያለው ፍላጎት ከይቅርታ በላይ መሆኑን የሚያሳየው እንዴት ነው?*

3. *የመለወጥ ምስጢር ምንድን ነው?*

4. *የውሸት መቀደስ ወደ ምን ይመራናል?*

5. *ቅድስና ቀጣይነት ያለው የማደግ ሕይወትን እንደሚጨምር እንዴት እናውቃለን?*

# አሮጌዉ ኪዳን

*የመታሰቢያ ጥቅስ፡- እነሆ፥ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል ይላል ጌታ። ዕብራዊያን 8፡8*

*እግዚአብሔር በሰፈሩ ውስጥ የሆነውን አየ። ሰዎቹ፣ መለኮታዊው ክብር ሳይነሳ ገና በሲና ተራራ ላይ እያለ፣ ለሰይጣን ፈተናዎች እንደተገዙ እና ሊታዘዙት ቃል በገቡለት አገዛዝ ላይ እያሴሩ እንደሆነ ተመልክቷል።"*–The Youth's Instructor, November 21, 1901

*ለንባብ የተመረጠዉ፡ አበዉ እና ነቢያት፣ገጽ* 370—373።

**እሁድ** **መጋቢት 3**

1. **ባርነት አእምሮን ግራ ያጋባል**

**ሀ. እስራኤላውያን ለተወሰኑ ዓመታት ያሳለፉት ሁኔታ ምን ይመስል ነበር? ይህ ሁኔታ ስለ አምላክና ስለ ሕጎቹ ያላቸውን እውቀት የጎዳው እንዴት ነው? ዘጸአት 20:1፣ 2፤ ዘዳግም 5:15**

*ዕብራዊያኑ በግብጽ የባርነት ዘመናቸዉ ስለ እግዚአብሔር የነበራቸዉ እዉቀትና የአብርሃምን ኪዳን መርሆች በከፍተኛ መጠን አጥተዉ ነበር። እግዚአብሔር ከግብጽ ሲያወጣቸዉ ይወዱትና ይተማመኑት ዘንድ ኃይሉንና ምህረቱን ሊገልጽላቸዉ ተመኘ። ግብጻዊያዉኑ ወደ እነርሱ እየገፉ ሲመጡና ማምለጫ መንገድ ሲጠፋ፤ ረዳት አልባነታቸዉን በመመልከት የመለኮትን ጣልቃ ገብነት ያስተዉሉ ዘንድ ቁልቁል ወደ ቀይ ባሕር ካመጣቸዉ በኋላ ከአሳዳጆቻቸዉ እጅ አዳናቸዉ። እስራኤላዊያን በታደጋቸዉ አምላካዊ ኃይል ብርቱ መተማመን ይዘዉ እግዚአብሔርን ወደዱት፣ ታላቅ ምስጋናም ሰጡት፤ የግዞት ዘመናቸዉን አክትሞ የራሱ ሕዝብ አድርጓቸዋልና።*

*ነገር ግን አሁንም ታላቅ እዉነት አዕምሯቸዉ ላይ ተጽዕኖ እንዲኖረዉ ይፈለግ ነበር። በጣዖት አምላኪያንና በእርክስና ዉስጥ ከነበሩ ሕዝቦች ጋር አብረዉ በመኖራቸዉ የገዛ ልባቸዉ በማያባራ ኃጢአት ዉስጥ ተዘፍቆ ነበር። የእግዚአብሔርን ሕግ ለመታዘዝና አዳኙ እንደሚያስፈልጋቸዉ ያሳት የነበረዉ ተነሳሽነት እጅግ ደካማ በመሆኑ ስለ እግዚአብሔር ቅድስን እዉነተኛዉ ግንዛቤ አልነበራቸዉም። በመሆኑም እነዚህን ሁሉ መማር የግድ ነበር።"–አበዉና ነቢያት፣ ገጽ*. 420 (1)

**ለ. የሕጉን ቅድስናና ጻዲቅነት ይረዱ ዘንድ እግዚአብሔር ወዴት አመጣቸው? ዘጸአት 19:1፣ 5፣ 6**

2. **የኃጢአት ክፋት**

### ሀ. እስራኤላውያን አምላክ ሲነግራቸው ሕጉን ከተረዱ በኋላ ለበረከት ተስፋዎች ምን ምላሽ ሰጡ? ዘጸአት 19:8፤ 24፡3።

*ያለክርስቶስ የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቅ የማይችሉት እነዚህ ሕዝቦች የገዛ ልባቸዉን ኃጢአተኝነት ሳያስተዉሉ ከእግዚአብሔር ጋር ኪዳን ሊገቡ ተዘጋጁ። የገዛ ጽድቃቸዉን ለማጽናት እንደሚችሉ ሆኖ ስለተሰማቸዉ “እግዚአብሔር ያዉን ሁሉ እናደርጋለን፤ እንታዘዛለን አሉ”* (ዘጸ. 24፡7)። *ሕጉ በአስፈሪ ግርማ ሲታወጅ አማኝ ሆነዉ ከተራራዉ ፊት በፍርሃት ቢንቀጠቀጡም፤ ከእግዚአብሔር ጋር የገቡትን ኪዳን አፍርሰዉ በጥጃ ምስል ለተሠራዉ ጣኦት አጎንብሰዉ ለመስገድ የወሰደባቸዉ ጥቂት ሳምንታት ብቻ ነበሩ። የገቡትን ኪዳን በማፍረሳቸዉ ዳግመኛ የእግዚአብሔርን ቸርነት እናገኛለን ብለዉ ተስፋ ማድረግ አልቻሉም። አሁን ግን ኃጢአተኝነታቸዉን በመመለከትና ይቅርታ እንደሚያሻቸዉ በማሰብ በአብርሃማዊዉ ኪዳን ተገልጾ ነገር ግን በመስዋዕታዊ ስርዓት የተሸፈነዉ አዳኝ እንደሚያስፈልጋቸዉ ተሰማቸዉ። አሁን በእምነት በፍቅር ከኀጢአት ግዞት ወደ አዳናቸዉ አምላክ ዞሩ። በዚህ ወቅት በአዲሱ ኪዳን በረከቶች ደስ ለመሰኘትና ምስጋና ለማቅረብ ዝግጁ ነበሩ።”–አበዉና ነቢያት፣ ገጽ*. 420፣ 421 (1)

### ለ. የዚህ ቃል ኪዳን ውሎች ምን ነበሩ? ዘዳግም 27:26፤ ሕዝቅኤል 20:11፤ ዘሌዋውያን 18:5

### ሐ. ከተፈጥሯዊ ሁኔታችን ጋር በሚመሳሰል መልኩ፣ ምን ሊረዱት አልቻሉም? ኤርምያስ 17:9፤ ኢሳይያስ 1:5፣ 6፤ 64፡6።

*“ኢያሱም ሕዝቡን እንዲህ አለ “እርሱ ቅዱስ አምላክ ነዉ … አመጻችሁን ወይም ኃጢአታችሁን ይቅር አይልም።” ማንኛዉም ዘላቂ ተሃዲሶ ከመምጣቱ አስቀድሞ ሰዎች በሥጋዊ አስተሳሰብ ተገፋፍተዉ እግዚአብሔርን መታዘዝ እንደማይችሉ ሊሰማቸዉ ይገባል። ሕጉን በመጣሳቸዉ እንደ ተላላፊ ስለኮነናቸዉ፤ አንዳችም ማምለጫ መንገድ አልተወላቸዉም ነበር። በራሳቸዉ ጥንካሬና ጽድቅ በመታመናቸዉ ለኀጢአታቸዉ ይቅርታ ለማግኘት ለማግኘት አልተቻላቸዉም። ቅዱሱ አምላካዊ ሕግ የሚጠይቀዉን ባለማሟላታቸዉ እግዚአብሔርን ለማገልገል የገቡት ቃል ከንቱ ነበር። ደህንነት ያገኙ ዘንድ በራሳቸዉ ጥረት ምላሽ ከመስጠት በመቆጠብ፤ ቃል በተገባዉ አዳኝ መታመን ነበረባቸዉ። ይህም በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ ያስችላቸዋል።”*–Ibid., p. 171፣ 172 (2)

## 3. ቃል ኪዳኑን ማጽደቅ

### ሀ. ሙሴ ሕጉን ሁሉንም የእርግማንና የበረከት ሁኔታዎች ካነበበ በኋላ እስራኤላውያን ያለማቋረጥ ምላሽ የሰጡት እንዴት ነው? ዘጸአት 24፡7

የሰዎች አእምሮ የታወረና በባርነት የተዋረደ ስለነበረ፣ የእግዚአብሔርን አስሩ ትእዛዛት መመሪያዎችን ሙሉ በሙሉ ለማስተዋል ዝግጁ አልነበረም። የሕጉን ግዴታዎች ሙሉ በሙሉ እንዲረዱና ተፈፃሚ እንዲያደርጉ፣ የአስሩ ትእዛዛት መመሪያዎችን የሚያሳዩና የሚያስተገብሩ ተጨማሪ መመሪያዎች ተሰጥተዋል። ከየአስሩ ትእዛዛት በተለየ መልኩ እነዚህ ለሙሴ በግል ተሰጥተዋል፤ እሱም ለሕዝቡ እንዲነግራቸው ተደርጓል።"—Fundamentals of Christian Education, p. 506.

ሙሴ የጻፈው አሥርቱን ትእዛዛት ሳይሆን የማይታዘዙ ከሆነ የሚደርስባቸዉን ፍርድ እና ቅድመ ሁኔታዎችን የሚታዘዙት የሚጠብቃቸዉን የተስፋ ኪዳንን ነው። ይህንንም ለሕዝቡ አነበበ፣ እናም እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል ሁሉ እንታዘዛለን በማለት ተስማሙ። ሙሴም ኪዳናቸውን በመጽሐፍ ጻፈ፥ ስለ ሕዝቡም ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን አቀረበ። የቃል ኪዳኑንም መጽሐፍ ወሰደ፥ በሕዝቡም ፊት አነበበ። እግዚአብሔር የተናገረውን ሁሉ እናደርጋለን እንታዘዛለንም አሉ። ሙሴም ደሙን ወስዶ በሕዝቡ ላይ ረጨው፥ እንዲህም አለ፡- "እነሆ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር የገባዉ የቃል ኪዳኑ ደም ይህ ነዉ።" ሕዝቡም ጌታ የተናገረውን ሁሉ ለማድረግ እና ለመታዘዝ የገቡትን ቃል ኪዳን ደገሙት።"–The Spirit of Prophecy, vol. 1, p. 240.

### ለ. እንዲህ ዓይነቱ ስምምነት ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ለማሳየት ወዲያውኑ ምን ተደረገ? ዘጸአት 24:6፣ 8

ስለዚህ ህዝቡ የተናገረውን ሁሉ ለመፈጸምና ለመታዘዝ ለጌታ የገቡትን ቃል ኪዳን አፀደቁ።"–The Signs of the Times, May 6, 1880

እዚህ ህዝቡ የቃል ኪዳኑን ቅድመ ሁኔታዎች ተቀበሉ። በእግዚአብሔርና በየሱስ ክርስቶስ አማኝ ሁሉ መካከል የተደረገውን ቃል ኪዳን የሚያሳይ ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ቃል ኪዳን ገቡ። ቅድመ ሁኔታዎቹ በህዝቡ ፊት በግልፅ ተቀምጠዋል። ቅድመ ሁኔታዎቹን በተሳሳተ መንገድ እንዲረዱ አልተተዉም ነበር። በተሰጡት ሁኔታዎች ሁሉ መስማማታቸዉን ወይም አለመስማማታቸዉን እንዲወስኑ በተጠየቁ ጊዜ ሁሉንም ግዴታዎች ለመታዘዝ በአንድ ድምፅ ተስማምተዋል። ሁሉም የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ለመታዘዝ ተስማምተው ነበር። ሕጉን ለመታዘዝ በቃል ኪዳን ውስጥ ምን ያህል እንደተደረገ እንዲያውቁ የሕጉ መርሆዎች አሁን ተለይተዋል፤ ልዩ ቅጣት የተጣለባቸውን የሕግ ዝርዝሮችም ተቀበሉ።"–Manuscript Releases, vol. 1, p. 114

4. **የጠፋዉ ትውልድ**

**ሀ. አብዛኞቹ የእስራኤል ብሔር ራሳቸውን ማዳን አለመቻላቸውንና ያለ መለኮታዊ እርዳታ ሕጉን መጠበቅ አለመቻላቸውን ስላልተገነዘቡ ምን አጋጠማቸው? ዘኍልቍ 26፡63–65።**

*"እኛ በራሳችን ጥረት የምናደርጋቸዉ ነገሮች በሙሉ በኃጢአት የረከሱ ናቸዉ።"*–Christ's Object Lessons, p. 311

*ኒቆዲሞስ መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ንስሃ መግባት፣ ስለጥምቀትና በመንፈስ ቅዱስ ስለሚያጠምቀዉ ሰዉ ሲሰብክ ሰምቶ ነበር። ኒቆዲሞስ ራሱ አይሁዶች መንፈሳዊ ድህነት እንዳጠቃቸዉ ማለትም የቀኖናዊነትና የዓለማዊ ምኞት ተገዥ መሆናቸዉ ይሰማዉ ነበር። መሲሑ ሲመጣ ሁኔታዎች ይሻሻላሉ የሚል ተሰፋ ነበረዉ። ነገር ግን ልብን የሚመረምረዉ የመጥምቁ መልዕክት የኃጢአተኛነት ስሜት እንዲኖረዉ አላደረገም። ጥንቁቅ ፈሪሳዊ ስለነበረ በጥሩ ሥራዉ ይኮራ ነበር። ስለ በጎ አድራጎቱና ቤተ መቅደሱን ለመርዳት በሚያደርገዉ ልግስና በሰፊዉ የታወቀ ስለነበረ በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስን እንደሚያገኝ ጥርጣሬ አልነበረዉም። እርሱ አሁን ባለበት ሁኔታ ሊያየዉ ብቃት የሌለዉ ፍጹም የሆነ መንግሥት ይኖራል የሚለዉ አስተሳሰብ አስደነገጠዉ።"–የዘመናት ምኞት፣ ገጽ.* 157.

**ለ. ችግሩ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር ወይንስ በዚህ "አሮጌ" ቃል ኪዳን ውስጥ ባሉት ሰዎች? ዕብራውያን 8፡8**

*"ተፈጥሮአዊ* (*የዉርስ*) *ክርስቲያን! ይህ አሳሳች ሃሳብ ለብዙዎችን እንደ የራስ የጽድቅ ልብስ ሆኖ አገልግሏል፣ እና ብዙዎች ስለ እርሱ፣ ስለ ልምምዱ፣ ስለ መከራዎቹ፣ ስለ እራስ የመካድ እና ስለ ራስን የመስዋዕትነት ህይወቱ ምንም እዉቀቱ ሳይኖራቸዉ በክርስቶስ ተስፋ እንዲያደርጉ አድርጓቸዋል። በብዙ የሚመታደቁበት ጽድቃቸው እንደ መርገም* (*እርኩሰት*) *ጨርቅ ብቻ ነው። የተወደደው መምህር ክርስቶስ፡- "በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ።" አዎን፣ በክፉም በመልካምም እርሱን ተከተሉት። በጣም ለተቸገሩትና ወዳጅ ለሌላቸዉን ወዳጅ በመሆን እርሱን ተከተሉት።"*–Testimonies for the Church, vol. 2, pp. 177, 178

*ባለጠጋና ሀብታም እንደሆኑ የሚሰማቸዉ ራቁትነትና ድህነት በምንድር ነው?–ይህ የክርስቶስ ጽድቅ እጦት ነው። በራሳቸው ፅድቅ የረከሰ ጨርቅ እንደለበሱ ተገልጸዋል፣ ነገር ግን በዚህ ሁኔታ የክርስቶስን ጽድቅ እንደለበሱ ራሳቸውን ያሞካሻሉ። ከዚህ የበለጠ ማታለል ሊኖር ይችላልን? በነቢዩ እንደተገለጸዉ ልባቸው በእርኩስትና በክፋት ተሞልቶ እያለ "የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ፣ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እኛ ነን"* (*ኤርምያስ* 7:4*ን ተመልከት*) *እያሉ ይጮሃሉ።*-This Day With God, p. 228.

## 5. ሌላ ቃል ኪዳን ያስፈልጋል

### ሀ. አሮጌው ኪዳን በጣም ተስፋ ስለሌለው፣ በብሉይ ኪዳን ዘመን ለሚኖሩት ተስፋ የሚሰጥ ብቸኛው የተስፋ ቃል ምንድን ነው? ኤርምያስ 31:31-33

በክርስቶስ በማመን ለህግ ሁሉ መታዘዝ ተችሏል።

የባርነት መንፈስ የሚመነጨው በህጋዊ ሀይማኖት መሰረት ለመኖር በመፈለግ፣ የህግ ጥያቄዎችን በራሳችን ሀይል ለማሟላት በመታገል ነው። ለእኛ ተስፋ ያለን በአብርሃም ቃል ኪዳን ሥር ስንሆን ብቻ ነው እርሱም በክርስቶስ የሱስ በማመን የሚገኘው የጸጋ ቃል ኪዳን ነው። ለአብርሃም የተሰበከለት፣ በእርሱም ተስፋ የነበረው ወንጌል ዛሬ የተሰበከልን፣ በእርሱም ተስፋ ያለንበት ወንጌል ነው። አብራሃም የሱስን ተመልክቶ ነበር፣ እርሱም ደግሞ የእምነታችን ጀማሪና ፈጻሚ ነዉ።"–The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 6, p. 1077..

### ለ. በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እነዚህን የመለኮታዊ እርዳታ ተስፋዎች የተቀበሉ ጀግኖችን ጥቀስ። ዕብራውያን 11:4-32

የእምነት ጀግኖች ከዘመን እስከ ዘመን ለእግዚአብሔር ባላቸው ታማኝነት ተለይተው ይታወቃሉ፣ እናም ብርሃናቸው በጨለማ ላሉት እንዲበራ በዓለም ፊት ጎልቶ ቀርቧል። ዳንኤል እና ሦስቱ አጋሮቹ የክርስቲያን ጀግንነት ምሳሌዎች ናቸው። . . . አምላክ በፍጹም ዓላማ እሱን ለሚያገለግሉት ሰዎች ምን እንደሚያደርግላቸው በባቢሎን አደባባይ ካገኙት ተሞክሮ እንማራለን።"– My Life Today, p. 68



## የግል የግምገማ ጥያቄዎች

1. የመለኮታዊውን የሥነ ምግባር ሕግ ትክክለኛ ትርጉም መረዳት ባለመቻላችን የዕብራውያንን ተሞክሮ የምንከተለው እንዴት ነው?
2. ሊፈጽሙት የማይችሏቸውን ቃል ኪዳን ወዲያውኑ የገቡት ለምንድን ነው?
3. በዛሬው ጊዜ ለአምላክ ተመሳሳይ ኪዳኖችን እንድንሰጥ በቀላሉ የምንመራው እንዴት ነው?
4. በቀሪው የእስራኤል ታሪክ ውስጥ ምን እየተፈጸመ ነው?
5. ብሄራዊ ክህደት ለእምነታችን መንገጫገጭ ሰበብ እንደማይሆን የሚያሳዩ ምን ምሳሌዎች አሉን?

# ኑ አብረን እንወያይ

የመታሰቢያ ጥቅስ፡- ኑና እንወያይ ይላል እግዚአብሔር፤ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች፤ እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች።" (ኢሳይያስ 1፡18)።

"ሰበአዊዉን ፍጡር ከመለኮታዊ ፈቃድ ጋር ዳግም በሰላም እንዲመላለስ የሚያስችለዉ የእግዚአብሔር ሕግ የዚህ ኪዳን መሠረት ነበር።"–አበዉና ነቢያት፣ ገጽ. 419 (1)

ለንባብ የተመረጠዉ፡ Thoughts From the Mount of Blessing, pp. 45—77.

**እሁድ መጋቢት 10**

1. **ሁለት ኪዳኖች**

**ሀ. በእግዚአብሔር ዘንድ ለመጽደቅ በእኛ በኩል ምን ዓይነት ስምምነት ያስፈልጋል? መዝሙረ ዳዊት 50:5**

**ለ. እንዲህ ዓይነት ስምምነት ለማድረግ ምን ዓይነት ዝንባሌ ሊኖረን ይገባል? ኢሳ 1፡18**

**ሐ. ምን አይነት የቃል ኪዳን አማራጮች ተሰጥተውናል? ዕብራውያን 8፡ 6-13**

የአሮጌዉ ኪዳን ቅድመ ሁኔታዎች ታዘዙና በሕይወት ኑሩ የሚል አንድምታ አላቸዉ። "ሰው ቢጠብቀዉ ኖሮ በሕይወት በሕይወት የሚኖርበትን ስርዓቴን ሰጠኋቸዉ" (ሕዝቅኤል 20፡11፤ ዘሌዋውያን 18፡ 5)። ነገር ግን "የዚህን ሕግ ቃሎች ያደርግ ዘንድ የማያጸና የተረገመ ይሁን።" ኦሪት ዘዳግም 27፡26። "አዲሱ ኪዳን" የተመሠረተዉ "በተሻሉ ተስፋዎች"–የኃጢአት ይቅርታ ተስፋና የእግዚአብሔር ጸጋ ልብን ለማደስና ከእግዚአብሔር ሕግ መርሆዎች ጋር እንዲስማማ ለማድረግ ነው። ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ቃል ኪዳን ይህ ነው፤ ከዚያ ወራት በኋላ ይላል እግዚአብሔር ሕጌን በልባቸው አኖራለሁ በልባቸውም እጽፈዋለሁ። . . . በደላቸውንም ይቅር እላለሁ፥ ኃጢአታቸውንም መልሼ አልጽፍም። ኤርምያስ 31:33, 34።"–አበዉና ነቢያት፣ ገጽ. 420፣ 421 (1) [በጸሐፊው አጽንዖት ተሰጥቷል።]

2. **ኪዳን ለምን አስፈለገ?**

**ሀ. ከፈጣሪያችን ጋር ከመሆን የሚለየን ምንድን ነው? ኢሳያስ 59፡2 ምን ይገባናል? ዘፍጥረት 2:17፤ ሮሜ 6፡23**

*አዳም በቅጽበት ለሰይጣን ፈተና ተሸንፎ፣ እና እግዚአብሔር አታድርግ ያለውን ነገር አደረገ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ በህያዋንና በሙታን መካከል ቆሞ፡- "ቅጣቱ በእኔ ላይ ይውረድ። በሰው ቦታ እቆማለሁ። ለሰዉ ልጅ ሌላ ፈተና ይሰጠው" ብሎ ሁሉንም ተቀበለ። መተላለፍ መላውን ዓለም በሞት ፍርድ ሥር አስቀመጠ። በሰማይም። "ቤዛ አግኝቻለሁ" የሚል ድምፅ ተሰማ። ኃጢአትን የማያወቀው ለወደቀው ሰው ዘር ሲል ኃጢአት ሆነ። በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፉ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። ክርስቶስ የንግሥና ልብሱን እና የንግሥና አክሊሉን አውልቆ፣ በሰማያት ሁሉ ላይ ያለዉን ስልጣኑን ተወ። ድክመቶችን ሁሉ እንዲሸከምና የሰውን ልጅ ፈተና ሁሉ እንዲቋቋም አምላክነቱን በሰው ልጅ አለበሰው። እሱ የሀዘን ሰው ነበር ሀዘንን ጋር የሚያወቅ። እርሱ ስለ መተላለፋችን ቈሰለ ስለ በደላችንም ደቀቀ። የሰላማችን ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፣ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን። በእርሱ ድህነት ባለጠጎች እንድንሆን ስለ እኛ ድሃ ሆነ። ለእኛ የመላእክትን ስግደት ትቶ ወደ ምድር በመምጣት የካህናቱንና የገዥዎቹን ስድብና ክስ ተቀበለ።"*–The Signs of the Times, June 27, 1900

**ለ. አምላክ ይህን የሞት ፍርድ ለማስወገድ ገና ከመጀመሪያው ምን ዝግጅት አድርጓል? ኢዮብ 33:24፤ እንዲሁም 1ኛ ዮሐንስ 4:19፤ ራእይ 13፡8።**

*ስለመዳናችን የተነደፈዉ ዕቅድ ቀደም ብሎ የታሰበበት እንጂ አዳም ከወደቀ በኋላ የተጠነሰሰ አይደለም። "ምስጥርን መግለጽ ከጥንት ጀምሮ ተሰዉሮ የነበረዉን" ይላልና። ሮሜ* 16፡25። *ይህም ዘላለማዊ የሆነዉን የእግዚአብሔርን ዙፋን መርሖች ለማሳወቅ ነዉ። ከመጀመሪያዉም እግዚአብሔርና ክርስቶስ ስለሰይጣን ክህደትና በሰይጣን አሳሳችነት የሰዉን ወድቀት ያዉቁ ነበር። እግዚአብሔር ኃጢአት ይኖር ዘንድ አላዘዘም። ዳሩ ግን ኃጢአት እንደሚመጣ አስቀድሞ ስላወቀ የመዳኛ ዘዴ ቀየሰ። ለዓለም የነበረዉ ፍቅር ታላቅ ከመሆኑ የተነሳ አንድ ልጁን አሳልፎ ለመስጠት ቃል ገባ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት ትሆንለት ዘንድ" ዮሐንስ* 3:16።– *የዘመናት ምኞት፣ ገጽ*. 12.

3. **የሴቲቱ ዘር**

**ሀ. ያ የቀደመው እባብ ዲያብሎስ በኤደን የመጀመሪያዎቹን ወላጆቻችንን ባታለለ ጊዜ አምላክ ለሰው ልጆች ተስፋ የሚሰጥ ምን ቃል ገብቷል? ዘፍጥረት 3፡15**

*የእኛ ተፈጥሯዊ ዝንባሌዎች በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ካልታረሙ በቀር በዉስጣቸዉ የስነ ምግባርን (ሞራል) ሞት ዘሮችን የያዙ ናቸው። ከእግዚአብሔር ጋር በሙሉ ቁርኝት እስካልሆንን ድረስ፣ ራስን መውደድን፣ ራስን ማስደሰትን፣ እና የኃጢአት ፈተናን ያልተቀደሰ ውጤት መቋቋም አንችልም።”*–Testimonies for the Church, vol. 8, pp. 315, 316

**ለ. ይህ የሴቲቱ ዘር ማን ነው? ዘፍጥረት 22:18፤ ገላትያ 3:8፣ 16፤ ዕብራውያን 2፡14**

*የመጀመሪያው የወንጌል ስብከት ከተሰበከበት በኤደን ገነት የሴቲቱ ዘር የእባቡን ራስ እንደሚቀጠቅጥ ከተነገረበት ጊዜ አንስቶ ክርስቶስ መንገድ፣ እዉነትና ሕይወት መሆኑ ጎልቶ ታይቷል። በአዳም ዘመን አቤል የአዳኛችን ደም ምሳሌ የሆነዉን በግ ደም ለእግዚአብሔር ባቀረበ ጊዜ የሱስ መንገድ ነበር። ክርስቶስ አበዉና ነቢያት የዳኑበት መንገድ ነዉ። ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት የምንችልበት ብቸኛዉ መንገድ እርሱ ነዉ።”–የዘመናት ምኞት፣ ገጽ*. 699፣ 700

**ሐ. አብርሃም ለኃጢአት ይቅርታ ከክርስቶስ በቀር በሌላ በማንም አላመነም፤(ገላትያ 3፡6-8) ታዲያ የእንደዚህ አይነት እምነት ውጤቱ ምን ነበር? ኦሪት ዘፍጥረት 26፡5**

*የክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞቱ፣ የሞት ሥልጣን ያለውን የኃጢአት መስራች የሆነውን መጥፋትን አረጋግጧል። ሰይጣን ሲጠፋ ወደ በክፉ የሚፈትን አይኖርም፤ የኃጢያት ክፍያው ፈጽሞ መደገም አያስፈልገውም፤ እና በእግዚአብሔር ዩኒቨርስ ውስጥ ሌላ አመፅ አደጋም አይኖርም። በዚህ የጨለማ አለም ውስጥ ብቻዉን ከሀጢያት የሚከለክለው በሰማይም ኃጢአትን ይከላከላል። የክርስቶስ ሞት አስፈላጊነት በቅዱሳንና በመላእክት ዘንደ ታይቷል። ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የታረደው በግ ከሌለ የወደቁት የሰዉ ልጆች በእግዚአብሔር ገነት ውስጥ ቤት ሊኖራቸው አይችልም። እንግዲህ የክርስቶስን መስቀል ከፍ ከፍ ማድረግ አያስፈልግምን?*

*መላእክት የእግዚአብሔርን ልጅ ስቃይ ከመመልከት በቀር ራሳቸዉን እንኳን በኃጢአት ከመዉደቅ ለመጠበቅ አስተማማኝ (ብቁ) አይደሉምና ለክርስቶስ ክብርና ዉዳሴን ይሰጣሉ። የሰማይ መላእክት ከክህደት የሚጠበቁት በመስቀሉ ብቃት ነው። ያለ መስቀል ከሰይጣን ውድቀት በፊት ከነበሩት መላዕክቶች የበለጠ ራሳቸዉን ከክፉ ለመጠበቅ ማድረግ የሚችሉት ነገር አይኖራቸዉም። የመላእክት ፍጹምነት በሰማይ ወድቋል። የደስታ ገነት በሆነችው በኤደን የሰው ፍጽምና ወድቋል። በምድርም ሆነ በሰማይ ደኅንነት የሚፈልጉ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር በግ መመልከት አለባቸው።”*–The SDA Bible Commentary [E. G. White Comments], vol. 5, p. 1132.

4. **የቃል ኪዳኑን ማጽደቅ**

**ሀ. ምንም እንኳን ይህ ቃል ኪዳን ከአዳም ጋር የተደረገ እና ለአብርሃም የታደሰ ቢሆንም፤ መቼ ነው የሚፀድቀው - እና ስለዚህ አዲስ ወይስ ሁለተኛው ቃል ኪዳን? ዕብራውያን 9፡16**

ምንም እንኳን ይህ ኪዳን ከአዳም ጋር ተገብቶ ለአብርሃም ቢታደስለትም፤ ነገር ግን እስከ ክርስቶስ ሞት ድረስ መጽደቅ አይችልም ነበር። የደህንነት ፍንጭ በመጀመሪያ ከተሰጠ አንስቶ ኪዳኑ በእግዚአብሔር ተስፋ እዉን ሆኖአል። በእምነት ተቀባይነት ቢያገኝም ነገር ግን በክርቶስ በጸደቀ ጊዜ አዲስ ኪዳን ተብሎ ይጠራል።"–አበዉና ነቢያት፣ ገጽ. 419 (1) [በጸሐፊው አጽንዖት]

**ለ. እስከ የሱስ ሞት ድረስ ካልጸደቀ፣ በመስቀል ፊት ለነበሩት የሰማያዊው ንጉሥ ልጆች እንዴት ይሠራል? ዕብራውያን 6፡13-18**

"ሁለተኛዉ" ወይም "አዲሱ" ኪዳን በክርስቶስ ደም የጸደቀዉና አብርሃማዊዉ በመባል የሚታወቀዉ ነዉ። ኪዳኑ የታተመበት ደም የፈሰሰዉ ከመጀመሪያዉ ኪዳን ደም በኋላ በመሆኑ ይህን መጠሪያ አግኝቷል። አዲሱ ኪዳን በአብርሃም ጊዜ የጸደቀ እግዚአብሔር በገባዉ ቃል ኪንና መሃላ መሆኑ እሙን ነዉ "እግዚአብሔር ከቶ ሊዋሽ አይችልም፤ እርሱ በሁለት በማይለወጡ ነገሮች ... ብርቱ መጽናናት እንድናገኝ አድርጎአል።" ዕብ 6:18ን አንብብ።—አበዉና ነቢያት፣ ገጽ. 420 (1)

ቃሉ የታመነ ነዉ። ተራሮች ይፈልሳሉ፥ ኮረብቶችም ይወገዳሉ፥ ቸርነቱ ግን ከሕዝቡ አይለይም፥ የሰላሙም ቃል ኪዳን አይወገድም። ድምፁም ተሰምቷል፡- "በዘላለም ፍቅር ወድጄሻለሁ" (ኤርምያስ 31፡3)። "በዘላለም ቸርነት እምርሃለሁ" (ኢሳይያስ 54:8) እግዚአብሔር ለጥርጣሬና ለጥያቄዎች መንስኤ የሆኑትን ሁሉ ከሰው ፍርሃትና ድካም ለማስወገድ ራሱን ዝቅ አድርጎ በእምነት ወደ እርሱ የደረሰውን የሚንቀጠቀጥ እጁን የሚይዝ መሆኑ ይህ ፍቅር እንዴት አስደናቂ ነው? እና እርሱ በብዙ ማረጋገጫዎች እና ዋስትናዎች እንድንታመን ይረዳናል። በመታዘዛችን ሁኔታ ላይ አስገዳጅ ስምምነት አድርጎናል፣ እና በራሳችን የነገሮችን መረዳት ሊገናኘን ይመጣል። ከባልንጀሮቻችን የተሰጠ ቃል ኪዳን ወይም ቃል ቢመዘገብም አሁንም ዋስትና ያስፈልገዋል ብለን እናስባለን። የሱስ እነዚህን ሁሉ ልዩ ፍርሃቶች አጋጥሞታል፣ እናም የገባውን ቃል በመሐላ አረጋግጧል፡ - "እግዚአብሔርም የተስፋውን ቃል ለወራሾች አብዝቶ ሊገልጽ ወድዶ የምክሩን የማይለወጥ መሆኑን በመሐላ አጸና። . . . ጌታችን በተስፋዎቹ ላይ ያለንን እምነት ለማጠናከር ከዚህ በላይ ምን ማድረግ ይችላል?"–That I May Know Him, p. 262

**ሐሙስ** **መጋቢት 14**

5. **የልብ ጠረጴዛዎች**

**ሀ. በክርስቶስ በመስቀል ላይ በከፈለው መስዋዕትነት ምን እድል አግኝተናል? ዕብራውያን 9፡15**

**ለ. በእግዚአብሔር ፊት ያለንን ሀላፊነት በምንገመግምበት ወቅት እግዚ-አብሔር ለእያንዳንዳችን በግል ምን ተማጽኖ ያደርጋል? 2ኛ ቆሮ 6፡2**

በድንጋዮቹ ገበታዎች ላይ የተጻፈዉ ተመሳሳይ ሕግ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በልባቸዉ ገበታ ላይ ተጻፈ። የራሳችንን ጽድቅ ለመመስረት በመሄድ ፋንታ የክርስቶስን ጽድቅ መቀበል ይኖርብናል። የእርሱ ደም ኃጢአታችንን ያስተሰርይልናል። ታዛዥነቱም ስለ እኛ ተቀባይነትን ያገኛል። ይህ ሲሆን በመንፈስ ቅዱስ የታደሰዉ ልብ “የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ” ያፈራል። በክርስቶስ ጸጋ በልባችን የሚጻፈዉ የእግዚአብሔር ሕግ ታዛዥ ሆነን እንኖራለን። የክርስቶስ መንፈስ ስለሚኖረን እርሱ እንደተራመደ እንራመዳለን። ክርስቶስ በነቢዩ አማካይነት እንዲህ ሲል ስለራሱ ተናግሮአል “አምላኬ ሆይ ፈቃድህን ላደርግ ወደድሁ ሕግህም በልቤ ውስጥ ነው” መዝሙረ ዳዊት 40:8። በሰዎች ጋር በነበረበት ጊዜ ደግሞ እንዲህ ብሏል “የላከኝ እርሱ ከእኔ ጋር ነዉ፤ ምን ጊዜም የሚያስደስተዉን ስለማደርግ ብቻዬን አልተወኝም። የዮሐንስ ወንጌል 8፡29።

ሐዋርያው ጳውሎስ በአዲሱ ኪዳን በእምነትና በሕጉ መካከል ያለውን ግንኙነት በግልጽ ተናግሯል። እንዲህ ይላል፡- “እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ” “እንግዲህ ሕግን በእምነት እንሽራለንን? እግዚአብሔር ይከልከል፡ ሕግን እናጸናለን እንጂ።” “ከሥጋ የተነሣ ስለ ደከመ ለሕግ ያልተቻለውን፥ እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ በኃጢአትም ምክንያት ልኮ አድርጎአልና፤ እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ ባንመላለስ፤ በእኛ የሕግ ትእዛዝ ይፈጸም ዘንድ ኃጢአትን በሥጋ ኰነነ።” ሮሜ 5:1፤ 3:31፤ 8:3፣ 4።”–አበዉና ነቢያት፣ ገጽ. 421፣ 422 (1)

**አርብ** **መጋቢት 15**

**የግል የግምገማ ጥያቄዎች**

1. ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ከመግባት ጋር በተያያዘ ምን ገጠመኞች አጋጥሚችኋል?

2. አዳም ኃጢአት በሠራ ጊዜ እግዚአብሔር የተዘጋጀው ለምንድን ነው?

3. አምላክ የሚመጣውን መሲሕ ያለማቋረጥ የሰዎች አእምሮ እንዲይዝ ለማድረግ የትኞቹን ምሳሌዎች ተጠቅሟል?

4. አብርሃም በአዲሱ ቃል ኪዳን ሥር እንደነበረ እንዴት እናውቃለን?

5. ከፈጣሪህ ጋር ምን አይነት ቃል ኪዳን ወይም ስምምነት ለማድረግ ተዘጋጅተሃል?

# የተሃድሶ ምክንያት

የሱስ መፈተን ያለባቸውን እንዴት መርዳት እንዳለበት ያውቅ ዘንድ እንደ እኛ በሁሉም ነገር ተፈተነ። የእሱ ሕይወት ምሳሌያችን ነው። ሰው የእግዚአብሄርን ህግ እንዲጠብቅ በፈቃዱ በመታዘዙና ህግን መታዘዝ ሳይሆን መተላለፍ ወደ ባርነት እንደሚያስገባ አሳይቷልል። አዳኙ በምህረትና በፍቅር የተሞላ ነበር፤ በደላቸው ትልቅ ቢሆንም በእውነት ንስሐ የገቡትን ከቶ አልጠላቸውም። እርሱ ግን ሁሉንም ዓይነት ግብዝነት አጥብቆ ወቀሰ። የሰዎችን ኃጢአት ያውቃል፣ ድርጊቶቻቸውንም ሁሉ ያውቃል፣ ሚስጥራዊ ዓላማቸውንም ያነባል። እርሱ ግን በኃጢአታቸው ከእነርሱ አልራቀም። ከኃጢአተኛው ጋር ይማጸናልና ይከራከራል፣ እና በአንድ መልኩ - የሰውን ልጅ ድካም ለመሸከም–ራሱን ከእነርሱ ጋር በአንድ ደረጃ ላይ አደረገ። ኑና እንወያይ ይላል እግዚአብሔር፤ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች፤ እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች።

ሰው የእግዚአብሔርን መልክ በተበላሸ ሕይወት በነፍሱ ያበላሸ፣ በራሱ ጥረት ብቻ በሕይወቱ ውስጥ ሥር ነቀል ለውጥ ሊያመጣ አይችልም። የወንጌልን አቅርቦት መቀበል አለበት፤ ሕጉን በመታዘዝና በየሱስ ክርስቶስ በማመን ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ አለበት። ከዚህ በኋላ ህይወቱ በአዲስ መርህ መመራት አለበት። በንስሐ፣ በእምነት፣ እና በበጎ ሥራ የጽድቅ ባህሪን ይፈጽማል፣ እናም በክርስቶስ ብቃት፣ የእግዚአብሔር ልጅነት መብቶችን ሊቀበል ይችላል። በልባችን ውስጥ የተቀበልነዉን የተከበሩ የመለኮታዊ እውነት መርሆች ልንደርስበት እንችላለን ብለን ወደማናውቀው የሞራል ልቀት ያደርሱናል። . . .

እዚህ ሰው የሚሠራው ሥራ አለ። መስተዋት የሆነውን የእግዚአብሔርን ሕግ ፊት ለፊት በመሆን የሥነ ምግባር ጉድለቱን በማስተዋልና የባሕርይ ልብሱን በበጉ ደም በማጠብ ኃጢአቱን ማስወገድ አለበት። ምቀኝነት፣ ትዕቢት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ ክርክር፣ እና ወንጀል የክርስቶስን ፍቅር ተቀባይ ከሆነውና እንደ እርሱ የመሆንን ተስፋ ከሚንከባከበው ልብ ይጸዳሉ። ...

ነገር ግን የወንጌል ተስፋ ተጽእኖ ኃጢአተኛው የእግዚአብሔርን ህግ በመጣስ እየኖረ የክርስቶስን ማዳን እንደ ነጻ ጸጋ እንዲመለከት አይመራውም። የእውነት ብርሃን በልቡናው ላይ ሲወጣና የእግዚአብሔርን መመዘኛዎች በሚገባ ሲረዳ እና የበደሉን መጠን ሲያውቅ መንገዱን ያስተካክላል፣ ከአዳኙ በተገኘው ሀይል ለእግዚአብሔር ታማኝ ይሆናል እናም አዲስና ንጹህ ህይወት ይመራል።"–Testimonies for the Church, vol. 4, pp. 294, 295

# የመጀመሪያ ሰንበት ሥጦታዎች




ታህሳስ 29
የመጀመሪያ ሰንበት ሥጦታ በሰሜን ካውካሰስ፣ ሩሲያ በአዲጂያ ውስጥ ላለው የትምህርትና የጤና ማእከል

ጥር 27
የመጀመሪያ ሰንበት ሥጦታ ለአለም የአደጋ እፎይታ






የካቲት 25
የመጀመሪያ ሰንበት ሥጦታ በሰሜን ህንድ ዩኒየን በፓታንኮት ውስጥ ላለው የጸሎት ቤት